# የሐዋርያት ሥራ

## መግቢያ

የሐዋርያት ሥራ ከሉቃስ ወንጌል የቀጠለ ነው፤ የመጽሐፉ ዋና ዓላማ የመጀመሪያዎቹ የኢየሱስ ተከታዮች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ስለ እርሱ የሚናገረውን የምሥራች ቃል "በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ አገር ሁሉ፣ በሰማርያ፣ እስከ ምድርም ዳርቻ" (1፥8) ወንጌልን እንዴት እንዳሰራጩ ለመተረክ ነው፤ መጽሐፉ የክርስትና እምነት በአይሁዳውያን መካከል ተጀምሮ የመላው ዓለም ሕዝብ እምነት እስኪሆን ድረስ እንዴት እንደተስፋፋ የሚናገር ታሪክ ነው። ጸሐፊው፣ ክርስቲያኖች የሮምን ንጉሠ ነገሥታዊ መንግሥት ለመቀናቀን ውስጥ ለውስጥ ሤራ የሚፈጽሙ ሰዎች እንዳልሆኑና የክርስትና ሃይማኖት፣ የአይሁዳውያንን ሃይማኖት ፍጹም የሚያደርግ እንደሆነ ለማስረዳት ብርቱ ጥረት አድርጎአል።

የሐዋርያት ሥራ፣ ስለ ኢየሱስ የሚናገረው የምሥራች ቃል የሚደርስበት ቦታ በየጊዜው እየሰፋ መሄዱንና የቤተ ክርስቲያንን መመሥረት በሚያንጸባርቁ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደብ ይችላል፦

1. የክርስትና ሃይማኖት ከኢየሱስ ወደ ሰማይ መውጣት በኋላ በኢየሩሳሌም ስለ መጀመሩ።
2. በእስራኤል አገር በሙሉ ስለ መዳረሱ።
3. ሮምን ጨምሮ በሜድትራኒያን ባሕር ዙሪያ ባሉት አገሮች መስፋፋቱ።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ጐላ ብሎ የሚታየው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሲሆን፣ በጸንጠቆስጤ ቀን በኢየሩሳሌም በነበሩት አማኞች ላይ በኀይል መውረዱን፣ እንዲሁም በመጽሐፉ ውስጥ በተዘረዘሩት ድርጊቶች ሁሉ እንደታየው መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንና መሪዎችዋን መምራቱንና ማበረታታቱን ይጨምራል። በጥንት ጊዜ ይቀርብ የነበረው የክርስትና መልእክት በልዩ ልዩ ስብከቶች ውስጥ በአስተዋጽዖ መልክ ቀርቦአል፤ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተፈጸሙት ድርጊቶችም መልእክቱ በአማኞች ሕይወትና በቤተ ክርስቲያን ኅብረት የነበረው ኀይል ምን ያህል ታላቅ መሆኑን ያስረዳሉ።

---

## ምዕራፍ 1

1 ቴዎፍሎስ ሆይ!
በመጀመሪያው መጽሐፌ ኢየሱስ የሠራው
ንና ያስተማረውን ሁሉ ጽፌአለሁ፤ የጻፍሁትም
ኢየሱስ ሥራውን ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ፣
2 ወደ ሰማይ እስከ ወጣበት ቀን ድረስ የሠራውን
ነው፤ ወደ ሰማይ የወጣውም ለመረጣቸው ሐዋ
ርያት ትእዛዙን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከሰ
ጣቸው በኋላ ነው፤ 3 ብዙ መከራ ተቀብሎ
ከሞተ በኋላ በብዙ ግልጽ ማስረጃዎች ሕያው
ሆኖ ታያቸው፤ አርባ ቀን ሙሉ እየተገለጠላቸ
ውም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አስተማራ
ቸው። 4 አብሮአቸውም በነበረ ጊዜ እንዲህ ሲል
አዘዛቸው፣ "እኔ የነገርኋችሁን ከአብ የተሰጠ
ተስፋ ጠብቁ እንጂ ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤
5 ዮሐንስ በውሃ አጠመቀ፤ እናንተ ግን ከጥቂት
ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ።"

### ኢየሱስ ወደ ሰማይ ወጣ

6 እነርሱ በአንድነት ተሰብስበው ሳሉ "ጌታ
ሆይ! መንግሥትን ለእስራኤል መልሰህ የምትሰ
ጥበት ጊዜ አሁን ነውን?" ሲሉ ጠየቁት።
7 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፣
"አብ በገዛ ሥልጣኑ የወሰነውን ጊዜና ዘመን
እናንተ ልታውቁት አትችሉም። 8 ነገር ግን
መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኀይ
ልን ትቀበላላችሁ፤ በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም፣
በይሁዳ አገር ሁሉ፣ በሰማርያ፣ እስከ ምድርም
ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።" 9 ይህን
ንም ካለ በኋላ እነርሱ እያዩት ወደ ሰማይ
ወጣ፤ ደመናም ከዐይናቸው ሰወረው።
10 እርሱ በሚሄድበት ጊዜ እነርሱ ወደ
ሰማይ ሲመለከቱ፣ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት
ሰዎች አጠገባቸው ቆመው፣ 11 "እናንተ የገ
ሊላ ሰዎች፣ ስለምን ወደ ሰማይ እየተመለከታ
ችሁ ቆማችኋል? ይህ ወደ ሰማይ ሲወጣ ያያች
ሁት ኢየሱስ፣ ወደ ሰማይ ሲወጣ ባያችሁት
ዐይነት ተመልሶ ይመጣል" አሉአቸው።

### በይሁዳ ምትክ ማትያስ ተመረጠ

12 ከዚህ በኋላ ደብረ ዘይት ከተባለው ተራራ
ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ የደብረ ዘይት
ተራራ ከኢየሩሳሌም የሚርቀው አንድ ኪሎ
ሜትር ያህል ነው። 13 ወደ ኢየሩሳሌም መጥ
ተው ወደሚኖሩበት ሰገነት ላይ ወጡ፤ እነር
ሱም "ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ፣ ያዕቆብ፣ እንድር
ያስ፣ ፊልጶስ፣ ቶማስ፣ በርቶሎሜዎስ፣ ማቴ
ዎስ፣ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ ቀናተኛው
ስምዖንና የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ" ናቸው።
14 እነዚህ ሁሉ ዘወትር ለጸሎት በአንድነት ይሰ
በሰቡ ነበር፤ ከእነርሱም ጋር አንዳንድ ሴቶችና
የኢየሱስ እናት ማርያም እንዲሁም የኢየሱስ
ወንድሞች ነበሩ።
15 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መቶ ሃያ በሚያህሉ
አማኞች መካከል ቆመና እንዲህ አለ፣ 16 "ወን
ድሞች ሆይ! ኢየሱስን ለያዙት ሰዎች መሪ ስለ
ሆናቸው ስለ ይሁዳ፣ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ
በዳዊት አፍ የተናገረው የትንቢት ቃል መፈ
ጸም ነበረበት። 17 ይሁዳ ከእኛ አንዱ ሆኖ የሥ
ራችን ተካፋይ ነበር። 18 ነገር ግን ይህ ሰው
በክፉ ሥራው ዋጋ መሬት ገዛ፤ በግንባሩም
ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ፤ አንጀቱም ተዘረ
ገፈ፤ 19 ይህም ነገር በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ
ሁሉ ታወቀ፤ ስለዚህ ያ መሬት በቋንቋቸው
'አኬልዳማ' ተብሎ ተጠራ፤ ትርጓሜውም
'የደም መሬት' ማለት ነው።
20 "ይህም የሆነበት ምክንያት በመዝሙር
መጽሐፍ፣
'መኖሪያው ባዶ ይሁን፤
ማንም አይኑርበት፣
ደግሞም ሹመቱን ሌላ ሰው ይውሰድበት'
የሚል ተጽፎ ስለነበር ነው።
21 "ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ በእኛ መካከል በተ
መላለሰበት ጊዜ ሁሉ ከእኛ ጋር አብረውን ከነ
በሩት፣ 22 እንዲሁም ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ
ጌታ ኢየሱስ ወደ ሰማይ እስከወጣበት ቀን
ድረስ አብረውን ከነበሩት ከነዚህ ሰዎች አንዱ
ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር እንዲሆን ያስፈ
ልጋል።"
23 ከዚህ በኋላ ሁለት ሰዎች አቀረቡ፤ እነር
ሱም በርሳባ ወይም ኢዮስጦስ የሚባለው ዮሴ
ፍና ማትያስ ነበሩ። 24 እንዲህ ሲሉም ጸለዩ፣
"የሰውን ሁሉ ልብ የምታውቅ ጌታ ሆይ! ከነ
ዚህ ከሁለቱ ማንን እንደመረጥህ አሳየን፤ 25 የም
ንጸልየውም ይሁዳ ወደ ራሱ ስፍራ ሲሄድ የተወ
ውን አገልግሎትና ሐዋርያነት በመቀበል የሚተ
ካውን እንድትገልጥልን ነው።" 26 ዕጣም በጣሉ
ጊዜ ዕጣው ለማትያስ ወጣ፤ ስለዚህ እርሱ ከዐ
ሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቈጠረ።

## ምዕራፍ 2

### መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ ወረደ

1 የአይሁድ ፋሲካ ባለፈ በኀምሳኛው ቀን
በሚከበረው በጴንጠቆስጤ በዓል ደቀ መዛሙ
ርቱ ሁሉ በአንድነት በአንድ ቦታ ተሰብስበው
ነበር፤ 2 በድንገት ብርቱ ዐውሎ ነፋስ የመሰለ
ድምፅ ከሰማይ መጣ፤ የነበሩበትንም ቤት
ሞላው። 3 የእሳት ነበልባሎች የሚመስሉ ምላ
ሶች ታዩአቸው፤ ተከፋፍለውም በእያንዳንዳ
ቸው ላይ ዐረፉባቸው። 4 ሁሉም በመንፈስ
ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስ ቅዱስ እንዲናገሩ በሰ
ጣቸው ችሎታ መጠን በሌሎች ቋንቋዎች መና
ገር ጀመሩ።
5 በዓለም ካሉት አገሮች ሁሉ የመጡ መንፈ
ሳውያን አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር።
6 ይህንንም ድምፅ በሰሙ ጊዜ ብዙ ሰዎች ተሰ
በሰቡ፤ በየቋንቋቸውም ሲናገሩ ስለሰሙአቸው
ተደነቁ። 7 በመገረምና በመደነቅም እንዲህ
አሉ፣ "እነዚህ እንዲህ የሚናገሩት ሁሉ የገ
ሊላ ሰዎች አይደሉምን? 8 ታዲያ እኛ በየትው
ልድ አገራችን ቋንቋ ሲናገሩ የምንሰማቸው እን
ዴት ነው? 9 እኛ በጳርቴ፣ በሜድ፣ በዔላም፣
በመስጴጦምያ፣ በይሁዳ፣ በቀጰዶቅያ፣ በጳን
ጦስ፣ በእስያ፣ 10 በፍርግያ፣ በጵንፍልያ፣ በግ
ብጽ፣ በቀሬና አጠገብ ባሉት በሊቢያ አውራጃ
ዎች የምንኖር ነን፤ ከሮምም የመጣን አይሁዳ
ውያንና ወደ አይሁድነትም የገባን እንገኛለን፤
11 እንዲሁም የቀርጤስና የዐረብ ሰዎች ይገ
ኛሉ፤ እነሆ እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔርን
ታላቅ ሥራ በየቋንቋችን ሲናገሩ እንሰማለን!"
12 ስለዚህ ሁሉም ተገርመውና የሚሉትን አጥ
ተው "ይህ ነገር ምን ይሆን!" ተባባሉ።
13 አንዳንዶቹ ግን "አዲስ የወይን ጠጅ ጠጥ
ተው ሰክረዋል!" እያሉ አፌዙባቸው።

### የጴጥሮስ ንግግር

14 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ከዐሥራ አንዱ ጋር
ቆመና ድምፁን ከፍ አድርጎ ለሕዝቡ እንዲህ

---

1፥1 ፦ ሉቃ. 1፥1-4። 1፥4 ፦ ሉቃ. 24፥49። 1፥5 ፦ ማቴ. 3፥11፤ ማር. 1፥8፤ ሉቃ. 3፥16፤ ዮሐ. 1፥33።
1፥8 ፦ ማቴ. 28፥19፤ ማር. 16፥15፤ ሉቃ. 24፥47-48። 1፥9 ፦ ማር. 16፥19፤ ሉቃ. 24፥50-51።
1፥13 ፦ ማቴ. 10፥2-4፤ ማር. 3፥16-19፤ ሉቃ. 6፥14-16። 1፥18-19 ፦ ማቴ. 27፥3-8። 1፥20 ፦ መዝ. 69፥25፤ 109፥8።
1፥22 ፦ ማቴ. 3፥16፤ ማር. 1፥9፤ 16፥19፤ ሉቃ. 3፥21፤ 24፥51። 2፥1 ፦ ዘሌ. 23፥15-21፤ ዘዳ. 16፥9-11።

ሲል ተናገረ ፥ "እናንተ የይሁዳ አገር ሰዎችና
የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁሉ ይህን የሆነውን
ነገር ለማወቅ ንግግሬን አዳምጡ ፤ [15]ቢጠዋቱ
ገና ሦስት ሰዓት ስለሆነ እናንተ እንዳሰባችሁት
እነዚህ ሰዎች አልሰከሩም ። [16]ነገር ግን ይህ
የሆነው ነቢዩ ኢዮኤል እንዲህ ሲል የተናገረው
ቃል እንዲፈጸም ነው ፥

17 'እግዚአብሔር በመጨረሻው ቀን እንዲህ
ይሆናል ይላል ፤
መንፈሴን በሰው ሁሉ ላይ አፈሳለሁ ፤
ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት
ይናገራሉ ፥
ጕልማሶቻችሁም ራእይ ያያሉ ፥
ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ ።
18 እንዲሁም በእነዚያ ቀኖች
በወንዶችና በሴቶች አገልጋዮቼ ላይ
መንፈሴን አፈስሳለሁ ፤
እነርሱም ትንቢት ይናገራሉ ።
19 በላይ በሰማይ ድንቅ ነገሮችን ፥
በታች በምድር ተአምራትን
አሳያለሁ ፤
ደምና እሳት የጢስ ጭጋግም
ይታያል ።
20 ታላቁና አስገራሚው
የእግዚአብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት
ፀሐይ ይጨልማል ፤
ጨረቃም ደም ትመስላለች ።
21 የእግዚአብሔርንም ስም የሚጠራ ሁሉ
ይድናል ።'

22 "የእስራኤል ሰዎች ሆይ! ይህን ቃል
አዳምጡ ፤ እናንተም እንደምታውቁት የናዝ
ሬቱ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ
የተገለጠ መለኮታዊ ሥልጣን ያለው ነው ፤
ይኸውም በእርሱ አማካይነት እግዚአብሔር
ተአምራትን ፥ ድንቅ ነገሮችንና ታላላቅ ምልክ
ቶችን ሁሉ በእናንተ ፊት በማድረጉ ተረጋግጦ
አል ። 23 ይህም ሰው እግዚአብሔር አስቀድሞ
ባቀደውና ባወቀው አሠራር መሠረት ለእናንተ
ተላልፎ ተሰጠ ፤ እናንተም በዐመፀኞች እጅ
እንዲሰቀልና እንዲሞት አደረጋችሁት ። 24 እግ
ዚአብሔር ግን የሞትን ኀይል አስወግዶ ከሞት
አስነሣው ፤ ምክንያቱም ሞት ይዞ ሊያስቀረው
አልቻለም ። 25 ዳዊትም ስለ እርሱ እንዲህ
ይላል ፥

'እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በፊቴ
አየዋለሁ ፥
ከእኔም ጋር ስለሆነ አልናወጥም ፥
26 ስለዚህ ልቤን ደስ አለው ፤
አንደበቴም በደስታ ተሞላ ፤
እንዲሁም ሟች የሆነው ሥጋዬ
በተስፋ ይኖራል ፤
27 ምክንያቱም ነፍሴን በሙታን ዓለም
አትተዋትም ፤
ቅዱስህንም በመቃብር ፈርሶ እንዲቀር
አታደርገውም ።
28 የሕይወትን መንገድ አስታወቅኸኝ ፤
ከእኔም ጋር በመሆንህ ደስታዬ ፍጹም
ይሆናል ።'

29 "ወንድሞቼ ሆይ! ከቀድሞ አባቶች
አንዱ የሆነው ዳዊት እንደሞተና እንደተቀበረ ፥
መቃብሩም እስከ ዛሬ በእኛ ዘንድ እንዳለ በግ
ልጥ ልነግራችሁ እችላለሁ ። 30 ነገር ግን ዳዊት
ይህን የተናገረው ፥ ነቢይ ስለነበረና እግዚአብ
ሔር 'ከዘርህ አንዱን በዙፋንህ ላይ አስቀምጥል
ሃለሁ' ሲል በመሐላ የሰጠውን የተስፋ ቃል
ያውቅ ስለነበር ነው ፤ 31 በዚህም ምክንያት
መሲሕ በሲኦል እንደማይቀርና ሥጋውም በመ
ቃብር ፈርሶ እንደማይቀር አስቀድሞ አይቶ ስለ
ትንሣኤው ተናገረ ። 32 ይህን ኢየሱስን እግዚአ
ብሔር ከሞት አስነሣው ፤ እኛም ሁላችን ለዚህ
ነገር ምስክሮች ነን ። 33 ስለዚህ እርሱ በእግዚአ
ብሔር ቀኝ በክብር በመቀመጡና ከአብ የተሰ
ጠውን ተስፋ መንፈስ ቅዱስን በመቀበሉ ፥
ይህን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው ።
34-35 እንግዲህ ወደ ሰማይ የወጣው ዳዊት ባለ
መሆኑ ዳዊት ራሱ እንዲህ ሲል ተናግሮአል ፥
'እግዚአብሔር ለጌታዬ (ለመሲሑ)
ጠላቶችህን በሥልጣንህ ሥር
እስካደርግልህ ድረስ
በቀኜ ተቀመጥ' ብሎታል ።

36 "እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን
ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታና መሲሕ እንዳደረ
ገው የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ በእርግጥ
ይወቅ!"

37 ሰዎቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ልባቸው በሐ
ዘን ተነክቶ ጴጥሮስንና ሌሎቹን ሐዋርያት
"ወንድሞች ሆይ! እንግዲህ ምን እናድርግ?"
አሉአቸው ።

38 ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው ፥ "ንስሐ
ግቡ ፤ ኃጢአታችሁም ይቅር እንዲባልላችሁ
እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠ
መቁ ፤ የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን መንፈስ
ቅዱስንም ትቀበላላችሁ ፤ 39 ምክንያቱም የተስ
ፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ፥ ጌታ አም
ላካችን ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ
ትም ሁሉ ነው ።"

40 በሌላም በብዙ ቃል እየመሰከረ "በዚህ
ጠማማ ትውልድ ላይ ከሚመጣው ቅጣት
ራሳችሁን አድኑ" በማለት መከራቸው ።
41 ከእነርሱ ብዙዎቹ ቃሉን ተቀብለው ተጠ
መቁ ፤ በዚያን ቀን ሦስት ሺ የሚያህሉ አማ
ኞች ተጨመሩ ። 42 እነርሱም የሐዋርያትን
ትምህርት በመስማት ፥ በወንድማማችነት
አብሮ በመኖር ፥ እንጀራ በመቍረስና በጸሎት
ይተጉ ነበር ።

### የአማኞች የወንድማማችነትና የኅብረት ኑሮ

43 በዚያን ጊዜ በሐዋርያት እጅ ብዙ ተአም
ራትና ድንቅ ነገሮች ይደረጉ ስለ ነበር በሁሉም
ላይ ፍርሃት አደረባቸው ። 44 አማኞች ሁሉ በአ
ንድነት አብረው ይኖሩ ነበር ፤ ያላቸውም ነገር
ሁሉ የጋራ ነበር ። 45 መሬታቸውንና ንብረታቸ
ውን እየሸጡ ገንዘቡን ለእያንዳንዱ እንደሚያስ
ፈልገው ያከፋፍሉ ነበር ። 46 በየቀኑ በቤተ
መቅደስ በአንድነት ይሰበሰቡ ነበር ፤ በቤታቸ
ውም እንጀራ እየቈረሱ በደስታና በጥሩ ልብ
ይመገቡ ነበር ፤ 47 እግዚአብሔርንም ያመሰግኑ
ነበር ፤ ሰውም ሁሉ ያከብራቸው ነበር ፤ እግዚ
አብሔርም የሚድኑትን ሰዎች በየቀኑ ወደ ማኅ
በራቸው ይጨምር ነበር ።

## ምዕራፍ 3

### ሽባው ተፈወሰ

1 አንድ ቀን ጴጥሮስና ዮሐንስ በጸሎት ሰዓት
ወደ ቤተ መቅደስ ይሄዱ ነበር ፤ ጊዜውም
ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ነበር ፤ 2 እዚያ "ውብ በር"
እየተባለ የሚጠራ ስፍራ ነበር ፤ ሲወለድ
ጀምሮ ሽባ የሆነ አንድ ሰው ነበረ ፤ እርሱንም
ሰዎች በየቀኑ እያመጡ እዚያ ያስቀምጡት
ነበር ፤ እርሱ እዚያ ተቀምጦ ወደ ቤተ መቅ
ደስ ከሚገቡት ሰዎች ምጽዋት ይለምን ነበር ።
3 ይህ ሰው ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ቤተ መቅደስ
ሲገቡ አይቶ ምጽዋት ለመናቸው ። 4 እነርሱም
ሰውየውን ትኵር ብለው አዩትና ጴጥሮስ "ወደ
እኛ ተመልከት" አለው ። 5 እርሱም ምጽዋት
የሚሰጡት መስሎት ትኵር ብሎ አያቸው ።
6 ጴጥሮስ ግን "ብርና ወርቅ የለኝም ፤ ያለኝን
ግን እሰጥሃለሁ ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ
ስም ተነሥና ተራመድ" አለው ። 7 ቀኝ እጁ
ንም ይዞ አስነሣው ፤ ወዲያውኑ እግሩና ቍርጭ
ምጭሚቱ በረታ ። 8 ብድግ ብሎም ቆመ ፤ እየ
ተራመደም ከእነርሱ ጋር ወደ ቤተ መቅደስ
ገባ ፤ እየተራመደና እየዘለለም እግዚአብሔርን
ያመሰግን ነበር ። 9 ሰዎቹም ሁሉ ፥ ሲራመድና
እግዚአብሔርን ሲያመሰግን አዩት ። 10 "ውብ
በር" እየተባለ በሚጠራው በቤተ መቅደሱ በር
አጠገብ ተቀምጦ ምጽዋት ይለምን የነበረው
እርሱ መሆኑን ዐወቁ ፤ በእርሱ ላይም በሆነው
ነገር ይገረሙና ይደነቁ ጀመር ።

### ጴጥሮስ በቤተ መቅደስ ያደረገው ንግግር

11 የዳነው ሰውዬ ከጴጥሮስና ከዮሐንስ አል
ይም በማለት ይዞአቸው ሳለ ፥ ሰዎቹ ተደንቀው
"የሰሎሞን መመላለሻ" ወደሚባለው ስፍራ
ወደ እነርሱ ሮጠው ሄዱ ፤ 12 ጴጥሮስም ሰዎ
ቹን ባየ ጊዜ እንዲህ አላቸው ፥ "የእስራኤል
ሰዎች ሆይ! በዚህ ነገር ስለምን ትደነቃላችሁ
ስለምንስ ትኵር ብላችሁ ታዩናላችሁ? እኛ
በራሳችን ኀይል ወይም በራሳችን መልካም
ሥራ ይህን ሰው እንዲራመድ ያደረግነው ይመ
ስላችኋልን? 13 የአብርሃም ፥ የይስሐቅ ፥ የያ
ቆብ አምላክ ፥ የአባቶቻችን አምላክ ልጁን ኢየ
ሱስን አከበረው ፤ እናንተ ግን እርሱን በጲላጦ
ፊት አሳልፋችሁ ሰጣችሁት ፤ ጲላጦስም ሊለቅ
ቀው ቢፈልግ እንኳ 'አንፈልግም' አላችሁ ።
14 እናንተ ቅዱሱንና ጻድቁን 'አንፈልገውም'
ብላችሁ ፥ አንድ ነፍሰ ገዳይ እንዲፈታላችሁ
ለመናችሁ ። 15 ሕይወት ሰጪ የሆነውንም ገደ
ችሁት ፤ እግዚአብሔር ግን ከሞት አስነሣው ፤
ስለዚህ ነገር እኛ ምስክሮች ነን ። 16 ይህ የምታ
ዩትና የምታውቁት ሰው ድኖ የበረታው ፥ በኢየ
ሱስ ስም በተገኘው እምነት ነው ፤ በኢየሱስ
ስም በማመኑም በሁላችሁ ፊት ሙሉ ጤና አግ
ኝቶአል ።

17 "አሁንም ወንድሞቼ ሆይ! በኢየሱስ ላይ
ያደረጋችሁት ነገር እናንተም እንዳለቆቻችሁ
ባለማወቅ እንዳደረጋችሁት ዐውቃለሁ ። 18 እግ
ዚአብሔር ግን አስቀድሞ በነቢያት ሁሉ አፍ
'መሲሑ መከራ መቀበል አለበት' ያለው ቃል
እንዲፈጸም አደረገ ። 19 እንግዲህ ኃጢአታችሁ
እንዲደመሰስላችሁ ንስሓ ገብታችሁ ወደ እግዚ
አብሔር ተመለሱ ፤ 20 ከእግዚአብሔርም ዘንድ
የመታደስ ዘመን ይመጣላችኋል ፤ እግዚአብሔር
አስቀድሞ ለእናንተ የመረጠውን መሲሕ ኢየሱ
ስን ይልክላችኋል ። 21 እርሱም በሰማይ የሚቆ
የው እግዚአብሔር አስቀድሞ በቅዱሳን ነቢያቱ
አፍ እንደተናገረው ዓለም ሁሉ እስኪታደስ
ድረስ ነው ። 22 ሙሴም እንዲህ ብሎአል ፥ 'እግ
ዚአብሔር አምላክ እኔን እንዳስነሣኝ እንዲሁ
ከወንድሞቻችሁ መካከል ነቢይ ያስነሣ
ላችኋል ፤ እርሱ የሚነግራችሁን ሁሉ ስሙ ፤
23 ያን ነቢይ የማይሰማ ሁሉ ከሕዝብ ተለይቶ
ይጥፋ ።' 24 ቀጥሎም ከሳሙኤል ጀምሮ የነበሩ
ነቢያት ሁሉ ስለዚህ ዘመን እንዲሁ ተናግረ
ዋል ። 25 እናንተ የነቢያት ወራሾች ናችሁ ፤
እንዲሁም እግዚአብሔር ለአብርሃም 'በምድር

2፥17-21 ፡- ኢዩ. 2፥28-32 ። 2፥23 ፡- ማቴ. 27፥35 ፤ ማር. 15፥24 ፤ ሉቃ. 23፥33 ፤ ዮሐ. 19፥18 ።
2፥24 ፡- ማቴ. 28፥5-6 ፤ ማር. 16፥6 ፤ ሉቃ. 24፥5 ። 2፥25-28 ፡- መዝ. 16፥8-11 ። 2፥30 ፡- መዝ. 132፥11 ፤
2ሳሙ. 7፥12-13 ። 2፥34-35 ፡- መዝ. 110፥1 ።

2፥44 ፡- ሐ.ሥ. 4፥32-35 ። 3፥13 ፡- ዘጸ. 3፥15 ። 3፥14 ፡- ማቴ. 27፥15-23 ፤ ማር. 15፥6-14 ፤ ሉቃ. 23፥13-23 ፤
ዮሐ. 19፥12-15 ። 3፥22 ፡- ዘዳ. 18፥15 ፤18 ። 3፥23 ፡- ዘዳ. 18፥19 ። 3፥25 ፡- ዘፍ. 22፥18 ።

ላይ ያሉ ሕዝቦች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ’ ብሎ
ከአባቶቻችን ጋር የገባው የቃል ኪዳን ወራሾች
ናችሁ ። 26 ስለዚህ እግዚአብሔር ልጁን የላከው
በመጀመሪያ ለእናንተ ነበር ፤ ይህንንም ያደረ
ገው እያንዳንዳችሁን ከክፉ መንገዳችሁ በመመ
ለስ እንዲባርካችሁ ነው ።”

## ምዕራፍ 4

### ጴጥሮስና ዮሐንስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቀረቡ

1 ጴጥሮስና ዮሐንስ ለሕዝቡ ሲናገሩ ሳሉ ፥
ካህናትና[1*] የቤተ መቅደሱ የዘበኞች አለቃ ፥
እንዲሁም ሰዱቃውያን ወደ እነርሱ መጡና ፥
2 ሁለቱ ሐዋርያት የኢየሱስን ከሞት መነሣት
በማስተማራቸውና በዚህም የሙታን ትንሣኤ
መኖሩን በማስረዳታቸው ተቈጡ ። 3 ስለዚህ
ያዙአቸውና ጊዜው መሽቶ ስለነበረ እስከ ማግ
ሥቱ ድረስ በወህኒ ቤት እንዲቆዩ አደረጉአ
ቸው ። 4 ነገር ግን ቃላቸውን ከሰሙት ሰዎች
ብዙዎቹ አመኑ ፤ የአመኑትም ሰዎች ቊጥር
ወደ አምስት ሺ ከፍ አለ ።

5 በማግሥቱ የአይሁድ አለቆችና ሽማግሌ
ዎች የሙሴ ሕግ መምህራንም በኢየሩሳሌም
ተሰበሰቡ ። 6 ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል ሊቀ
ካህናቱ ሐናና ቀያፋ ፤ ዮሐንስና እስክንድሮስ ፥
የሊቀ ካህናቱም ወገኖች ሁሉ ይገኙባቸዋል ፤
7 እነርሱም ሁለቱን ሐዋርያት በመካከላቸው
አቁመው “ይህን ያደረጋችሁት በምን ኀይልና
በማን ስም ነው?” ሲሉ ጠየቁአቸው ።

8 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞ
ልቶ እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥ “እናንተ የሕ
ዝብ አለቆችና ሽማግሌዎች ሆይ! 9 እኛ ዛሬ
የምንጠየቀው ለአንድ ሽባ ሰው ስለ ተደረገለት
መልካም ሥራና በምን ዐይነት ሁኔታ እንደዳነ
ነው ። 10 ይህ ሰው ድኖ በፊታችሁ የቆመው ፥
እናንተ በሰቀላችሁትና እግዚአብሔርም ከሞት
ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እን
ደሆነ ለእናንተ ለሁላችሁና ለእስራኤል ሕዝብ
ሁሉ የታወቀ ይሁን ። 11 እናንተ ግንበኞች ንቃ
ችሁ የጣላችሁትም ድንጋይ እርሱ ነው ፤ ነገር
ግን እርሱ የማእዘን ዋና ድንጋይ ሆነ ። 12 ስለ
ዚህ ደኅንነት ከእርሱ በቀር በሌላ በማንም
የለም ፤ ምክንያቱም እኛ ልንድንበት የሚገባን
እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠው ስም ከእርሱ
በቀር በመላው ዓለም ማንም የለም ።”

13 ጴጥሮስና ዮሐንስ በድፍረት መናገራቸ
ውን የሸንጎ አባሎች ባዩ ጊዜ ያልተማሩ ተራ
ሰዎች መሆናቸውን ያውቁ ስለነበረ ተደነቁ ፤
ከኢየሱስ ጋር እንደነበሩም ዐወቁ ፤ 14 የዳነው
ንም ሰው ከእነርሱ ጋር ቆሞ በማየታቸው በእነ
ርሱ ላይ የሚሉትን አጡ ። 15 ስለዚህ ከሸንጎው
ወዲያ ገለል አደረጉአቸውና በቆይታ እንዲህ
ሲሉ ተማከሩ ። 16 “እንግዲህ በእነዚህ ሰዎች
ላይ ምን እናድርግ? ይህ ታላቅ ተአምር በእነ
ርሱ እጅ መደረጉ በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁሉ
ታውቆአል ፤ ስለዚህ ልንክደው አንችልም ።
17 ነገር ግን በሕዝቡ ዘንድ እየተስፋፋ እንዳይ
ሄድ ከእንግዲህ ወዲህ የኢየሱስን ስም በመጥ
ራት ለማንም እንዳይናገሩ በብርቱ እናስጠንቅቃ
ቸው ።”

18 ከዚህ በኋላ ጠሩአቸውና የኢየሱስን ስም
በመጥራት ከቶ እንዳይናገሩ ወይም እንዳያስተ
ምሩ በጥብቅ አዘዙአቸው ። 19 ጴጥሮስና ዮሐ
ንስ ግን እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው ፥ “ለእግዚአ
ብሔር ከመታዘዝ ይልቅ ለእናንተ መታዘዝ በእ
ግዚአብሔር ፊት ተገቢ ነውን? እስቲ እናንተ
ራሳችሁ ፍረዱ ። 20 እኛስ ያየነውንና የሰማነ
ውን ከመናገር አንቈጠብም ።” 21 የሕዝብ አለ
ቆችና የሸንጎው አባሎች ጴጥሮስንና ዮሐንስን
የሚያስቀጣ ምንም ምክንያት ባለማግኘታ
ቸው ፥ ሕዝቡንም ስለፈሩ እንደገና አስጠንቅ
ቀው ለቀቁአቸው ፤ ምክንያቱም ሕዝቡ በሆነው
ነገር እግዚአብሔርን ያመሰግን ስለ ነበር ነው ።
22 በዚህ ተአምር የተፈወሰው ያ ሰው ዕድሜው
ከአርባ ዓመት በላይ ነበር ።

### ሐዋርያትና አማኞች በስደት ጊዜ ያደረጉት ጸሎት

23 ጴጥሮስና ዮሐንስ ተለቅቀው ወደ ጓደኞ
ቻቸው በተመለሱ ጊዜ የካህናት አለቆችና የአይ
ሁድ ሽማግሌዎች ያሉአቸውን ሁሉ ነገሩአ
ቸው ። 24 እነርሱም ይህንን በሰሙ ጊዜ ድምፃ
ቸውን በአንድነት ከፍ አድርገው ወደ እግዚአ
ብሔር እንዲህ ሲሉ ጸለዩ ፥ “ሰማይን ፥ ምድ
ርን ፥ ባሕርን ፥ በውስጣቸው የሚኖረውን ሁሉ
የፈጠርህ ልዑል እግዚአብሔር ሆይ! 25 በመን
ፈስ ቅዱስ አማካይነት በአገልጋይህ በአባታችን
በዳዊት አፍ እንዲህ ብለህ የተናገርህ አንተ
ነህ ፥

‘አረማውያን ስለምን በቊጣ
አጒረመረሙ?
ሕዝቦችስ ስለምን በከንቱ ዶለቱ?
26 የምድር ነገሥታት ተሰልፈው ፥
ገዢዎችም በአንድነት ተሰብስበው ፥
በእግዚአብሔርና በመሲሑ ላይ
በጠላትነት ተነሡ ።’

27 “በእርግጥም ሄሮድስና ጴንጤናዊ ጲላ
ጦስ ከአረማውያንና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር
በዚህች ከተማ ተሰብስበው መሲሕ ባደረግኸው

[1*] 4፥1 ካህናት ፦ አንዳንድ ቅጂዎች “ሊቃነ ካህናት” ይላሉ ።
4፥11 ፦ መዝ. 118፥22 ። 4፥24 ፦ ዘጸ. 20፥11 ፤ ነህ. 9፥6 ፤ መዝ. 146፥6 ። 4፥25-26 ፦ መዝ. 2፥1-2 ።
4፥27 ፦ ማቴ. 27፥1-2 ፤ ማር. 15፥1 ፤ ሉቃ. 23፥1 ፥7-11 ፤ ዮሐ. 18፥28-29 ።



በቅዱሱ አገልጋይህ በኢየሱስ ላይ ተነሡ ፤
28 እንዲህም የሆነው አንተ አስቀድመህ በገዛ
ኀይልህና በገዛ ፈቃድህ ያቀድኸውን ለመፈ
ጸም ነው ፤ 29 አሁንም ጌታ ሆይ! ዛቻቸውን
ተመልከት ፤ አገልጋዮችህ ቃልህን ያለ ፍርሃት
በድፍረት እንዲናገሩ አድርግ ፤ 30 በቅዱሱ
ልጅህ በኢየሱስ ስም በሽተኞች እንዲድኑና
ተአምራትም ፥ ድንቅ ነገሮችም እንዲደረጉ
እጅህን ዘርጋ ።”

31 ከጸለዩ በኋላ የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ ፤
ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ ፤ የእግዚአብሔ
ርንም ቃል ያለ ፍርሃት በድፍረት ተናገሩ ።

### የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የኅብረት ኑሮ

32 አማኞች ሁሉ አንድ ልብና አንድ አሳብ
ነበራቸው ፤ ማንም ሰው “ይህ የእኔ ነው” የሚ
ለው ነገር አልነበረውም ፤ በመካከላቸውም
ሁሉ ነገር የጋራ ነበር ፤ 33 ሐዋርያትም የጌታን
የኢየሱስን ትንሣኤ በታላቅ ኀይል ይመሰክሩ
ነበር ፤ በሁሉም ላይ ታላቅ የእግዚአብሔር ጸጋ
ነበረ ። 34 መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ
እየሸጡ ገንዘቡን ያመጡ ስለነበር በመካከላ
ቸው አንድም ችግረኛ አልነበረም ። 35 ገንዘቡ
ንም አምጥተው ለሐዋርያት ያስረክቡ ነበር ።
ለእያንዳንዱ እንደ አስፈላጊነቱ ይታደል ነበር ።
36 የቆጵሮስ ተወላጅ የሆነ ዮሴፍ የሚባል
አንድ ሌዋዊ ነበረ ፤ ሐዋርያት “በርናባስ”
እያሉ ይጠሩት ነበር ፤ ትርጓሜው “የመጽናናት
ልጅ” ማለት ነው ። 37 እርሱም መሬቱን ሸጠና
ገንዘቡን አምጥቶ ለሐዋርያት አስረከበ ።

## ምዕራፍ 5

### ሐናንያና ሰጲራ

1 ሐናንያ የሚባል አንድ ሰው ሰጲራ ከምት
ባለው ሚስቱ ጋር ሆኖ መሬት ሸጠ ፤ 2 ሚስ
ቱም እያወቀች ከመሬቱ ሽያጭ ከፊሉን አስቀ
ረና ከፊሉን አምጥቶ ለሐዋርያት አስረከበ ፤
3 ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው ፥ “ሐናንያ ሆይ!
በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንድትዋሽና ከመሬቱም
ሽያጭ ከፊሉን እንድታስቀር ያደረገህ ሰይጣን ፥
ስለምን ወደ ልብህ ገባ? 4 ሳትሸጠው በፊት
መሬቱ የአንተ አልነበረምን? ከሸጥከውስ በኋላ
ገንዘቡ የአንተ አልነበረምን? ታዲያ ይህን ነገር
ስለምን በልብህ አሰብህ? የዋሸኸው በእግዚአብ
ሔር ላይ ነው እንጂ በሰው ላይ አይደለም ።”
5 ሐናንያ ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ወደቀና ሞተ ፤
ይህን ነገር የሰሙ ሰዎች ሁሉ እጅግ ፈሩ ።
6 ጒልማሶች ተነሥተው አስከሬኑን ከፈኑና ወስ
ደው ቀበሩት ።

7 ከሦስት ሰዓት በኋላ የሐናንያ ሚስት ወደ
ዚያ መጣች ፤ በባልዋም ላይ የደረሰበትን ነገር
አላወቀችም ነበር ። 8 ጴጥሮስም “እስቲ ንገሪኝ
መሬታችሁን የሸጣችሁት ይህን ለሚያህል ገን
ዘብ ነውን?” አላት ። እርስዋም “አዎ ፥ ይህን
ለሚያህል ገንዘብ ነው” አለች ።
9 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ “የእግዚአብሔርን መን
ፈስ ለመፈታተን እንዴት ተስማማችሁ? እነሆ
ባልሽን ቀብረው የሚመለሱት ሰዎች በበር
ናቸው ፤ አንቺንም ወስደው ይቀብሩሻል”
አላት ። 10 እርስዋም በድንገት በእግሩ ሥር
ወደቀችና ሞተች ፤ ጒልማሶችም ሲገቡ ሞታ
አገኙአትና ወስደው በባልዋ አጠገብ ቀበሩ
አት ። 11 በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህን ነገር
በሰሙ ሰዎች ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ ።

### በሐዋርያት እጅ የተደረጉ ተአምራትና ድንቅ ነገሮች

12 ብዙ ተአምራትና ድንቅ ነገሮች በሕዝቡ
መካከል በሐዋርያት እጅ ይደረጉ ነበር ፤
ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው በሰሎሞን መመላ
ለሻ ይሰበሰቡ ነበር ። 13 ከእነርሱ ውጭ ከሆኑት
ሰዎች አንድ እንኳ ከእነርሱ ጋር ለመሆን የሚ
ደፍር አልነበረም ፤ ይሁን እንጂ ሕዝቡ ያከብራ
ቸው ነበር ። 14 በጌታ የሚያምኑ ወንዶችና
ሴቶች ቊጥራቸው በጣም እየበዛ ይሄድ ነበር ።
15 በሐዋርያት እጅ ይደረጉ በነበሩት ድንቅ
ሥራዎች ምክንያት ፥ ሰዎች ብዙ በሽተኞችን
ወደ መንገድ እያወጡ ፥ በአልጋ ላይና በሰሌን
ላይ ያስተኙአቸው ነበር ፤ እንዲህም ያደረጉት
ጴጥሮስ በዚያ በኩል ሲያልፍ ጥላው እንኳ በአ
ንዳንዶቹ ላይ እንዲያርፍባቸው ነበር ።
16 ሰዎች በኢየሩሳሌም ዙሪያ ካሉት ከተሞች
በሽተኞቻቸውንና በርኩሳን መናፍስት የሚሠቃ
ዩትን ያመጡ ነበር ፤ ሁሉም ይድኑ ነበር ።

### በሐዋርያት ላይ ስደት ተነሣ

17 ሊቀ ካህናቱና ከእርሱ ጋር የነበሩት የሰዱ
ቃውያን ወገኖች ሁሉ በጠላትነት ተነሡ ፤ በቅ
ንአትም ተሞልተው ፥ 18 ሐዋርያትን ያዙና
በሕዝቡ ወህኒ ቤት አስገቡአቸው ። 19 የእግዚአ
ብሔር መልአክ ግን በሌሊት የወህኒ ቤቱን በር
ከፍቶ አስወጣቸውና ፥ 20 “ሂዱ ፥ በቤተ መቅ
ደስ ቆማችሁ ይህን የሕይወት ቃል ሁሉ ለሕ
ዝቡ ንገሩ” አላቸው ፤ 21 ሐዋርያቱም ትእዛዙን
ተቀብለው በማለዳ ወደ ቤተ መቅደስ ገቡና
ማስተማር ጀመሩ ። በዚያን ጊዜ ሊቀ ካህናቱና
ከእርሱ ጋር የነበሩት መጥተው የሸንጎውን አባ
ሎችና የአይሁድ ሽማግሌዎችን ሁሉ በአንድ
ነት ሰበሰቡ ፤ ሐዋርያትንም እንዲያመጡአቸው

4፥32 ፦ ሐ.ሥ. 2፥44-45 ።

ሰዎችን ወደ ወህኒ ቤት ላኩ ። 22 መልእክተ
ኞቹ ግን ወደ ወህኒ ቤት ሄደው ሐዋርያትን
በዚያ አላገኙአቸውም ፤ ተመልሰውም
መጡና ፣ 23 “የወህኒ ቤቱ በር በጥብቅ ተቈልፎ
ጠባቂዎችም በበሩ ፊት ቆመው አገኘናቸው ፤
የወህኒ ቤቱን በር በከፈትነው ጊዜ ግን በውስጥ
ማንንም አላገኘንም” ብለው ተናገሩ ። 24 የቤተ
መቅደሱ ዘብ አዛዥና የካህናት አለቆች ይህን
በሰሙ ጊዜ “ይህ ነገር ምን ይሆን?” በማለት
ተገርመው ስለ እነርሱ የሚሉትን አጡ ።
25 በዚህ ጊዜ አንድ ሰው መጣና “በወህኒ ቤት
ያስገባችኋቸው ሰዎች እነሆ በቤተ መቅደስ
ቆመው ሕዝቡን ያስተምራሉ” ብሎ ነገራ
ቸው ። 26 ወዲያውኑ የቤተ መቅደሱ የዘበኞች
አለቃና ሎሌዎቹ ሄደው አመጡአቸው ፤ ያመ
ጡአቸውም በኀይል ሳይሆን በማግባባት ነው ፤
ይህንንም ያደረጉት ሕዝቡ በድንጋይ እንዳይወ
ግራቸው በመፍራት ነው ።
27 አምጥተውም በሸንጎው ፊት አቆሙአ
ቸው ፤ ሊቀ ካህናቱም እንዲህ ሲል ጠየቃ
ቸው ፤ 28 “የኢየሱስን ስም በመጥራት እንዳታስ
ተምሩ በጥብቅ አዘናችሁ ነበር ፤ ነገር ግን
እነሆ ኢየሩሳሌምን በትምህርታችሁ
ሞላችኋት ፤ እናንተ እኮ የዚያን ሰው ደም
በእኛ ላይ ልታደርጉብን ትፈልጋላችሁ ።”
29 ጴጥሮስና ሌሎች ሐዋርያት ግን እንዲህ
ሲሉ መለሱ ፣ “ለሰው ከመታዘዝ ለእግዚአብ
ሔር መታዘዝ ይገባናል ፤ 30 የአባቶቻችን አም
ላክ እናንተ በእንጨት ላይ ሰቅላችሁ የገደላች
ሁትን ኢየሱስን ከሞት አስነሣው ፤ 31 እግዚአብ
ሔር ለእስራኤል ሕዝብ ንስሓንና የኀጢአትን
ይቅርታ እንዲሰጥ ይህን ኢየሱስን መሪና አዳኝ
አድርጎ በክብር በቀኙ አስቀመጠው ፤ 32 ስለዚህ
ነገር እኛ ምስክሮች ነን ፤ እግዚአብሔር ለሚታ
ዘዙት ሁሉ የሰጣቸው መንፈስ ቅዱስም ምስ
ክር ነው ።”
33 የሸንጎ አባሎች ይህን በሰሙ ጊዜ በጣም
ተቈጥተው ሐዋርያቱን ለመግደል ፈለጉ ።
34 ነገር ግን በሕዝቡ የተከበረና የሙሴ ሕግ
መምህር የሆነ ገማልያል የተባለ አንድ ፈሪሳዊ
ተነሣና ለጥቂት ጊዜ ሐዋርያቱን ገለል እንዲያ
ደርጉአቸው አዘዘ ። 35 ከዚህ በኋላ የሸንጎውን
አባሎች እንዲህ አላቸው ፣ “የእስራኤል ሰዎች
ሆይ! በእነዚህ ሰዎች ላይ ምን እንደምታደርጉ
ተጠንቀቁ ። 36 ከዚህ በፊት ቴዎዳስ የሚባል
ሰው ‘እኔ ትልቅ ሰው ነኝ’ ብሎ ተነሥቶ
ነበር ፤ አራት መቶ የሚያህሉም ሰዎች ከእርሱ
ጋር ተባብረው ነበር ። ነገር ግን እርሱ ተገደለ ፤
ተከታዮቹ ተበታተኑ ፤ ዓላማውም እንዳልነበረ
ሆነ ። 37 ከዚያም በኋላ የሕዝብ ቈጠራ በተደረ
ገበት ዘመን ገሊላዊው ይሁዳ ተነሥቶ ብዙ
ሰዎች እንዲከተሉት አድርጎ ነበር ፤ እርሱም
ተገደለ ፤ የተከተሉትም ሁሉ ተበታተኑ ።
38 ስለዚህ አሁንም እኔ የምላችሁ ፣ ከነዚህ
ሰዎች እንድትርቁና እንድትተዉአቸው ነው ፤
ምክንያቱም ይህ አሳብ ወይም ሥራ ከሰው
የመጣ ከሆነ ይጠፋል ። 39 ከእግዚአብሔር
የመጣ ከሆነ ግን እነርሱን ልታጠፉአቸው አት
ችሉም ፤ እንዲያውም ከእግዚአብሔር ጋር
መጣላት ይሆንባችኋል ።” እነርሱም የገማልያ
ልን ምክር ተቀበሉ ።
40 ከዚህ በኋላ ሐዋርያቱን ወደ እነርሱ ጠር
ተው አስገረፉአቸው ፤ የኢየሱስንም ስም በመጥ
ራት እንዳይናገሩ አዘዙአቸውና ለቀቁአቸው ።
41 ሐዋርያት ግን ስለ ኢየሱስ ስም ውርደት ለመ
ቀበል የተገቡ በመሆናቸው ደስ እያላቸው ከሸን
ጎው ወጥተው ሲሄዱ ፤ 42 በየቀኑም በቤተ መቅ
ደስና በየቤቱም ስለ መሲሑ ኢየሱስ ማስተማር
ንና የምሥራች መናገርን አላቋረጡም ነበር ።

## ምዕራፍ 6

### ሰባት ዲያቆናት ተመረጡ

1 ከጥቂት ጊዜ በኋላ የአማኞች ቍጥር እየ
በዛ ሲሄድ የግሪክ ቋንቋ የሚናገሩ አይሁዳው
ያን ፣ የይሁዳ አገር ተወላጆች በሆኑት አይሁዳ
ውያን ላይ ማጒረምረም ጀመሩ ፤ ምክንያቱም
በየቀኑ ይታደል በነበረው ዕርዳታ መበለቶቻቸ
ውን ችላ ይሉባቸው ስለነበር ነው ። 2 ስለዚህ
ዐሥራ ሁለቱ ፣ አማኞችን ሁሉ ሰብስበው እን
ዲህ አሉአቸው ፣ “ምግብ ለማደል ብለን ፣ የእ
ግዚአብሔርን ቃል የማስተማር ሥራችንን
መተው አይገባንም ። 3 እንግዲህ ወንድሞች
ሆይ! በመልካም ጠባያቸው የተመሰገኑ ፣ በመ
ንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ ፣ ሰባት ሰዎችን
ከመካከላችሁ ምረጡ ፤ እነርሱን ለዚህ ኀላፊነት
እንሾማቸዋለን ። 4 እኛ ግን በመጸለይና የእግዚ
አብሔርን ቃል በማስተማር እንተጋለን ።”
5 ይህ አባባል ሁሉንም ደስ አሰኘ ፤ ቀጥሎ
ያሉትንም ሰዎች መረጡ ፣ በእምነትና በመን
ፈስ ቅዱስ የተሞላ እስጢፋኖስ ፣ ፊልጶስ ፣ ጵሮ
ኮሮስ ፣ ኒቃሮና ፣ ጢሞና ፣ ጰርሜና ወደ አይሁ
ድነት ገብቶ የነበረው የአንጾኪያው ኒቆላዎስ ።
6 እነዚህን በሐዋርያት ፊት አቆሙአቸው ፤ ሐዋ
ርያትም ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው ።
7 በዚህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ቃል እየተስ
ፋፋ ስለሄደ በኢየሩሳሌም የአማኞች ቍጥር
በጣም እየበዛ ሄደ ፤ ከካህናትም ብዙዎቹ
አመኑ ።

### ዲያቆኑ እስጢፋኖስ ተያዘ

8 እስጢፋኖስ በጸጋና በኀይል ተሞልቶ
ድንቅ ነገሮችንና ታላላቅ ተአምራትን በሕዝቡ

5፥28 ፦ ማቴ. 27፥25 ።



መካከል ያደርግ ነበር ፤ 9 በዚያን ጊዜ “የነጻ
ወጪዎች ምኩራብ” የተባለው የአይሁድ
ጸሎት ቤት ሰዎች ፣ የቀሬናና የእስክንድርያ
ሰዎች ፣ የኪልቅያና የእስያ ሰዎች ተነሥተው
እስጢፋኖስን በመቃወም ይከራከሩት ነበር ።
10 ነገር ግን እስጢፋኖስ ይናገርበት የነበረውን
ጥበብና መንፈስ መቋቋም አልቻሉም ። 11 በዚ
ያን ጊዜ “ይህ ሰው በሙሴና በእግዚአብሔር
ላይ የስድብ ቃል ሲናገር ሰምተነዋል” የሚሉ
ሰዎችን በስውር አነሣሡበት ። 12 በዚሁ ዐይነት
ሕዝቡንና ሽማግሌዎቹን የሙሴ ሕግ መምህራ
ንንም አነሣሡ ፤ ወደ እስጢፋኖስም ሄዱና
ይዘው በሸንጎው ፊት አቀረቡት ። 13 በእርሱ
ላይ በሐሰት የሚመሰክሩ አንዳንድ ሰዎችንም
አመጡ ፤ የሐሰት ምስክሮችም እንዲህ አሉ ፣
“ይህ ሰው በዚህ ቤተ መቅደስ ላይና በሙሴ
ሕግ ላይ የስድብ ቃል ከመናገር አይቈጠብም ።
14 ደግሞም ‘ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ቤተ
መቅደስ ያፈርሳል ፤ ሙሴም ያስተላለፈልንን
ሥርዓት ይለውጣል’ ብሎ ሲናገር ሰምተነ
ዋል ።” 15 በዚህ ጊዜ በሸንጎው የተገኙት ሁሉ
እስጢፋኖስን ትኵር ብለው ሲመለከቱት ፊቱ
እንደ መልአክ ፊት ሆኖ ታያቸው ።

## ምዕራፍ 7

### የእስጢፋኖስ ንግግር

1 ሊቀ ካህናቱ እስጢፋኖስን “ይህ የተባለው
ነገር ልክ ነውን?” ሲል ጠየቀው ።
2 እስጢፋኖስም እንዲህ ሲል መለሰ ፣ “ወን
ድሞቼና አባቶቼ ሆይ! እስቲ ስሙኝ ፤ አባታ
ችን አብርሃም በካራን ለመኖር ከመሄዱ በፊት
ገና በመስጴጦምያ ሳለ የክብር አምላክ ተገለጠ
ለትና ፣ 3 ‘ከአገርህ ወጥተህ ፣ ከዘመዶችህ ተለይ
ተህ ፣ እኔ ወደማሳይህ አገር ሂድ’ አለው ።
4 በዚያን ጊዜ ከከለዳውያን አገር ወጥቶ በካራን
ተቀመጠ ፤ አባቱ ከሞተ በኋላም እግዚአብሔር
ከካራን አውጥቶ ዛሬ እናንተ ወደምትኖሩበት
አገር አመጣው ። 5 ይሁን እንጂ የእግር ማሳረ
ፊያ እንኳ የሚያህል ርስት አልሰጠውም ፤ ነገር
ግን ይህችን አገር ለእርሱና ለዘሩ በኋላ ርስት
አድርጎ እንደሚሰጠው ቃል ገብቶለት ነበር ፤
ይህን ቃል የገባለትም አብርሃም ገና ልጅ ሳይኖ
ረው ነበር ። 6 ዘሩም በባዕድ አገር ስደተኛ ሆኖ
እንደሚኖርና በዚያም አገር አራት መቶ ዓመት
ባሪያ አድርገው በጭቈና እንደሚገዙት ነግሮት
ነበር ። 7 ቀጥሎም ‘ባሪያ አድርጎ በሚገዛው
ሕዝብ ላይ እፈርድበታለሁ ፤ ከዚያም በኋላ ነጻ
ወጥተው በዚህ ስፍራ ያመልኩኛል’ ብሎ እግ
ዚአብሔር ተናግሮአል ። 8 የመገረዝንም ኪዳን
ሰጠው ፤ ስለዚህ አብርሃም ይስሐቅን በወለደው
ጊዜ በስምንተኛው ቀን ገረዘው ፤ እንዲሁም
ይስሐቅ ልጁን ያዕቆብን ገረዘው ። ያዕቆብም የነ
ገድ አባቶች የሆኑትን ዐሥራ ሁለቱን ልጆቹን
ገረዘ ።
9 “የያዕቆብ ልጆች በወንድማቸው በዮሴፍ
ላይ ቀንተው በግብጽ አገር ባሪያ እንዲሆን
ሸጡት ፤ እግዚአብሔር ግን ከእርሱ ጋር ነበረ ፤
10 ከመከራው ሁሉ አወጣው ፤ በግብጽ ንጉሥ
በፈርዖን ፊትም ሞገስንና ጥበብን ሰጠው ። ንጉ
ሡም በግብጽና በቤቱም ሁሉ ላይ አዛዥ አደረ
ገው ። 11 በዚያን ጊዜ በግብጽና በከነዓን አገር
ሁሉ ላይ ታላቅ ችግር ያስከተለ ረሀብ ሆነ ፤
አባቶቻችንም ምግብ ሊያገኙ አልቻሉም ።
12 ያዕቆብም በግብጽ እህል መኖሩን በሰማ ጊዜ
አባቶቻችንን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደዚያ ላከ ።
13 ደግመኛ ወደ ግብጽ ተመልሰው በሄዱ ጊዜ
ዮሴፍ ለወንድሞቹ ተገለጠ ፤ ቤተ ዘመዱም
በፈርዖን ዘንድ ታወቀ ። 14 ከዚህ በኋላ ዮሴፍ
አባቱን ያዕቆብንና ዘመዶቹን ሁሉ ወደ እርሱ
አስመጣቸው ፤ እነርሱም በጠቅላላው ሰባ አም
ስት ሰዎች ነበሩ ። 15 ስለዚህ ያዕቆብ ወደ
ግብጽ ሄደ ፤ እርሱና አባቶቻችን እዚያ ሞቱ ።
16 ዐጽማቸው ወደ ሴኬም ተወስዶ አብርሃም
በሴኬም ከኤሞር ልጆች በገንዘቡ በገዛው መቃ
ብር ተቀበረ ።
17 “እግዚአብሔር ለአብርሃም በመሐላ የሰ
ጠው ተስፋ የሚፈጸምበት ጊዜ ሲቃረብ በግ
ብጽ የነበረው የሕዝባችን ቍጥር እየበዛ ሄደ ።
18 ይህም የሆነው ዮሴፍን የማያውቅ ሌላ
ንጉሥ በግብጽ እስከ ነገሠበት ጊዜ ድረስ ነው ።
19 አዲሱ ንጉሥ በሕዝባችን ላይ በተንኰል ተነ
ሥቶ ሕፃናቶቻቸው እንዲሞቱ ፣ ወደ ውጭ
አውጥተው እንዲጥሉዋቸው አባቶቻችንን አስገ
ደዳቸው ። 20 በዚያን ጊዜ ሙሴ ተወለደ ፤
እርሱ በእግዚአብሔር ፊት ያማረ ሕፃን ነበር ፤
ሦስት ወር በአባቱ ቤት አደገ ፤ 21 ወደ ውጭም
በተጣለ ጊዜ የፈርዖን ሴት ልጅ አነሣችውና
እንደ ልጅዋ አድርጋ አሳደገችው ። 22 ሙሴም
የግብጻውያንን ጥበብ ሁሉ ተማረ ፤ በቃሉና
በሥራውም የበረታ ሆነ ።
23 “ሙሴ አርባ ዓመት በሞላው ጊዜ ወንድ
ሞቹን የእስራኤልን ልጆች ለመጐብኘት

7፥2-3 ፦ ዘፍ. 12፥1 ። 7፥4 ፦ ዘፍ. 11፥31 ፤ 12፥4 ። 7፥5 ፦ ዘፍ. 12፥7 ፤ 13፥15 ፤ 15፥18 ፤ 17፥8 ።
7፥6-7 ፦ ዘፍ. 15፥13-14 ። 7፥7 ፦ ዘፀ. 3፥12 ። 7፥8 ፦ ዘፍ. 17፥10-14 ፤ 21፥2-4 ፤ 25፥26 ፤ 29፥31-35፥18 ።
7፥9 ፦ ዘፍ. 37፥11 ፤28 ፤ 39፥2 ፤21 ። 7፥10 ፦ ዘፍ. 41፥39-41 ። 7፥11 ፦ ዘፍ. 42፥1-2 ። 7፥13 ፦ ዘፍ. 45፥1 ፤16 ።
7፥14 ፦ ዘፍ. 45፥9-10 ፤17-18 ፤ 46፥27 ። 7፥15 ፦ ዘፍ. 46፥1-7 ፤ 49፥33 ።
7፥16 ፦ ዘፍ. 23፥3-16 ፤ 33፥19 ፤ 50፥7-13 ፤ ኢያሱ 24፥32 ። 7፥17-18 ፦ ዘፀ. 1፥7-8 ። 7፥19 ፦ ዘፀ. 1፥10-11 ፤22 ።
7፥20 ፦ ዘፀ. 2፥2 ። 7፥21 ፦ ዘፀ. 2፥3-10 ። 7፥23-29 ፦ ዘፀ. 2፥11-15 ።

እሰበ ። 24 ከወንድሞቹም አንዱ ፥ በአንድ ግብ
ጻዊ ሰው ሲበደልና ሲገፋ አይቶ ረዳው ፤ ለተገ
ፋውም በመበቀል ግብጻዊውን መታና ገደ
ለው ። 25 እግዚአብሔር በእርሱ አማካይነት ነፃ
እንደሚያወጣቸው ወገኖቹ የሚገነዘቡ መስ
ሎት ነበር ፤ እነርሱ ግን ይህን አልተገነዘቡም ።
26 በማግሥቱም ሁለት እስራኤላውያን እርስ
በርሳቸው ሲጣሉ አገኘና ሊገላግላቸው በመፈ
ለግ ‘እናንተ ሰዎች ፥ እናንተ ወንድማማቾች
ናችሁ ፤ ስለምን ትጣላላችሁ?’ አላቸው ። 27 ያ
ባልንጀራውን ይደበድብ የነበረው ሰው ሙሴን
ወዲያ ገፈተረና ፥ ‘አንተን በእኛ ላይ ገዥና
ፈራጅ ያደረገህ ማን ነው? 28 ትናንትና ግብጻዊ
ውን እንደገደልኸው እኔንም ልትገድለኝ ትፈል
ጋለህን?’ አለው ። 29 ሙሴ ይህን በሰማ ጊዜ ከግ
ብጽ አገር ሸሽቶ ወደ ምድያም አገር ሄደና
እዚያ ኖረ ፤ በዚያ ሁለት ልጆች ወለደ ።
30 “ሙሴ በዚያ አገር አርባ ዓመት ካሳለፈ
በኋላ ፥ በደብረ ሲና በረሓ በሚነድደው
የቍጥቋጦ ነበልባል ውስጥ የእግዚአብሔር
መልአክ ታየው ። 31 ሙሴ ይህን ባየ ጊዜ ተገ
ረመ ፤ ቀረብ ብሎም ሲመለከት እንዲህ የሚለ
ውን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰማ ፤ 32 ‘እኔ የአ
ባቶችህ አምላክ ነኝ ፤ የአብርሃም አምላክ ፤ የይ
ስሐቅ አምላክ ፥ የያዕቆብ አምላክ ነኝ ፤’
ሙሴም በፍርሃት ተንቀጠቀጠ ፤ ለመመልከትም
አልደፈረም ። 33 እግዚአብሔርም እንዲህ
አለው ፥ ‘የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ምድር
ስለሆነ ጫማህን አውልቅ ፤ 34 በግብጽ ያለውን
የሕዝቤን ጽኑ መከራ በእርግጥ አይቻለሁ ፤
የጭንቀት ጩኸታቸውንም ሰምቻለሁ ፤ ስለዚህ
ላድናቸው ወርጃለሁ ፤ አሁንም ና ፥ እኔ አንተን
ወደ ግብጽ እልክሃለሁ ።’
35 “የእስራኤል ሕዝብ ሙሴን ‘በእኛ ላይ
ገዥና ፈራጅ እንድትሆን ያደረገህ ማን ነው?’
በማለት ተቃውመውት ነበር ፤ ይሁን እንጂ እግ
ዚአብሔር ይህንኑ ሙሴን በቍጥቋጦው ውስጥ
በተገለጠለት መልአክ አማካይነት ገዥና ፈራጅ
አድርጎ ወደ እነርሱ ላከው ። 36 በግብጽና በቀይ
ባሕር ድንቆችንና ተአምራትን በማድረግ ሕዝ
ቡን እውጥቶ አርባ ዓመት የመራቸው ይህ
ሙሴ ነበር ። 37 ‘እግዚአብሔር አምላክ እኔን
እንዳስነሣኝ እንዲሁ ከወንድሞቻችሁ መካከል
ነቢይ ያስነሣላችኋል’ ብሎ ለእስራኤላውያን
የተናገረው ይኸው ሙሴ ነበር ። 38 በበረሓ ተሰ
ብስቦ ከነበረው ሕዝብ ጋርና ከሲና ተራራ ላይ
ከተናገረው መልአክ ጋር ፥ እንዲሁም ከአባቶቻ
ችን ጋር የነበረው እርሱ ነው ። የእግዚአብሔ
ርን የሕይወት ቃል ለእኛ ያስተላለፈልንም
ይኸው ሙሴ ነው ።
39 “አባቶቻችን ግን ተቃወሙት እንጂ አል
ታዘዙትም ፤ በልባቸውም ወደ ግብጽ ለመመ
ለስ አሰቡ ። 40 አሮንንም ‘ይህ ከግብጽ አገር
ያወጣን ሙሴ ምን እንደደረሰበት አናውቅምና
እፊት እፊታችን እየሄዱ የሚመሩንን አማልክት
ሥራልን’ አሉት ። 41 በዚያን ጊዜ በጥጃ ምስል
ጣዖት ሠርተው መሥዋዕት አቀረቡ ፤ በእጃቸ
ውም ሥራ ተደሰቱ ። 42 እግዚአብሔር ግን ተለ
ያቸው ። የሰማይንም ከዋክብት እንዲያመልኩ
አሳልፎ ሰጣቸው ፤ ይህም በነቢያት እንዲህ
ተብሎ እንደተጻፈ ነው ፤
‘እናንተ የእስራኤል ሰዎች ሆይ!
የታረደውን እንስሳና መሥዋዕትን
አርባ ዓመት ሙሉ በበረሓ
ያቀረባችሁት ለእኔ ነውን?
43 ይዛችሁ የሄዳችሁት የሞሎክን ድንኳንና
ሬፋን የሚባለውን የአምላካችሁን
ኮከብ ምስል ነበር ፤
እነርሱም በእጃችሁ ሠርታችሁ
ትሰግዱላቸው የነበሩ አማልክት
ናቸው ።
እኔም ከባቢሎን ወዲያ እንድትሰደዱ
አደርጋለሁ ።’
44 “አባቶቻችን በበረሓ እግዚአብሔር የሚ
መለክባት ድንኳን ነበረቻቸው ፤ ይህችንም
ድንኳን እግዚአብሔር በነገረውና ባሳየው መሠ
ረት የሠራት ሙሴ ነበር ። 45 እግዚአብሔር
ከፊታቸው ያባረረላቸውን የአረማውያንን አገር
በወረሱ ጊዜ አባቶቻችን ይህችን የተቀበሉአትን
ድንኳን ከኢያሱ ጋር ወደዚያ አገቡአት ፤ እስከ
ዳዊት ዘመንም ድረስ እዚያ ኖረች ። 46 ዳዊ
ትም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አግኝቶ በያዕ
ቆብ ነገድ መካከል ለእግዚአብሔር ማደሪያ
የሚሆን ቤት ለመሥራት በጸሎት ለመነ ።
47 ነገር ግን ለእግዚአብሔር ቤት የሠራው ሰሎ
ሞን ነው ።
48 “ሆኖም ልዑል እግዚአብሔር በሰው እጅ
በተሠራ ቤት ውስጥ አይኖርም ፤ ይህም ነቢዩ
እንዲህ ሲል እንደጻፈው ነው ፤
49 ‘ሰማይ ዙፋኔ ነው ፤
ምድርም የእግሬ ማሳረፊያ ናት ፤
ታዲያ ለእኔ ምን ዐይነት ቤት
ትሠሩልኛላችሁ?
የማርፍበትስ ቦታ ምን ዐይነት ነው?

7፥29 ፦ ዘጸ. 18፥3-4 ። 7፥30-34 ፦ ዘጸ. 2፥14 ። 7፥36 ፦ ዘጸ. 7፥5 ፤ 14፥21 ፤ ዘኍ. 14፥33 ። 7፥37 ፦ ዘዳ. 18፥15 ፤ 18 ።
7፥38 ፦ ዘጸ. 19፥1-20፥17 ፤ ዘዳ. 5፥1-33 ። 7፥40 ፦ ዘጸ. 32፥1 ። 7፥41 ፦ ዘጸ. 32፥2-6 ።
7፥42-43 ፦ አሞጽ 5፥25-27 ። 7፥44 ፦ ዘጸ. 25፥9 ፤ 40 ። 7፥45 ፦ ኢያሱ 3፥14-17 ። 7፥46 ፦ 2ሳሙ. 7፥1-16 ፤
1ዜ.መ. 17፥1-14 ። 7፥47 ፦ 1ነገ. 6፥1-38 ፤ 2ዜ.መ. 3፥1-17 ። 7፥49-50 ፦ ኢሳ. 66፥1-2 ።



50 ይህን ሁሉ እኔ በእጄ የሠራሁት
አይደለምን?’ ይላል
እግዚአብሔር ።
51 “እናንተ አንገታችሁ የደነደነ እልኸ
ኞች! ልባችሁ የተደፈነ ፥ ጆሮአችሁም የማይ
ሰማ! እናንተም ልክ እንዳባቶቻችሁ ሁልጊዜ
መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ ። 52 ከነቢያት
መካከል አባቶቻችሁ ያላሳደዱት ማን አለ? እነ
ርሱ የጻድቁን መምጣት አስቀድመው የተናገሩ
ትን ገደሉአቸው ፤ እናንተም አሁን ይህን ጻድ
ቁን አሳልፋችሁ በመስጠት ገደላችሁት ።
53 እናንተ በመላእክት አማካይነት ሕግን ተቀብ
ላችሁ ነበር ፤ ነገር ግን አልጠበቃችሁትም ።”

### እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ሞተ

54 የሸንጎ አባሎች ይህን በሰሙ ጊዜ ተና
ደዱ ፤ በእስጢፋኖስ ላይም ብቍጣ ጥርሳቸውን
አፋጩ ። 55 እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ተሞ
ልቶ ወደ ሰማይ ትኵር ብሎ ሲመለከት ፥ የእግ
ዚአብሔርን ክብር አየ ፤ ኢየሱስንም በእግዚአብ
ሔር ቀኝ ቆሞ አየው ፤ ስለዚህ “እነሆ ሰማይ
ተከፍቶ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ
አያለሁ” አለ ።
57 በዚህ ጊዜ እነርሱ በታላቅ ድምፅ ጮኹ ፤
ጆሮአቸውንም ደፍነው በአንድነት ወደ እርሱ
ሮጡ ። 58 ከከተማ አወጡትና በድንጋይ ወገ
ሩት ፤ ምስክሮችም ልብሳቸውን ወስደው
ሳውል የሚባል አንድ ጕልማሳ እንዲጠብቅላ
ቸው በእግሩ ሥር አስቀመጡ ። 59 በድንጋይ
ሲወግሩት ሳሉ እስጢፋኖስ “ጌታ ኢየሱስ
ሆይ! ነፍሴን ተቀበል!” ብሎ ጸለየ ። 60 ተንበ
ርክኮም “ጌታ ሆይ! ይህን በደል አትቍጠርባ
ቸው” ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ ። ይህንንም
ብሎ ሞተ ።

## ምዕራፍ 8

### ሳውል ቤተ ክርስቲያንን አሳደደ

1 ሳውልም በእስጢፋኖስ መገደል ተስማምቶ
ነበር ። እስጢፋኖስ በሞተበት ቀን በኢየሩሳ
ሌም በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ
ስደት ተነሣ ፤ ከሐዋርያት በቀር አማኞች ሁሉ
ወደ ይሁዳ አገርና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበ
ተኑ ። 2 አንዳንድ መንፈሳውያን ሰዎች እስጢፋ
ኖስን ቀበሩት ፤ በታላቅ ድምፅም እየጮኹ አለ
ቀሱለት ።
3 ሳውል ግን ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት
ይጥር ነበር ፤ ከቤት ወደ ቤትም እየገባ ወንዶ
ችንና ሴቶችን አማኞችን እየጐተተ ያወጣ ነበር ፤
ወደ እስር ቤትም ያስገባቸው ነበር ።

### ወንጌል በሰማርያ ተሰበከ

4 የተበተኑትም አማኞች በሄዱበት ስፍራ
ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምሩ ነበር ።
5 ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ሄዶ ሰዎቹን
ስለ መሲሕ አስተማራቸው ። 6 ሰዎቹም የፊልጶ
ስን ቃል በሰሙ ጊዜ የሚያደርጋቸውንም ተአ
ምራት ባዩ ጊዜ በአንድነት በጥንቃቄ ያዳም
ጡት ነበር ። 7 ርኩሳን መናፍስትም በታላቅ
ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበር ፤
ብዙ ሽባዎችና አንካሶችም ይድኑ ነበር ። 8 ስለ
ዚህ በዚያች ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ ።
9 በዚያች ከተማ ሲሞን የሚባል አንድ ሰው
ነበረ ፤ ይህ ሰው በከተማይቱ ውስጥ አስማት እያ
ደረገ የሰማርያን ሕዝብ ሲያስደንቅ ቆይቶአል ፤
“እኔ ትልቅ ሰው ነኝ!” እያለም ይናገር ነበር ።
10 ሰዎች ሁሉ ትንሹም ትልቁም “ይህ ሰው
ታላቅ ተብሎ የሚጠራው የእግዚአብሔር ኀይል
ነው!” እያሉ ያዳምጡት ነበር ። 11 ምክንያቱም
ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በአስማት ያስደንቃቸው ስለነ
በረ ነው ። 12 ነገር ግን ፊልጶስ ስለ እግዚአብሔር
መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተናገረ
ውን መልካም ዜና በሰሙ ጊዜ ወንዶችም ሴቶ
ችም አምነው ተጠመቁ ። 13 ሲሞን እንኳን ሳይ
ቀር አምኖ ተጠመቀና ከፊልጶስ ጋር ተባባሪ
ሆነ ፤ የሚደረጉትንም ድንቅ ነገሮችና ታላላቅ
ተአምራት በማየቱ ይገረም ነበር ።
14 በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማ
ርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መቀበላቸውን
በሰሙ ጊዜ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ወደ ሰማርያ
ላኩአቸው ። 15 ስለዚህ የሰማርያ ሰዎች መንፈስ
ቅዱስን እንዲቀበሉ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሄደው
ጸለዩላቸው ። 16 ምክንያቱም የሰማርያ ሰዎች
በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠምቀው ነበር እንጂ
መንፈስ ቅዱስ ገና በአንዳቸውም ላይ አልወረ
ደም ነበር ። 17 ስለዚህ ጴጥሮስና ዮሐንስ እጆቻ
ቸውን በጫኑባቸው ጊዜ ሰዎቹ መንፈስ ቅዱ
ስን ተቀበሉ ።
18 ሐዋርያት እጆቻቸውን ሲጭኑባቸው መን
ፈስ ቅዱስ ለሰዎቹ መሰጠቱን ሲሞን ባየ ጊዜ
ገንዘብ አመጣላቸውና ፥ 19 “እኔም እጄን የም
ጭንበት ሰው መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ይህን
ሥልጣን ስጡኝ” አለ ።
20 ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው ፥ “የእግዚአብ
ሔርን ስጦታ በገንዘብ ለማግኘት በመፈለግህ ገን
ዘብህ ካንተ ጋር ይጥፋ! 21 ልብህ በእግዚአብ
ሔር ፊት ቅን ስላልሆነ አንተ ከዚህ ነገር
ክፍል ወይም ዕጣ የለህም ። 22 እንግዲህ በዚህ
በክፋትህ ተጸጸትህ ንስሐ ግባ ፤ ምናልባት የል
ብህን አሳብ ይቅር ይልልህ እንደሆን እግዚአብ
ሔርን ለምን ። 23 ምክንያቱም አንተ በመራራ

7፥51 ፦ ኢሳ. 63፥10 ። 8፥3 ፦ ሐ.ሥ. 22፥4-5 ፤ 26፥9-11 ።

ቅንአት እንደተሞላህና የኃጢአት እስረኛ እንደ
ሆንህ አያለሁ ።”
24 ሲሞንም “አሁን ከተናገራችሁት አንዳች
እንኳን እንዳይደርስብኝ እናንተ ራሳችሁ ወደ
ልዑል እግዚአብሔር ጸልዩልኝ” አላቸው ።
25 ጴጥሮስና ዮሐንስ ከመሰከሩና የጌታንም
ቃል ከተናገሩ በኋላ በብዙ የሰማርያ መንደሮች
መልካሙን ዜና እያበሠሩ ወደ ኢየሩሳሌም
ተመለሱ ።

ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ አጠመቀ

26 የእግዚአብሔር መልአክ ፊልጶስን “ተን
ሥና ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ በሚወስደው መን
ገድ ወደ ደቡብ ሂድ” አለው ፤ ያ መንገድ የበ
ረሓ መንገድ ነበር ። 27 እርሱም ተነሥቶ ሄደ ።
እነሆ አንድ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ለእግዚአብ
ሔር ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ነበር ፤ ይህ
ሰው ሕንደኬ ለተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት
ባለሟልና የገንዘብዋ ሁሉ አዛዥ ነበረ ።
28 እርሱ ወደ አገሩ ሲመለስ ፥ በሠረገላ ተቀ
ምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ
ነበር ። 29 በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን
“ሂድ ወደዚያ ሠረገላ ቅረብ” አለው ። 30 ስለ
ዚህ ፊልጶስ ወደዚያ ሮጦ ሄደና ኢትዮጵያዊው
የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰምቶ
“የምታነበው ትርጒሙ ይገባሃልን?” አለው ።
31 ኢትዮጵያዊውም “የሚያስረዳኝ ሰው ሳይኖር
እንዴት ሊገባኝ ይችላል?” አለና ፥ ፊልጶስን
“ወደ ሠረገላው ውጣና ከእኔ ጋር ተቀመጥ”
አለው ። 32 ጃንደረባው ያነበው የነበረው የመጽ
ሐፍ ክፍል ይህ ነበረ ፥

“ለመታረድ እንደሚነዳ በግ ነበረ ፤
ሲሸልቱት ዝም እንደሚል ጥቦት
እርሱም ለመናገር አፉን አልከፈተም ።
33 እርሱ ተዋረደ ፤ ቅን ፍርድም
አልተሰጠውም ፤
ሕይወቱም ከምድር ተወግዶአልና
ስለ ትውልዱ ማን ሊናገር ይችላል?”

34 ጃንደረባውም ፊልጶስን “ነቢዩ ይህን የተ
ናገረው ስለማን ነው? ስለ ራሱ ነውን ወይስ
ስለሌላ? እባክህን ንገረኝ” አለው ። 35 ፊልጶስም
ከዚህ መጽሐፍ ክፍል ጀምሮ ስለ ኢየሱስ መል
ካሙን ዜና አበሠረው ። 36 ሲሄዱም ውሃ ወዳለ
በት ቦታ ደረሱ ፤ ጃንደረባውም “እነሆ እዚህ
ውሃ አለ ፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ነገር
ምንድን ነው?” አለ ።
[37 ፊልጶስም “በሙሉ ልብህ ካመንህ መጠ
መቅ ትችላለህ” አለው ። ጃንደረባውም “ኢየ
ሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን
አምናለሁ” አለ ።][2*]
38 ጃንደረባው ሠረገላው እንዲቆም አዘዘ ፤
ሁለቱም ወደ ውሃው ወረዱና ፊልጶስ ጃንደረባ
ውን አጠመቀው ። 39 ከውሃው ከወጡ በኋላ የእ
ግዚአብሔር መንፈስ ፊልጶስን ወሰደው ፤ ጃንደ
ረባውም ዳግመኛ አላየውም ፤ ደስ እያለውም
ጒዞውን ቀጠለ ። 40 ፊልጶስ ግን በአዞጦስ
ተገኘ ፤ ወደ ቂሳርያም እስከ መጣ ድረስ በየከ
ተማዎቹ እየሄደ መልካሙን ዜና ያበሥር
ነበር ።

## ምዕራፍ 9

ሳውል በክርስቶስ አመነ
(ሐ.ሥ. 22፥6-16፤ 26፥12-18)

1 በዚያን ጊዜ ሳውል የጌታን ደቀ መዛሙ
ርት ለመግደል ገና እየዛተ ወደ ሊቀ ካህናቱ
ሄደ ። 2 የጌታንም መንገድ የሚከተሉትን ሰዎች
ወንዶችንም ሴቶችንም ሲያገኝ እያሰረ ወደ ኢየ
ሩሳሌም ለማምጣት የሚያስችል ደብዳቤ ለደማ
ስቆ ምኵራቦች ተጽፎ እንዲሰጠው ሊቀ ካህና
ቱን ጠየቀ ።
3 ሲሄድም ወደ ደማስቆ በቀረበ ጊዜ በእርሱ
ዙሪያ በድንገት ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ ።
4 በዚያን ጊዜ በምድር ላይ ወደቀ ፤ “ሳውል!
ሳውል! ለምን ታሳድደኛለህ?” የሚል ድምፅ
ሰማ ።
5 ሳውልም “ጌታ ሆይ! አንተ ማን ነህ?”
አለ ፤ እርሱም “እኔ አንተ የምታሳድደኝ ኢየ
ሱስ ነኝ ፤[3*] 6 አሁን ግን ተነሥና ወደ ከተማ
ግባ ፤ ልታደርገው የሚገባህም እዚያ ይነገር
ሃል” አለው ።
7 ከሳውል ጋር ይሄዱ የነበሩ ሰዎች ድምፅ
እየሰሙ ማንንም ባለማየታቸው የሚናገሩትን
አጥተው ዝም ብለው ቆሙ ። 8 ሳውልም ከወደ
ቀበት መሬት ተነሣ ፤ ዐይኖቹን በገለጠ ጊዜ
ምንም ማየት አልቻለም ፤ ስለዚህ ሰዎቹ እጁን
ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ ወሰዱት ። 9 ሦስት
ቀን ሙሉ ምንም ማየት ሳይችል ፥ ሳይበላና
ሳይጠጣም ቈየ ።
10 በደማስቆ ሐናንያ የሚባል አንድ ደቀ
መዝሙር ነበር ። ጌታ በራእይ “ሐናንያ!”
ብሎ ጠራው ፤ እርሱም “እነሆኝ ጌታ ሆይ!”
አለ ።
11 ጌታም እንዲህ አለው ፥ “ቀጥተኛ ወደም
ትባለው መንገድ ሂድ ፤ እዚያ በይሁዳ ቤት
ሳውል የሚባለውን የጠርሴስ ሰው ፈልግ ፥
እርሱ አሁን በጸሎት ላይ ነው ።” 12 ሳውልም
ዐይኖቹ እንደገና ማየት እንዲችሉ ሐናንያ የተ
ባለ ሰው ወደ እርሱ ገብቶ እጁን ሲጭንበት
በራእይ አየ ።
13 ሐናንያ ግን እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “ጌታ
ሆይ! ይህ ሰው በኢየሩሳሌም በሚኖሩ ቅዱሳን
ላይ ብዙ ክፉ ነገር ማድረጉን ከብዙዎች ሰም
ቻለሁ ። 14 እዚህም ስምህን የሚጠሩትን ሁሉ
ለማሰር ከካህናት አለቆች ሥልጣን ተቀብሎ
አል ።”
15 ጌታም ሐናንያን እንዲህ አለው ፥ “እርሱ
ስሜን ለአረማውያንና ለነገሥታት ፥ ለእስራኤል
ሰዎችም የሚያሳውቅ የእኔ ምርጥ መሣሪያ ስለ
ሆነ ወደ እርሱ ሂድ ፤ 16 ስለ እኔ ምን ያህል
ብዙ መከራ እንደሚቀበል እገልጥለታለሁ ።”
17 ስለዚህ ሐናንያ ወደዚያ ሄዶ ወደ ቤት
ገባ ፤ እጁንም በሳውል ላይ ጭኖ “ወንድሜ
ሳውል ሆይ! ወደዚህ ስትመጣ ሳለ በመንገድ
የተገለጠልህ ጌታ ኢየሱስ እንደገና ማየት እንድ
ትችልና መንፈስ ቅዱስም እንዲሞላብህ ወደ
አንተ ልኮኛል” አለው ። 18 ወዲያውኑ ቅርፊት
የሚመስል ነገር ከዐይኑ ወደቀና ማየት ቻለ ፤
ተነሥቶም ተጠመቀ ። 19 መብልም በላና
በረታ ፤ በደማስቆ ከነበሩት ደቀ መዛሙርት ጋር
ለጥቂት ቀኖች ቈየ ።

ሳውል በደማስቆ

20 ወዲያውም ሳውል በደማስቆ “ኢየሱስ
የእግዚአብሔር ልጅ ነው” እያለ በየምኵራቡ
ማስተማር ጀመረ ።
21 የሰሙትም ሁሉ “ይህ ሰው በኢየሩሳሌም
ይህን ስም የሚጠሩትን ሁሉ በብርቱ ያሳድድ
የነበረ አይደለምን? ወደዚህስ የመጣው እነር
ሱን እያሰረ ወደ ካህናት አለቆች ለመውሰድ
አይደለምን?” በማለት ይደነቁ ነበር ።
22 ሳውል ግን ይበልጥ እየበረታ ሄደ ፤ ኢየ
ሱስ መሲሕ መሆኑን በማስረዳት በደማስቆ
ይኖሩ የነበሩትን አይሁዳውያን መልስ ያሳጣ
ቸው ነበር ።
23 ከብዙ ቀን በኋላ አይሁዳውያን ሳውልን
ለመግደል ተማከሩ ፤ 24 እርሱ ግን ሊገድሉት
መማከራቸውን ዐወቀ ፤ እነርሱም እርሱን ለመ
ግደል ቀንና ሌሊት በሮቹን ይጠብቁ ነበር ።
25 ነገር ግን በሌሊት የራሱ ደቀ መዛሙርት
ሳውልን በቅርጫት አድርገው በግንብ ላይ አሳለ
ፉትና ወደታች አወረዱት ።

ሳውል በኢየሩሳሌም

26 ሳውል ወደ ኢየሩሳሌም በሄደ ጊዜ እዚያ
ካሉት ደቀ መዛሙርት ጋር ለመደባለቅ ሞከረ ፤
እነርሱ ግን የእርሱ በክርስቶስ ማመን እውነት
ስላልመሰላቸው ሁሉም ፈሩት ። 27 በርናባስ
ግን ሳውልን ወደ ሐዋርያት አቀረበውና በመን
ገድ ሳለ ጌታ እንዴት እንደተገለጠለትና እንዳነ
ጋገረው ፥ በደማስቆም በኢየሱስ ስም እንዴት
በድፍረት እንዳስተማረ ነገራቸው ። 28 ስለዚህ
ሳውል ከእነርሱ ጋር ሆኖ በኢየሩሳሌም ይዘዋ
ወር ነበር ። በጌታም ስም በድፍረት ያስተምር
ነበር ፤ 29 የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑት አይሁዳ
ውያን ጋር እየተናገረ ይከራከር ነበር ። እነርሱ
ግን ሊገድሉት ዐቅደው ነበር ። 30 ወንድሞች
ይህን ባወቁ ጊዜ ወደ ቂሳርያ ወሰዱት ፤ ከዚ
ያም ወደ ጠርሴስ እንዲሄድ አደረጉ ።
31 በይሁዳ አገር ፥ በገሊላና በሰማርያ አገር
ሁሉ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ሰላም አገኘች ፤
በረታችም ፤ ጌታን እያከበረችና በመንፈስ እየተ
ጽናናች በቊጥር አደገች ።

ጴጥሮስ በልዳና በኢዮጴ

32 ጴጥሮስ በየአገሩ ሲዘዋወር ሳለ ፥ በልዳ
ወደሚኖሩትም ቅዱሳን ሄደ ። 33 እዚያም ስም
ንት ዓመታት ሙሉ በአልጋ ላይ የተኛ ኤንያ
የሚባለውን ሽባ አገኘ ። 34 ጴጥሮስም “ኤንያ
ሆይ! ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃል ፤ ተነሥና
አልጋህን አንጥፍ” አለው ፤ እርሱም ወዲያውኑ
ተነሣ ። 35 የልዳና የሳሮናም ነዋሪዎች ሁሉ እር
ሱን አይተው በጌታ አመኑ ።
36 በኢዮጴም ጣቢታ የምትባል አንዲት
አማኝ ነበረች ፤ የስሟም ትርጒም በግሪክኛ
ዶርቃ ወይም ሚዳቋ ማለት ነው ፤ እርስዋ
መልካም ነገር ማድረግና ለድኾች መለገስ የም
ታዘወትር ሴት ነበረች ፤ 37 በዚያን ጊዜ እርስዋ
ታመመችና ሞተች ፤ አጥበውም በሰገነት ላይ
ባለው ክፍል ውስጥ አኖርዋት ። 38 ልዳ ለኢ
ዮጴ ቅርብ ስለ ነበረች በኢዮጴ ያሉት ደቀ
መዛሙርት ጴጥሮስ በልዳ መኖሩን ሰምተው
“ሳትዘገይ በቶሎ ናልን” ብለው የሚጠሩትን
ሁለት ሰዎች ላኩበት ። 39 ስለዚህ ጴጥሮስ ተነ
ሥቶ ከመልእክተኞቹ ጋር መጣ ፤ በደረሰም ጊዜ
በሰገነቱ ላይ ወዳለው ክፍል ወሰዱት ፤ መበለ
ቶቹ ሁሉ በዙሪያው ቆመው እያለቀሱ ዶርቃ
ከእነርሱ ጋር በሕይወት ሳለች የሠራቻቸውን
ቀሚሶችና ልብሶች ያሳዩት ነበር ፤ 40 ጴጥሮስ
ግን ሁሉንም ወደ ውጪ አስወጣና ተንበርክኮ
ጸለየ ፤ ወደ አስከሬኑም መለስ አለና “ጣቢታ
ተነሺ” አለ ፤ እርስዋም ዐይኖችዋን ከፈተች ፤
ጴጥሮስንም አየች ፤ ተነሥታም ቁጭ አለች ።
41 እርሱም እጁን ዘርግቶ ያዘና አስነሣት ፤ መበለ
ቶችንና ሌሎችንም አማኞች ጠርቶ በሕይወት
በፊታቸው አቀረባት ። 42 ይህም ነገር በኢዮጴ
ሁሉ ታወቀ ፤ ብዙ ሰዎችም በጌታ አመኑ ።
43 ጴጥሮስም ስምዖን ከሚባለው አንድ ቍርበት
ፋቂ ጋር ለብዙ ቀኖች በኢዮጴ ተቀመጠ ።

---

[2*] 8፥37 አንዳንድ ቅጂዎች ቍ. 37 ይጨምራሉ ፤ የጥንት ቅጂዎች ግን አይጨምሩም ። [3*] 9፥5 አንዳንድ ትርጒሞች “በሰይፍ ስለት ላይ ብትቆም ራስህን ትጐዳለህ” ይላሉ ፥ ደግሞም “ሳውልም እየተንቀጠቀጠ በፍርሃት በመደነቅ ‘ጌታ ሆይ ! ምን እንዳደርግ ትወድዳለህ?’ አለው” ይላሉ ። ይህም በሥ. 22፥10 ፤ 26፥14 ላይ ተጽፎ ይገኛል ።
8፥32-33 ፦ ኢሳ. 53፥7-8 ።

9፥23-25 ፦ 2ቆሮ. 11፥32-33 ።

## ምዕራፍ 10
### ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ

1በቂሳርያ የሚኖር ቆርኔሌዎስ የሚባል
አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም "የኢጣሊያ ጓድ"
በሚባለው ክፍለ ጦር ውስጥ የመቶ አለቃ
ነበረ፤ 2እርሱ ከቤተ ሰቡ ሁሉ ጋር በአይሁድ
ሥርዓት እግዚአብሔርን የሚያመልክ መንፈሳዊ
ሰው ነበረ፤ ለአይሁድም ሕዝብ ብዙ ችሮታ
ያደርግ ነበር፤ ወደ እግዚአብሔርም ዘወትር
ይጸልይ ነበር። 3አንድ ቀን ዘጠኝ ሰዓት ገደማ
ላይ የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲገባና
"ቆርኔሌዎስ!" ብሎ ሲጠራው በራእይ በግልጥ
ታየው።
4ትኵር ብሎ ወደ መልአኩ ተመለከተና
በመደንገጥ "ጌታ ሆይ! ምንድን ነው?"
አለ።
መልአኩም እንዲህ አለው፥ "ጸሎትህና
ለድኾች የምታደርገው ችሮታህ በእግዚአብሔር
ዘንድ ታስቦልሃል፤ 5አሁንም ሰዎችን ወደ
ኢዮጴ ላክና ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንን አስ
ጠራ፤ 6እርሱ አሁን በባሕር አጠገብ በሚገ
ኘው በቁርበት ፋቂው በስምዖን ቤት በእንግድ
ነት ተቀምጦአል።" 7ይህን የነገረው መልአክ
ተለይቶት በሄደ ጊዜ፥ ቆርኔሌዎስ ከአገልጋ
ዮቹ ሁለቱንና የእርሱ ክፍል ከሆኑት ወታደ
ሮች መንፈሳዊ የሆነውን አንዱን ጠራና፥
8ሁሉንም ነገር ከነገራቸው በኋላ ወደ ኢዮጴ
ላካቸው።
9በማግሥቱ እነርሱ ሄደው ወደ ከተማው
ሲቀርቡ፥ ስድስት ሰዓት ገደማ ጴጥሮስ ሊጸ
ልይ ወደነበረበት ቤት ሰገነት ላይ ወጣ።
10በዚያን ጊዜ ራበውና መብላት ፈለገ፤ ምሳ
በመዘጋጀት ላይ እንዳለም ራእይ አየ። 11ያየ
ውም ራእይ ሰማይ ተከፍቶ በአራት ማእዘን
የተያዘ ትልቅ የመጋረጃ ጨርቅ የሚመስል
ነገር ወደ ምድር ሲወርድ ነው። 12በዚያም
ላይ፥ ልዩ ልዩ እንስሳት፥ በልባቸው የሚሳቡ
ፍጥረቶችና በሰማይ የሚበርሩ ወፎች ነበሩ
በት። 13በዚያን ጊዜ "ጴጥሮስ ሆይ! ተነሥና
እያረድህ ብላ" የሚል ድምፅ ወደ እርሱ
መጣ።
14ጴጥሮስ ግን "ጌታ ሆይ፥ አይሆንም! እኔ
ያልተቀደሰ ወይም ርኩስ ነገር በልቼ አላው
ቅም" አለ።
15ደግሞም "እግዚአብሔር ንጹሕ ያደረገ
ውን አንተ ርኩስ ነው ማለት አትችልም"
የሚል ድምፅ እንደገና ወደ እርሱ መጣ።
16ይህም ሦስት ጊዜ ከሆነ በኋላ ያ ጨርቅ የሚ
መስል ነገር ወዲያውኑ ወደ ሰማይ ተወሰደ።
17ጴጥሮስ የራእዩ ፍች "ምን ይሆን?"
እያለ በአሳቡ ሲጨነቅ፥ ቆርኔሌዎስ የላካቸው
ሰዎች በጥያቄ የስምዖንን ቤት አግኝተው በበር
ቆመው ነበር፤ 18ተጣርተውም "ጴጥሮስ የተባ
ለው ስምዖን በእንግድነት የሚገኘው እዚህ
ነውን?" ብለው ጠየቁ።
19ጴጥሮስ የራእዩን ነገር በማሰላሰል ላይ
ሳለ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ አለው፥ "እነሆ
ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃል፤ 20ተነሥና ውረድ፤
የላክኋቸው እኔ ስለሆንሁ ሳታመነታ ከእነርሱ
ጋር ሂድ።" 21ጴጥሮስም ወርዶ ወደ ሰዎቹ
ሄደና "እነሆ የምትፈልጉት ሰው እኔ ነኝ፤
የመጣችሁበት ምክንያት ምንድን ነው?" አላ
ቸው። 22እነርሱም "እኛ የመጣነው ከመቶ
አለቃው ከቆርኔሌዎስ ዘንድ ነው፤ እርሱ የአይ
ሁድ ሕዝብ ሁሉ የሚያከብረው በአይሁድ
ሥርዓት እግዚአብሔርን የሚያመልክ ደግ ሰው
ነው። አንተን ወደ ቤቱ አስጠርቶ የምትለውን
እንዲሰማ ቅዱስ መልአክ ተገልጦለታል"
አሉት። 23ጴጥሮስም ወደ ቤት አስገባቸውና
ለምሳ አሳደራቸው።
በማግሥቱም ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር ሄደ፤
በኢዮጴ ከነበሩት ወንድሞች አንዳንዶቹም አብ
ረውት ሄዱ። 24በነጋታውም ወደ ቂሳርያ
ደረሱ፤ ቆርኔሌዎስም ዘመዶቹንና የቅርብ ወዳ
ጆቹን ጠርቶ እነጴጥሮስን ይጠባበቅ ነበር።
25ጴጥሮስ ወደ ቤት ሲገባ ቆርኔሌዎስ ወደ
እርሱ ቀረበና በእግሩ ሥር ወድቆ ሰገደለት።
26ጴጥሮስ ግን "ተነሥ! እኔ እኮ እንደ አንተ
ሰው ነኝ!" ብሎ አስነሣው።
27እያነጋገረውም ወደ ውስጥ ሲገባ ብዙ
ሰዎች ተሰብስበው አገኘ። 28እንዲህም አላ
ቸው፥ "አይሁዳዊ ከአረማዊ ጋር ለመተባበርና
ወደ ቤቱም ለመግባት በሃይማኖታችን ሕግ እን
ደማይፈቀድ እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፤
ነገር ግን ማንንም ያልተቀደሰ ወይም ርኩስ እን
ዳልል እግዚአብሔር ገልጦልኛል። 29ስለዚህ
በተላከብኝ ጊዜ ያለ አንዳች ማመንታት
መጣሁ፤ እንግዲህ ለምን እንደጠራችሁኝ
ማወቅ እፈልጋለሁ።"
30ቆርኔሌዎስም እንዲህ አለ፥ "የዛሬ አራት
ቀን ልክ በዚህ ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት በቤቴ እጸ
ልይ ነበር፤ እነሆ በድንገት አንድ የሚያንጸባ
ርቅ ልብስ የለበሰ ሰው በፊቴ ቆመ፤ 31እንዲ
ህም አለኝ፥ 'ቆርኔሌዎስ ሆይ! እግዚአብሔር
ጸሎትህን ሰምቶአል፤ ለድኾች የምታደርገው
ንም ችሮታ ተቀብሎልሃል፤ 32እንግዲህ ወደ
ኢዮጴ መልእክተኛ ላክና ጴጥሮስ የተባለውን
ስምዖንን አስጠራ፤ እርሱ አሁን በባሕር አጠ
ገብ በሚገኘው በቁርበት ፋቂው በስምዖን ቤት
በእንግድነት ተቀምጦአል።' 33ስለዚህ ወዲያ
ውኑ መልእክተኞች ወደ አንተ ላክሁ፤ አን
ተም በመምጣትህ መልካም አድርገሃል፤ እንግ
ዲህ እግዚአብሔር እንድትናገር ያዘዘህን ሁሉ
ለመስማት እኛ ሁላችን በእግዚአብሔር ፊት
እዚህ ተሰብስበናል።"



### የጴጥሮስ ንግግር

34ጴጥሮስ እንዲህ ሲል መናገር ጀመረ፥
"በእውነት እግዚአብሔር ሰውን ከሰው እንደማ
ያበላልጥና እንደማያዳላ አስተዋልሁ፤ 35የማን
ኛውም አገር ሰው ቢሆን እግዚአብሔርን የሚ
ፈራና እውነት የሆነውን ነገር የሚያደርግ
ከሆነ፥ እግዚአብሔር ይቀበለዋል። 36እግዚአብ
ሔር ለእስራኤል ሕዝብ ቃሉን መላኩ የታወቀ
ነው፤ የሰላም ምሥራች በኢየሱስ ክርስቶስ የመ
ጣውም ለእነርሱ ነው፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስ
ቶስ የሁሉም ጌታ ነው። 37ዮሐንስ ስለ ጥም
ቀት ከሰበከበት ጊዜ ጀምሮ ከገሊላ አንሥቶ በይ
ሁዳ አገር ሁሉ የሆነውን ነገር ታውቃላችሁ።
38"ደግሞም እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየ
ሱስን በመንፈስ ቅዱስ እንደቀባውና ኀይልም
እንደሰጠው ታውቃላችሁ፤ እግዚአብሔርም
ከእርሱ ጋር ስለ ነበረ እርሱ መልካም ነገርን
እያደረገና በዲያብሎስ የተያዙትን ሁሉ እየፈ
ወሰ ተዘዋወረ።
39"በይሁዳ ገጠርና በኢየሩሳሌም ከተማ፥
እርሱ ስላደረገው ነገር ሁሉ እኛ ምስክሮች
ነን፤ እርሱን በእንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት።
40ነገር ግን እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን
ከሞት አስነሣውና እንዲገለጥ አደረገው።
41የተገለጠውም አስቀድሞ በእግዚአብሔር ለተ
መረጡት ምስክሮች ነው እንጂ ለሕዝቡ ሁሉ
አይደለም፤ እርሱ ከሞት ከተነሣ በኋላ እኛ ከእ
ርሱ ጋር አብረን የበላንና የጠጣን ምስክሮቹ
ነን፤ 42ይህን ነገር ለሕዝቡ እንድናበሥር
እርሱ በሕያዋንና በሙታን ላይ እንዲፈርድ፥
በእግዚአብሔር የተወሰነ መሆኑን እንድንመሰ
ክር አዞናል። 43በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ
የኃጢአት ይቅርታ እንደሚያገኝ ነቢያት ሁሉ
ይመሰክሩለታል።"

### አረማውያን አምነው መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ

44ጴጥሮስ ይህን በሚናገርበት ጊዜ ቃሉን
በሰሙት ሰዎች ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ
ወረደ። 45ከጴጥሮስ ጋር የመጡት አይሁዳው
ያን አማኞች እግዚአብሔር ለአረማውያንም
መንፈስ ቅዱስን እንደሰጣቸው ባዩ ጊዜ ተደ
ነቁ። 46ለአረማውያን መንፈስ ቅዱስ እንደተ
ሰጠ ያወቁትም፥ አረማውያን በሌሎች ቋንቋ
ዎች ሲናገሩና እግዚአብሔርን በምስጋና ሲያከ
ብሩ በመስማታቸው ነው። በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ
47"እነዚህ ሰዎች እንደ እኛ መንፈስ ቅዱስን
ተቀብለዋል፤ ታዲያ በውሃ እንዳይጠመቁ ማን
ይከለክላቸዋል?" ሲል ተናገረ። 48ስለዚህ በኢ
የሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ አዘዘ፤ ከዚህ
በኋላ ጴጥሮስ ከእነርሱ ጋር ለጥቂት ቀኖች እን
ዲቆይ ለመኑት።

## ምዕራፍ 11
### ጴጥሮስ ከአረማውያን ወገን ወዳመኑ ሰዎች ቤት ስለምን እንደገባ አስረዳ

1አረማውያን የእግዚአብሔርን ቃል መቀበላ
ቸውን በይሁዳ አገር የሚገኙ ሐዋርያትና ወን
ድሞች ሰሙ። 2ጴጥሮስ ወደ ኢየሩሳሌም ተመ
ልሶ በሄደ ጊዜ በግዝረት አስፈላጊነት የሚያ
ምኑ አይሁዳውያን አማኞች፥ 3"ስለምን ወዳል
ተገረዙ ሰዎች ቤት ገብተህ ከእነርሱ ጋር
በላህ?" በማለት ወቀሱት። 4ጴጥሮስ ግን እን
ዲህ ሲል ሁሉንም ነገር በየተራ ማስረዳት
ጀመረ።
5"እኔ በኢዮጴ ከተማ በጸሎት ላይ ሳለሁ
በተመስጦ ራእይ አየሁ፤ ያየሁትም ትልቅ የመ
ጋረጃ ጨርቅ የሚመስል ነገር፥ በአራት ማእዘን
ተይዞ ከሰማይ ሲወርድና ወደ እኔ ሲመጣ
ነው፤ 6እርሱን ትኵር ብዬ ስመለከት ልዩ ልዩ
እንስሳትን፥ የዱር አራዊትን፥ በልባቸው የሚ
ሳቡ ፍጥረቶችንና በሰማይ የሚበርሩ ወፎችን
አየሁ፤ 7'ጴጥሮስ ሆይ! ተነሥና እያረድህ
ብላ' የሚለኝንም ድምፅ ሰማሁ፤ 8እኔ ግን
'አይሆንም ጌታ ሆይ! ያልተቀደሰ ወይም
ርኩስ ነገር በአፌ ገብቶ አያውቅም' አልሁ።
9ነገር ግን ሁለተኛ ጊዜ 'እግዚአብሔር ንጹሕ
ያደረገውን አንተ ርኩስ ነው ማለት አትችልም'
የሚል መልስ ከሰማይ መጣ። 10ይህም ሦስት
ጊዜ ከሆነ በኋላ ያ ጨርቅ የሚመስል ነገር
በሙሉ ወደ ሰማይ ተወሰደ። 11እነሆ በዚያን
ጊዜ ከቂሳርያ ወደ እኔ የተላኩ ሦስት ሰዎች
እኛ ወደነበርንበት ቤት ደረሱ። 12ያላንዳች
ማመንታት ከእነርሱ ጋር እንድሄድም መንፈስ
ቅዱስ ነገረኝ፤ እነዚህ ስድስት ወንድሞችም
ከእኔ ጋር ነበሩ፤ ከእነርሱም ጋር አብረን ቆርኔ
ሌዎስ ወደ ተባለው ሰው ቤት ገባን። 13እር
ሱም መልአክን በቤቱ ቆሞ እንዳየና 'ወደ
ኢዮጴ ሰው ልከህ ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንን
አስጠራ፤ 14እርሱ አንተና ቤተሰብህ ሁሉ የም
ትድኑበትን ቃል ይነግርሃል' እንዳለው ነገረን።
15እኔም መናገር በጀመርሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ
በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደወረደ ዐይነት በእነ
ርሱ ላይ ወረደ። 16በዚያን ጊዜ 'ዮሐንስ በውሃ
አጠመቀ፤ እናንተ ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመ
ቃላችሁ' በማለት ጌታ የተናገረውን ቃል አስታ
ወስሁ። 17እኛ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ባመ
ንን ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠውን ስጦታ
ለእነርሱም ከሰጣቸው፤ ታዲያ እግዚአብሔርን
ለመከልከል እኔ ችሎታ አለኝን?"

10፥34 ዘዳ. 10፥17። 11፥16 ሐ.ሥ. 1፥5።

18 እነርሱም ይህንን በሰሙ ጊዜ የሚመል
ሱት አጥተው ዝም አሉ ፤ "እንግዲህ እግዚአብ
ሔር አረማውያንንም ለአዲስ ሕይወት የሚያበ
ቃቸውን ንስሓ ሰጥቶአቸዋል" በማለትም እግዚ
አብሔርን አመሰገኑ ።

አማኞች በአንጾኪያ
"ክርስቲያን" ተባሉ

19 እስጢፋኖስ ተወግሮ በሞተ ጊዜ በተነ
ሣው ስደት ምክንያት የተበተኑት አማኞች
እስከ ፊንቂና እስከ ቆጵሮስ እስከ አንጾኪያም
ሄዱ ፤ ቃሉንም ለአይሁዳውያን ብቻ እንጂ ለሌ
ሎች አይናገሩም ነበር ። 20 ይሁን እንጂ ከቆጵሮ
ስና ከቀሬና የመጡ አንዳንድ አማኞች ወደ አን
ጾኪያ በሄዱ ጊዜ ለአረማውያን* ጭምር ስለ
ጌታ ኢየሱስ መልካም ዜናን አበሠሩ ።
21 ጌታም ይረዳቸው ነበር ፤ ብዙ ሰዎችም አም
ነው ወደ ጌታ ተመለሱ ።
22 በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን
ይህን ስለሰማች በርናባስን ወደ አንጾኪያ ላከ
ችው ። 23 እርሱም ሄዶ እግዚአብሔር ጸጋውን
ለሕዝቡ እንዴት እንደሰጠ ባየ ጊዜ ደስ
አለው ፤ ሁሉም በሙሉ ልብ ጸንተው ለጌታ
ታማኞች ሆነው እንዲኖሩም መከራቸው ።
24 እርሱ መንፈስ ቅዱስና እምነት የሞላበት
ደግ ሰው ነበረ ። ቊጥራቸው ብዙ የሆኑ ሰዎ
ችም ወደ ጌታ ተመለሱ ።
25 ከዚህ በኋላ በርናባስ ሳውልን ለመፈለግ
ወደ ጠርሴስ ሄደ ። 26 ባገኘውም ጊዜ ወደ አን
ጾኪያ አመጣው ፤ ሁለቱም አንድ ዓመት ሙሉ
እዚያ ከነበሩት አማኞች ጋር በአንድነት ሆነው
ብዙ ሰዎችን አስተማሩ ፤ አማኞች ለመጀመሪያ
ጊዜ በአንጾኪያ "ክርስቲያን" ተብለው
ተጠሩ ።
27 በዚያን ጊዜ አንዳንድ ነቢያት ከኢየሩሳ
ሌም ወደ አንጾኪያ ሄዱ ፤ 28 ከእነርሱም አንዱ
አጋቦስ የሚባለው ተነሥቶ በዓለም ሁሉ ታላቅ
ረሀብ እንደሚሆን በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት
ትንቢት ተናገረ ፤ ይህም የሆነው በሮም ንጉሠ
ነገሥት በቀላውዴዎስ ዘመን ነበር ። 29 ስለዚህ
አማኞች ሁሉ እያንዳንዳቸው የችሎታቸውን
ያህል ገንዘብ አዋጥተው በይሁዳ አገር ላሉት
ወንድሞች ዕርዳታ ለመላክ ወሰኑ ። 30 መዋ
ጮም አድርገው በበርናባስና በሳውል እጅ ወደ
ሽማግሌዎች ላኩ ።

## ምዕራፍ 12

በቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ

1 በዚያን ዘመን ፤ ንጉሥ ሄሮድስ አንዳንድ
የቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ማሳደድ ጀመረ ፤
2 የዮሐንስን ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ አስገደ
ለው ። 3 ይህ ነገር አይሁዳውያንን ደስ እንዳሰኛ
ቸው ባየ ጊዜ ጴጥሮስንም ደግሞ አሲያዘው ።
ይህም የሆነው በአይሁድ ፋሲካ በዓል ቂጣ
በሚበላባቸው ቀኖች ነበር ። 4 ጴጥሮስን ካስያዘ
በኋላ ወደ ወህኒ ቤት አስገባው ፤ ከአይሁድ
ፋሲካ በኋላ ለሕዝቡ እስኪያቀርበው ድረስ ፥
አራት አራት ሆነው እንዲጠብቁት ለአራት
ጭፍራዎች አስረከበው ። 5 ስለዚህ ጴጥሮስ በወ
ህኒ ቤት ተይዞ ይጠበቅ ነበር ፤ ነገር ግን ቤተ
ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር በብ
ርቱ ትጸልይ ነበር ።

መልአክ ጴጥሮስን ከእስር ቤት አወጣው

6 ሄሮድስ ጴጥሮስን ለሕዝቡ ሊያቀርበው
አስቦ ነበር ። ጴጥሮስም በዚያች ሌሊት በሁለት
ሰንሰለት ታስሮ በሁለት ወታደሮች መካከል
ተኝቶ ነበር ፤ ሌሎች ወታደሮችም የወህኒ
ቤቱን በር ይጠብቁ ነበር ። 7 በዚያን ጊዜ የእግ
ዚአብሔር መልአክ ተገልጦ ታየ ፤ በወህኒ
ቤቱም ውስጥ ጴጥሮስ በነበረበት ክፍል ብርሃን
በራ ፤ መልአኩ የጴጥሮስን ጐን መትቶ ቀሰቀሰ
ውና "በፍጥነት ተነሥ!" አለው ። ሰንሰለቶ
ቹም ከእጆቹ ላይ ወደቁ ። 8 መልአኩም "ቀበቶ
ህን ታጠቅ ፥ ጫማህንም አድርግ" አለው ። ጴጥ
ሮስ እንደታዘዘው አደረገ ፤ መልአኩም "ነጠላ
ህን ልበስና ተከተለኝ" አለው ። 9 ጴጥሮስም
ወጣና ተከተለው ፤ ራእይ የሚያይ መሰለው
እንጂ መልአኩ ያደረገው ነገር ሁሉ እውነት
አልመሰለውም ። 10 አንደኛውንና ሁለተኛውን
ዘብ አልፈው ወደ ከተማ ወደሚወስደው ወደ
ብረቱ መዝጊያ ደረሱ ። መዝጊያው ሰው ሳይነ
ካው እንዲሁ ተከፈተላቸውና ወጥተው በአንድ
ሰላች መንገድ አልፈው ሄዱ ፤ በድንገትም መል
አኩ ከጴጥሮስ ተለይቶ ሄደ ።
11 ጴጥሮስም ወደ ልቡናው ተመልሶ "እግ
ዚአብሔር መልአኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅና የአ
ይሁድ ሕዝብ ይጠባበቁት ከነበረው ነገር ሁሉ
ያዳነኝ መሆኑን አሁን ገና በእውነት ዐወቅሁ"
አለ ።
12 ወደ ልቡናው ከተመለሰ በኋላ ብዙ ሰዎች
በአንድነት ተሰብስበው ወደሚጸልዩበት ወደ
ማርያም ቤት ሄደ ፤ ማርያም ማርቆስ የተባለው
የዮሐንስ እናት ነበረች ። 13 ጴጥሮስ እዚያ
ደርሶ የውጪውን በር ባንኳኳ ጊዜ ሮዳ የምት
ባል አንዲት ገረድ ማን እንደሆነ ለማወቅ ወደ
በሩ መጣች ። 14 የጴጥሮስ ድምፅ መሆኑን ባወ
ቀች ጊዜ ከደስታዋ ብዛት የተነሣ በሩን ሳትከ
ፍት ሮጣ ወደ ውስጥ ገባችና "ጴጥሮስ በበር
ቆሞአል!" ስትል ተናገረች ። 15 እነርሱም

4* 11፥20 አረማውያን ፦ አንዳንድ ቅጂዎች "የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ" ይላሉ ።
11፥19 ፦ ሐ.ሥ. 8፥1-4 ። 11፥28 ፦ ሐ.ሥ. 21፥10 ። 12፥4 ፦ ዘጸ. 12፥1-27 ።



"አብደሻል!" አሉአት ። እርስዋ ግን "በእው
ነት እርሱ ነው" ስትል አረጋገጠች ። እነርሱም
እንግዲያውስ "የእርሱ መልአክ ይሆናል"
አሉ ።
16 ጴጥሮስ ግን በር ማንኳኳቱን ቀጠለ ፤ እነ
ርሱም በሩን ከፍተው ባዩት ጊዜ ተገረሙ ።
17 እርሱ ግን ዝም እንዲሉ በእጁ አመልክቶ ፥
እግዚአብሔር ከወህኒ ቤት እንዴት እንዳስወ
ጣው አወራላቸውና "ይህን ነገር ለያዕቆብና
ለሌሎቹም አማኞች ንገሩ" አላቸው ። ተለይቶ
አቸውም ወደ ሌላ ቦታ ሄደ ።
18 በማግሥቱ ጠዋት "ጴጥሮስ የት ጠፋ"
በማለት ወታደሮቹ ሁሉ ተራወጡ ። 19 ሄሮድ
ስም ጴጥሮስን አስፈልጎ ባጣው ጊዜ ዘብ ጠባቂ
ዎችን ከመረመረ በኋላ እንዲገደሉ አዘዘ ፤ ከዚ
ህም በኋላ ሄሮድስ ከይሁዳ ወደ ቂሳርያ ሄዶ
እዚያ ተቀመጠ ።

የሄሮድስ አሟሟት

20 ሄሮድስ በጢሮስና በሲዶና ሰዎች ላይ
በጣም ተቈጥቶ ነበር ፤ እነርሱም በአንድነት
መጡና ፤ የንጉሥ ባለሟል ብላስጦስ እንዲተባበራ
ቸው ለምነው እሺ ካሰኙትም በኋላ ንጉሡን
ዕርቅ ጠየቁ ፤ ይህንንም ያደረጉት አገራቸው
ምግብ የምታገኘው ከንጉሡ ግዛት ስለነበረ ነው ።
21 በተቀጠረው ቀን ሄሮድስ ልብሰ መንግሥ
ቱን ለበሰና በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ለሕዝቡ ንግ
ግር አደረገ ። 22 ሕዝቡም "ይህ የአምላክ
ድምፅ ነው እንጂ የሰው ድምፅ አይደለም"
እያሉ ጮኹ ። 23 ሄሮድስ ለእግዚአብሔር
ክብር ሳይሰጥ በመቅረቱ ወዲያውኑ የእግዚአብ
ሔር መልአክ ቀሠፈውና ተልቶ ሞተ ።
24 የእግዚአብሔር ቃል ግን ዘወትር እያደ
ገና እየተስፋፋ ይሄድ ነበር ። 25 በርናባስና
ሳውል አገልግሎታቸውን ፈጽመው ከኢየሩሳ
ሌም ወደ አንጾክያ ተመለሱ ፤ ማርቆስ የተባለ
ውን ዮሐንስንም ከእነርሱ ጋር ይዘው መጡ ።

## ምዕራፍ 13

በርናባስና ሳውል በመንፈስ ቅዱስ
ተመርጠው ለማስተማር ተላኩ

1 በአንጾኪያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያ
ትና መምህራን ነበሩ ፤ እነርሱም ፥ "በርናባስ ፥
ጥቁር የተባለው ስምዖን ፥ የቀሬናው ሉክዮስ ፥
የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስ ባለምዋል የነ
በረው ምናሔና ሳውል" ነበሩ ። 2 እነርሱ ወደ
እግዚአብሔር ሲጸልዩና ሲጾሙ ሳሉ መንፈስ
ቅዱስ "እኔ ለመረጥኋቸው ሥራ በርናባስንና
ሳውልን ለዩልኝ" አለ ።
3 እንደገናም ጾመውና ጸልየው እጆቻቸውን
ከጫኑባቸው በኋላ አሰናበቱአቸው ።

በርናባስና ሳውል በቆጵሮስ

4 በርናባስና ሳውል በመንፈስ ቅዱስ ተልከው
ወደ ሴሌውቅያ ሄዱ ፤ ከዚያም በመርከብ ወደ
ቆጵሮስ ዘለቁ ። 5 ወደ ስልማናም በደረሱ ጊዜ
በአይሁዳውያን ምኵራቦች የእግዚአብሔርን
ቃል አስተማሩ ፤ ዮሐንስም ከእነርሱ ጋር ሆኖ
ይረዳቸው ነበር ።
6 የቆጵሮስን ደሴት አቋርጠው ወደ ጳፉ በደ
ረሱ ጊዜ ባርየሱስ የሚባለውን አንድ አይሁዳዊ
ጠንቋይ አገኙ ፤ እርሱ ሐሰተኛ ነቢይ ነበር ።
7 የሚኖረውም ሰርግዮስ ጳውሎስ ከሚባለው አስ
ተዋይ አገረ ገዥ ጋር ነበረ ፤ ይህ አገረ ገዥ በር
ናባስንና ሳውልን አስጠርቶ የእግዚአብሔርን
ቃል ለመስማት ፈለገ ። 8 ነገር ግን በግሪክ
ቋንቋ "ኤሊማስ" ተብሎ የሚጠራው ጠንቋይ
ባርየሱስ አገረ ገዥው እንዳያምን ፈልጎ በርናባ
ስንና ሳውልን ተቃወማቸው ። 9 ጳውሎስ የተባ
ለው ሳውል ግን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ሰው
የውን ትኵር ብሎ ተመለከተውና እንዲህ
አለው ፥ 10 "አንተ የዲያብሎስ ልጅ ፥ የእውነት
ሁሉ ጠላት ፥ ማታለልና ክፋት ሁሉ የሞላ
ብህ ፥ ቀጥተኛውን የእግዚአብሔርን መንገድ
ማጣመም አትተውምን? 11 አሁንም እነሆ የእ
ግዚአብሔር እጅ ይመታሃል ፤ ዕውርም ትሆና
ለህ ፤ ለጥቂት ጊዜም የፀሐይን ብርሃን አታ
ይም ።"
ወዲያውኑ ዐይኖቹን ጭጋግና ጨለማ ሸፈና
ቸው ፤ እጁን ይዞ የሚመራውንም ሰው ዙሪያ
ውን መፈለግ ጀመረ ። 12 አገረ ገዥውም የሆነ
ውን ነገር ባየ ጊዜ አመነ ፤ ስለ ጌታ በሰማውም
ትምህርት ተደነቀ ።

በርናባስና ጳውሎስ በጲስድያ
ወደምትገኘው አንጾኪያ ሄዱ

13 ከዚህ በኋላ ጳውሎስና ጓደኞቹ በመርከብ
ተሳፍረው ከጳፉ በጵንፍልያ ወደምትገኘው
ወደ ጴርጌ ሄዱ ፤ ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ
ግን ከእነርሱ ተለይቶ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ
ሄደ ። 14 እነርሱ ግን ከጴርጌ ተነሥተው በጲስ
ድያ ወደምትገኘው ወደ አንጾኪያ ሄዱ ፤ በሰን
በት ቀን ወደ አንድ ምኵራብ ገብተው ተቀ
መጡ ። 15 የሙሴና የነቢያት መጻሕፍት ከተነ
በቡ በኋላ የምኵራቡ አለቆች "ወንድሞች
ሆይ! ሕዝቡን የሚያጽናና የምስክር ቃል ካላ
ችሁ ተናገሩ" ብለው ወደነጳውሎስ ሰው ላኩ ።
16 ስለዚህ ጳውሎስ ተነሣና ሕዝቡን በእጁ
ጠቀሰ ፤ እንዲህም ሲል ተናገረ ፥ "የእስራኤል
ሰዎችና በአይሁድ ሥርዓት እግዚአብሔርን
የምታመልኩ እናንተ አሕዛብ ሆይ! ስሙ ፤
17 የዚህ የእስራኤል ሕዝብ አምላክ የቀድሞ

13፥17 ፦ ዘጸ. 1፥7 ፥ 12፥51 ።

አባቶቻችንን መረጠ ፤ በግብጽ አገር በነበሩበት
ጊዜም ትልቅ ሕዝብ አደረጋቸው ፤ በታላቅ
ኀይሉም ከዚያ አገር አወጣቸው ። 18 ለአርባ
ዓመትም ያህል በበረሓ በመታገሥ[5*] ረዳቸው ፤
19 ከዚያም በኋላ በከነዓን አገር ሰባት መንግሥ
ታትን አጥፍቶ ፥ የእነርሱን ምድር አወረሳ
ቸው ፤ 20 ከዚህም በኋላ ለአራት መቶ ኀምሳ
ዓመት ያህል እስከ ነቢዩ ሳሙኤል ድረስ መሳ
ፍንትን ሰጣቸው ።
21 “ከዚያም ቀጥሎ ንጉሥ እንዲያነግሥላ
ቸው እግዚአብሔርን ለመኑ ፤ እግዚአብሔርም
ከብንያም ወገን የሆነውን ፥ የቂስን ልጅ ሳኦልን
ለአርባ ዓመት አነገሠላቸው ። 22 ሳኦልንም ከሻ
ረው በኋላ ዳዊትን አነገሠላቸው ፤ እግዚአብ
ሔር ስለ ዳዊት ሲመሰክር ‘ከልቤ የምወደ
ውን ፥ ፈቃዴንም የሚፈጽመውን የእሴይን
ልጅ ዳዊትን አገኘሁ’ ብሎአል ። 23 ከዚህ ሰው
ዘር እግዚአብሔር በገባው የተስፋ ቃል መሠ
ረት የእስራኤልን አዳኝ ኢየሱስን አመጣ ።
24 ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት ዮሐንስ የእስራ
ኤል ሰዎች ንስሓ ገብተው እንዲጠመቁ አስቀ
ድሞ ሰብኮ ነበር ። 25 ዮሐንስ ሥራውን በጨረሰ
ጊዜ ‘እኔ ማን መሰልኋችሁ? እኔ እኮ መሲሕ
አይደለሁም ፤ ነገር ግን የጫማውን ማሰሪያ ለመ
ፍታት እንኳ የማልበቃ ፥ ከእኔ በኋላ ሌላ ይመ
ጣል’ ይል ነበር ።
26 “እናንተ ከአብርሃም ዘር የተወለዳችሁ
ወንድሞችና በአይሁድ ሥርዓት እግዚአብሔርን
የምታመልኩ አሕዛብ! ይህ የደኅንነት ቃል የተ
ላከው እኮ ለእኛ ነው ። 27 ነገር ግን በኢየሩሳ
ሌም የሚኖሩ ሰዎችና አለቆቻቸው ኢየሱስ
አዳኝ መሆኑን አላወቁም ፤ በየሰንበቱም የሚነበ
ቡትን የነቢያትን መጻሕፍት ሳያስተውሉ የመጻ
ሕፍቱ ቃል እንዲፈጸም ፈረዱበት ። 28 ምንም
እንኳ ለሞት የሚያበቃ ምክንያት ባያገኙበትም
እንዲገድልላቸው ጲላጦስን ለመኑት ። 29 ስለ
እርሱ የተጻፈውን ሁሉ ከፈጸሙ በኋላም ከመስ
ቀል አውርደው ቀበሩት ፤ 30 ነገር ግን እግዚአ
ብሔር ከሞት አስነሣው ። 31 ከገሊላ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ከእርሱ ጋር ለመጡትም ብዙ ቀን ታያ
ቸው ፤ እነርሱም አሁን በሕዝብ ፊት ምስክሮቹ
ናቸው ። 32 እኛም ይዘንላችሁ የመጣነው እግዚ
አብሔር ለአባቶቻችን በተስፋ የሰጠውን መል
ካም ዜና ነው ። 33 ምክንያቱም እግዚአብሔር
ኢየሱስን ከሞት በማስነሣቱ ይህንኑ ተስፋ
ለእኛ ለልጆቻቸው ፈጽሞታል ። ይህም በሁለተ
ኛው መዝሙር ፥

‘አንተ ልጄ ነህ ፥ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ!’

ተብሎ እንደተጻፈው ነው ። 34 መበስበስ እንዳይ
ደርስበት እግዚአብሔር ከሞት እንዳስነሣው
ለማስረዳት ፥

‘ቅዱስና የታመነ የሆነውን ፥
ለዳዊት የተሰጠውን ተስፋ
እሰጣችኋለሁ’ ብሎ ተናግሮአል ።

35 ደግሞም በሌላ መዝሙር ፥

‘ቅዱሱ ልጅህ መበስበስ እንዲደርስበት
አታደርገውም’ ይላል ።

36 ነገር ግን ዳዊት በሕይወቱ ዘመን አገልግሎ
ቱን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከፈጸመ በኋላ
ሞቶአል ፤ ከአባቶቹም ጋር ተቀብሮአል ፤ መበስ
በስም ደርሶበታል ። 37 እግዚአብሔር ከሞት ያስ
ነሣው ግን መበስበስ አልደረሰበትም ። 38 እንግ
ዲህ ወንድሞች ሆይ! የኀጢአት ይቅርታ የሚገ
ኘው በኢየሱስ መሆኑ እንደተሰበከላችሁ
ዕወቁ ፤ 39 በእርሱ የሚያምን ሁሉ ፥ የሙሴ
ሕግ ነፃ ሊያወጣው ከማይችለው ኃጢአት ሁሉ
ነፃ ይወጣል ። 40 ስለዚህ በነቢያት እንዲህ
ተብሎ የተነገረው እንዳይደርስባችሁ ተጠን
ቀቁ ፤

41 ‘እናንተ አሽሟጣጮች! እዩ ፥ ተደነቁ ፥
ጥፉም!
ምክንያቱም ማንም ሰው
ቢያወራላችሁ
የማታምኑትን ሥራ በዘመናችሁ
እሠራለሁ ።’ ”

42 ጳውሎስና በርናባስ ከምኵራብ ሲወጡ
ይህንኑ ነገር በሚመጣው ሰንበት እንደገና እን
ዲነግሩአቸው ሰዎቹ ለመኑአቸው ። 43 የምኵ
ራቡ ጉባኤ በተበተነ ጊዜ ብዙ አይሁዳውያንና
ወደ አይሁዳውያን እምነት የገቡ መንፈሳውያን
ሰዎች ጳውሎስንና በርናባስን ተከተሉአቸው ፤
ጳውሎስና በርናባስም ሰዎቹን በማስተማር በእግ
ዚአብሔር ጸጋ ጸንተው እንዲኖሩ አሳሰቡአ
ቸው ።
44 በሁለተኛው ሰንበት ከከተማው ነዋሪዎች
ጥቂቶቹ ብቻ ሲቀሩ ፥ የቀሩት በሙሉ የእግዚአ
ብሔርን ቃል ለመስማት ተሰበሰቡ ፤ 45 አይሁዳ
ውያን የሕዝቡን ብዛት ባዩ ጊዜ በቅንአት
ተሞሉ ፤ ንግግሩንም እየተቃወሙ ጳውሎስን
ሰደቡት ፤ 46 ጳውሎስና በርናባስ ግን እንዲህ

[5*] 13፥18 በመታገሥ ፦ አንዳንድ ቅጂዎች “በመከባከብ” ይላሉ ።

13፥18 ፦ ዘኍ. 14፥34 ፤ ዘዳ. 1፥31 ። 13፥19 ፦ ዘዳ. 7፥1 ፤ ኢያሱ 14፥1 ። 13፥20 ፦ መሳ. 2፥16 ፤ 1ሳሙ. 3፥20 ።
13፥21 ፦ 1ሳሙ. 8፥5 ፤ 10፥21 ። 13፥22 ፦ 1ሳሙ. 13፥14 ፤ 16፥12 ፤ መዝ. 89፥20 ። 13፥24 ፦ ማር. 1፥4 ፤ ሉቃ. 3፥3 ።
13፥25 ፦ ማቴ. 3፥11 ፤ ማር. 1፥7 ፤ ሉቃ. 3፥16 ፤ ዮሐ. 1፥20 ፥27 ። 13፥28 ፦ ማቴ. 27፥22-23 ፤ ማር. 15፥13-14 ፤
ሉቃ. 23፥21-23 ፤ ዮሐ. 19፥15 ። 13፥29 ፦ ማቴ. 27፥57-61 ፤ ማር. 15፥42-47 ፤ ሉቃ. 23፥50-56 ፤ ዮሐ. 19፥38-42 ።
13፥31 ፦ ሐ.ሥ. 1፥3 ። 13፥33 ፦ መዝ. 2፥7 ። 13፥34 ፦ ኢሳ. 55፥3 ። 13፥35 ፦ መዝ. 16፥10 ።
13፥41 ፦ ዕን. 1፥5 ።



ሲሉ በድፍረት ተናገሩ ፥ “የእግዚአብሔር ቃል
አስቀድሞ ለእናንተ እንዲነገር አስፈላጊ ነው ፤
እምቢ ካላችሁና የዘላለም ሕይወት እንደማይገ
ባችሁ በራሳችሁ ከፈረዳችሁ ግን ፥ እነሆ እኛ
ዞር ብለን ወደ አረማውያን እንሄዳለን ። 47 ምክ
ንያቱም ጌታ

‘ዓለም ሁሉ በአንተ እንዲድን
ለአረማውያን ብርሃን አድርጌሃለሁ’
በማለት ስላዘዘ ነው ።”

48 አረማውያን ይህን በሰሙ ጊዜ ደስ አላ
ቸው ፤ የእግዚአብሔርንም ቃል አከበሩ ፤ ለዘላ
ለም ሕይወት የተመረጡትም ሁሉ አመኑ ።
49 የጌታም ቃል በዚያ አገር ሁሉ ተስፋፋ ።
50 አይሁዳውያን መሪዎች ግን ፥ የአይሁድ እም
ነት ተከታዮች የሆኑትን ሀብታሞች ሴቶችና የከ
ተማውን ታላላቅ ሰዎች አሳድመው በጳውሎስና
በበርናባስ ላይ ስደት እንዲነሣ አደረጉ ፤ ከአገራ
ቸውም አስወጡአቸው ። 51 ጳውሎስና በርናባ
ስም የማስጠንቀቂያ ምስክር እንዲሆን የእግራቸ
ውን አቧራ አራግፈው ወደ ኢቆንዮ ሄዱ ።
52 ደቀ መዛሙርቱም በደስታና በመንፈስ ቅዱስ
ተሞሉ ።

## ምዕራፍ 14

### ጳውሎስና በርናባስ በኢቆንዮም

1 በኢቆንዮም ጳውሎስና በርናባስ አብረው
ወደ አይሁዳውያን ምኵራብ ገቡ ፤ በዚያም
በታላቅ ኀይል ስለተናገሩ ብዙ አይሁዳውያንና
ግሪኮች አመኑ ። 2 ያላመኑት አይሁዳውያን ግን
አረማውያንን አነሣሥተው በወንድሞች ላይ
ጥላቻ እንዲፈጠር አደረጉ ። 3 ስለዚህ ጳውሎስና
በርናባስ የጌታን ነገር በድፍረት እየተናገሩ
እዚያ ብዙ ጊዜ ቆዩ ፤ ጌታም ተአምራትና
ድንቅ ነገሮች በእነርሱ እጅ እንዲደረጉ ሥል
ጣን በመስጠት የእርሱ የጸጋ ቃል እውነተኛ
መሆኑን ያረጋግጥ ነበር ። 4 የከተማው ነዋሪዎች
ግን በሁለት ተከፍለው ግማሹ ከአይሁዳውያን
ጋር ፥ ግማሹም ከሐዋርያት ጋር ሆኑ ።
5 አረማውያንና አይሁዳውያን ከአለቆቻቸው
ጋር ሆነው ጳውሎስንና በርናባስን ሊያንገላቱአ
ቸውና በድንጋይ ሊወግሩአቸው ፈለጉ ፤ 6 ጳው
ሎስና በርናባስ ይህን ባወቁ ጊዜ ልስጥራና
ደርቤ ወደሚባሉት ወደ ሊቃኦንያ ከተሞችና
በዙሪያቸው ወዳለው አገር ሸሽተው ሄዱ ።
7 እዚያም መልካም ዜናን አበሠሩ ።

### ጳውሎስና በርናባስ በልስጥራና በደርቤ

8 በልስጥራ እግሩ የሰለለ አንድ ሰው ነበረ ፤
ይህ ሰው ከተወለደ ጀምሮ ሽባ ስለነበር በእግሩ
ሄዶ አያውቅም ፤ 9 ይህ ሰው ጳውሎስ በሚናገር
በት ጊዜ ተቀምጦ ያዳምጥ ነበር ፤ ጳውሎስ
ሰውየውን ትኩር ብሎ ተመለከተና ለመዳን
የሚያበቃው እምነት እንዳለው ባየ ጊዜ ፤
10 “ቀጥ ብለህ በእግርህ ቁም!” ሲል በታላቅ
ድምፅ ተናገረ ፤ ሰውየውም ብድግ አለና መራ
መድ ጀመረ ። 11 ሰዎቹም ጳውሎስ ያደረገውን
ባዩ ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው “አማል
ክት በሰው አምሳል ሆነው ወደ እኛ ወርደ
ዋል!” በማለት በሊቃኦንያ ቋንቋ ተናገሩ ።
12 በርናባስንም “ድያ” አሉት ፤ ዋናው ተናጋሪ
ጳውሎስ ስለነበረ እርሱን “ሄርሜን” አሉት ።
13 ከከተማው ውጪ ያለው የድያ ቤተ መቅደስ
ካህን ፥ ኮርማዎችንና የአበባ ጒንጒኖችን ወደ
ከተማው በር አምጥቶ ከሕዝቡ ጋር በመተባ
በር ፥ ለጳውሎስና ለበርናባስ መሥዋዕት ሊያቀ
ርብላቸው ፈለገ ።
14 ሐዋርያቱ ጳውሎስና በርናባስ ግን ይህን
በሰሙ ጊዜ በሐዘን ልብሳቸውን ቀደዱ ፤ እየጮ
ኹም ወደ ሕዝቡ ሮጡና እንዲህ አሉ ፥
15 “እናንተ ሰዎች ለምን ይህን ታደርጋላችሁ?
እኛም እኮ እንደ እናንተ ሰዎች ነን ፤ እኛ
እዚህ የመጣነው እናንተ ከዚህ ከከንቱ ነገር
ሁሉ ርቃችሁ ሰማይን ፥ ምድርን ፥ ባሕርንና
በውስጣቸው የሚገኙትን ሁሉ ወደ ፈጠረው
ወደ ሕያው አምላክ እንድትመለሱ መልካም
ዜና ልናበሥራችሁ ነው ፤ 16 ባለፉት ዘመናት
ሕዝቦች ሁሉ በገዛ ራሳቸው መንገድ እንዲሄዱ
እግዚአብሔር ትቶአቸዋል ፤ 17 ይሁን እንጂ
እርሱ እንዴት ያለ ቸር አምላክ መሆኑን የሚ
መሰክር መልካም ሥራ ማድረጉን አላቋረጠም ፤
ምክንያቱም ከሰማይ ዝናምን አዘነመላችሁ ፤
ፍሬ የሚያፈራበትንም ወራት ሰጣችሁ ፤ በምግ
ብና በደስታ ልባችሁን አረካ ።” 18 ምንም
እንኳ ሐዋርያት ይህን ቢናገሩም ሕዝቡ ለእነ
ርሱ መሥዋዕት እንዳያቀርብ ያስተዉት በብዙ
ችግር ነው ።
19 አይሁዳውያን ግን ከአንጾኪያና ከኢቆንዮ
ወደዚያ መጥተው ሕዝቡን አሳደሙና ጳውሎ
ስን በድንጋይ ወገሩት ፤ የሞተ መስሎአቸውም
ጐትተው ከከተማ አወጡት ። 20 ነገር ግን ደቀ
መዛሙርቱ መጥተው በዙሪያው በቆሙ ጊዜ
ጳውሎስ ተነሣና ወደ ከተማ ገባ ፤ በማግሥቱም
ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤ ሄደ ።

### ጳውሎስና በርናባስ በሶርያ ወደምትገኘው አንጾኪያ ተመለሱ

21 ጳውሎስና በርናባስ በደርቤ መልካሙን
ዜና አብሥረው ብዙ ሰዎች አማኞች እንዲሆኑ
አደረጉ ። ከዚህም በኋላ በልስጥራና በኢቆንዮን
አልፈው በጵስድያ ወደምትገኘው አንጾኪያ

13፥47 ፦ ኢሳ. 42፥6 ፤ 49፥6 ። 13፥51 ፦ ማቴ. 10፥14 ፤ ማር. 6፥11 ፤ ሉቃ. 9፥5 ፤ 10፥11 ። 14፥15 ፦ ዘጸ. 20፥11 ፤
መዝ. 146፥6 ።

ሄዱ ። 22 በእነዚያም አገሮች ሁሉ አማኞች በእ
ምነታቸው እንዲጸኑ በማበረታታትና በመምከር
“ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ብዙ
መከራ መቀበል አለብን” እያሉ አስተማሩአ
ቸው ። 23 የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችንም
ሾሙላቸው ፤ ከጾሙና ከጸለዩም በኋላ ላመኑ
በት ጌታ ዐደራ ሰጡአቸው ።
24 በጵስድያም አልፈው ወደ ጵንፍልያ
ሄዱ ፤ 25 በጴርጌም ቃሉን ከተናገሩ በኋላ ወደ
ኢጣሊያ ወረዱ ፤ 26 ከዚያም በመርከብ ተሳፍ
ረው በሶርያ ወደምትገኘው አንጾኪያ ተመለሱ ፤
አንጾኪያ ፥ ስለፈጸሙት ሥራ ለእግዚአብሔር
ጸጋ ዐደራ የተሰጡባት ከተማ ናት ።
27 እዚያም በደረሱ ጊዜ አማኞችን በአንድ
ነት ሰብስበው ፥ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር
ሆኖ ያደረገውን ሁሉና አረማውያንም እንዲያ
ምኑ እንዴት አድርጎ በር እንደከፈተላቸው ነገ
ሩአቸው ። 28 እዚያም ከአማኞች ጋር ብዙ ጊዜ
ቆዩ ።

## ምዕራፍ 15

### የኢየሩሳሌም ጉባኤ

1 አንዳንድ ሰዎች ወደ አንጾኪያ ሄደው ፥
“በሙሴ ሕግ መሠረት የግዝረትን ሥነ ሥርዓት
ካልፈጸማችሁ ልትድኑ አትችሉም” እያሉ አማ
ኞችን ያስተምሩ ጀመር ። 2 ጳውሎስና በርናባስ
ስለዚህ ጉዳይ ከሰዎቹ ጋር በብርቱ ተከራከሩ ፤
ከዚህ በኋላ ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ ካሉ
ከሌሎች ጥቂት ወንድሞች ጋር ሆነው ወደ ኢየ
ሩሳሌም እንዲሄዱና ጉዳዩን ለሐዋርያትና ለሽ
ማግሌዎች እንዲያቀርቡ ተወሰነ ።
3 ስለዚህ እነርሱ በቤተ ክርስቲያን ተልከው
ሄዱ ፤ በፊንቄና በሰማርያ ሲያልፉም የአረማው
ያንን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ተናገሩ ፤
ይህም ዜና አማኞችን ሁሉ አስደሰተ ። 4 ወደ
ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንና ሐዋ
ርያት ፥ ሽማግሌዎችም ተቀበሉአቸው ፤ መልእ
ክተኞቹም እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ሆኖ
ያደረገውን ሁሉ አወሩላቸው ። 5 ነገር ግን ከፈ
ሪሳውያን ወገን የሆኑ አንዳንድ አማኞች ተነ
ሡና “አረማውያን እንዲገረዙና የሙሴንም
ሕግ እንዲጠብቁ ማድረግ ይገባል” አሉ ።
6 ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ይህን ጉዳይ ለመ
መርመር ተሰበሰቡ ፤ 7 ብዙ ክርክር ከተደረገም
በኋላ ጴጥሮስ ተነሥቶ እንዲህ አላቸው ፥ “ወን
ድሞች ሆይ! አረማውያን በእኔ አማካይነት የም
ሥራቹን ቃል ሰምተው እንዲያምኑ ከዚህ
በፊት እግዚአብሔር እኔን ከእናንተ መካከል
እንደመረጠኝ ታውቃላችሁ ። 8 የሰውን ልብ
የሚያውቅ አምላክ ፥ መንፈስ ቅዱስን ለእኛ
እንደሰጠው ዐይነት ለእነርሱም በመስጠት መሰ
ከረላቸው ። 9 ልባቸውን በእምነት ስላነጻ በእ
ኛና በእነርሱ መካከል ምንም ልዩነት አላደረ
ገም ። 10 ታዲያ አባቶቻችንም ሆኑ እኛ ልንሸከ
መው ያልቻልነውን ቀንበር በአማኞች ጫንቃ
ላይ በመጫን እግዚአብሔርን አሁን ለምን ትፈ
ታተኑታላችሁ? 11 እኛም የዳንነው ልክ እንደ
እነርሱ በጌታ ኢየሱስ ጸጋ መሆኑን እናምና
ለን ።”
12 በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ጸጥ አለና በርናባስና
ጳውሎስ በእነርሱ አማካይነት እግዚአብሔር
በአረማውያን መካከል ያደረገውን ተአምርና
ድንቅ ነገር ሁሉ ሲናገሩ በመገረም አዳመጡ
ቸው ። 13 እነርሱ ተናግረው ካበቁ በኋላ ያዕቆብ
እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “ወንድሞች ሆይ! እስቲ
ስሙኝ ፥ 14 እግዚአብሔር በስሙ የሚጠራ ሕዝ
ብን ለመምረጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አረማውያንን
እንዴት እንደጐበኘ ስምዖን አስረድቶአል ።
15 ከዚህም አሳብ ጋር የነቢያት ቃል ይስማ
ማል ፤ ይህም እንዲህ ተብሎ የተጻፈው ነው ፦
16 ‘ከዚህ በኋላ እመለሳለሁ ፤
የፈረሰውንም የዳዊትን ቤት
እሠራለሁ ፤
ፍርስራሹንም ጠግኜ እንደገና
አቆማለሁ ።
17 ይህንንም የማደርገው ሌሎች ሰዎችና
በስሜ የተጠሩት አረማውያን ሁሉ
እግዚአብሔርን እንዲፈልጉ ነው ፤
18 ከጥንት ጀምሮ ይህን ሁሉ ያስታወቀ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ።’
19 “ስለዚህ የእኔ አሳብ ፥ ወደ እግዚአብሔር
የሚመለሱትን አረማውያን እንዳናስቸግራቸው
ነው ። 20 ይልቅስ ‘ለጣዖት በመሠዋቱ ምክንያት
የረከሰ ምግብ አትብሉ ፤ ከዝሙት ራቁ ፥ ሳይታ
ረድና ደሙም ሳይፈስ ታንቆ የሞተ እንስሳ አት
ብሉ ፤ ደምንም አትብሉ’ ብለን እንጻፍላቸው ።
21 ምክንያቱም ከጥንቱም ጀምሮ የሙሴ ሕግ
በየሰንበቱ በምኵራቦች ይነበብ ነበር ፤ ቃሉም
በየከተማው ይሰበክል ።”

### የጉባኤው ውሳኔና ለአማኞች የተጻፈ ደብዳቤ

22 ከዚህ በኋላ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች
ከቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሁሉ ጋር ሆነው ፥ ከጉ
ባኤው መካከል ጥቂት ሰዎችን መርጠው ፥ ከጳ
ውሎስና ከበርናባስ ጋር ወደ አንጾኪያ ለመላክ
ወሰኑ ፤ ስለዚህ በወንድሞች መካከል በመሪነት
መልካም ዝና የነበራቸውን በርስያን የተባለውን
ይሁዳንና ሲላስን መረጡ ። 23 የተጻፈውን ደብ
ዳቤ በእነርሱ እጅ ላኩ ፤ ደብዳቤውም እንዲህ
የሚል ነበር ፦

15፥1 ፦ ዘሌ. 12፥3 ። 15፥7 ፦ ሐ.ሥ. 10፥1-43 ። 15፥8 ፦ ሐ.ሥ. 2፥4 ፤ 10፥44 ። 15፥16-18 ፦ አሞጽ 9፥11-12 ።
15፥20 ፦ ዘጸ. 34፥15-17 ፤ ዘሌ. 17፥10-16 ፤ 18፥6-23 ።



“እኛ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ወንድ
ሞቻችሁ ፥
በአንጾኪያና በሶርያ ፥ በኪልቅያም ለም
ትኖሩ ከአረማውያን ወገን ለሆናችሁ ወንድ
ሞቻችን ሰላምታ እናቀርባለን ፤ 24 ከእኛ
መካከል አንዳንድ ሰዎች ሳናዛቸው ወደ
እናንተ መጥተው በነገሩአችሁ ቃል እንዳስ
ቸገሩአችሁና ግራ እንዳጋቡአችሁ ሰምተ
ናል ፤ 25 ስለዚህ በአንድነት ከተሰበሰብን
በኋላ መልእክተኞችን መርጠን ከተወደ
ዱት ወንድሞቻችን ከበርናባስና ከጳውሎስ
ጋር ወደ እናንተ ልንልካቸው ተስማማን ።
26 በርናባስና ጳውሎስ ስለ ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ
ናቸው ። 27 ውሳኔያችንን በቃልም ጭምር
እንዲነግሩአችሁ ይሁዳንና ሲላስን ልከ
ናል ። 28 ከእነዚህ ከሚከተሉት አስፈላጊ
ነገሮች በስተቀር ሌላ ከባድ ሸክም እንዳን
ጭንባችሁ መንፈስ ቅዱስና እኛ መልካም
ሆኖ አግኝተነዋል ፤ 29 ለጣዖት በመሠዋቱ
ምክንያት የረከሰ ምግብ አትብሉ ፤ ሳይታረ
ድና ደሙ ሳይፈስ ታንቆ የሞተ እንስሳ
አትብሉ ፤ ደምም አትብሉ ፤ ከዝሙት
ራቁ ፤ ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ ብትጠበቁ
መልካም ታደርጋላችሁ ፤ ደኅና ሁኑ ።”
30 መልእክተኞቹም ተሰናብተው ወደ አንጾኪያ
ሄዱ ፤ አማኞቹንም ሰብስበው ደብዳቤውን ሰጡ
አቸው ። 31 አማኞቹም ደብዳቤውን ባነበቡ
ጊዜ በመልእክቱ ተጽናንተው እጅግ ደስ አላ
ቸው ። 32 ይሁዳና ሲላስ ነቢያት ስለነበሩ ወንድ
ሞችን በብዙ ቃል መክረው አጽናኑአቸው ፤
አበረታቱአቸውም ። 33 ይሁዳና ሲላስ ጥቂት
ቀኖች እዚያ ከቆዩ በኋላ ፥ ከአማኞች ወንድ
ሞች ጋር ተሰነባብተው ወደ ላኩአቸው ተመል
ሰው ሄዱ ።6* 35 ጳውሎስና በርናባስም ከሌሎች
ከብዙ አማኞች ጋር ሆነው የጌታን ቃል እያስ
ተማሩና እየሰበኩ ጥቂት ቀኖች በአንጾኪያ
ቆዩ ።

### የጳውሎስና የበርናባስ መለያየት

36 ከጥቂት ቀኖች በኋላ ጳውሎስ በርናባስን
“ና እንመለስና ከዚህ በፊት የጌታን ቃል ባበሠ
ርንባቸው ከተማዎች ሁሉ ያሉትን ወንድሞች
እንጐብኝ ፤ እንዴት እንደሆኑም እንወቅ”
አለው ። 37 በርናባስም ማርቆስ የተባለው ዮሐ
ንስ ከእነርሱ ጋር አብሮአቸው እንዲሄድ
ፈለገ ። 38 ጳውሎስ ግን ይህ ሰው ከእነርሱ ጋር
አብሮ እንዲሄድ አልፈቀደም ፤ ምክንያቱም
እርሱ በጵንፍልያ ከእነርሱ ተለይቶ ስለቀረና
ወደ ሥራም ከእነርሱ ጋር ስላልሄደ ነው ።
39 በዚህ ምክንያት በመካከላቸው ከፍ ያለ ክር
ክር ተነሣና ተለያዩ ፤ ስለዚህ በርናባስ ማርቆስን
ይዞ በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄደ ። 40 ጳውሎስ
ግን ሲላስን መረጠ ፤ ወንድሞችም ጳውሎስን
ለጌታ ጸጋ ዐደራ ከሰጡት በኋላ ሄደ ። 41 እር
ሱም አብያተ ክርስቲያናትን እያበረታታ በሶር
ያና በኪልቅያ በኩል አለፈ ።

## ምዕራፍ 16

### ጢሞቴዎስ ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር

1 ጳውሎስ ወደ ደርቤና ወደ ልስጥራ ሄደ ፤
በልስጥራ ጢሞቴዎስ የሚባል አማኝ ይኖር
ነበር ፤ እናቱ አይሁዳዊት ክርስቲያን ነበረች ፤
አባቱ ግን አረማዊ ግሪክ ነበር ። 2 ጢሞቴዎስ
በልስጥራንና በኢቆንዮን ባሉት ወንድሞች
ዘንድ መልካም ዝና ነበረው ። 3 ጳውሎስ ጢሞ
ቴዎስን ይዞ መሄድ ስለፈለገ እንዲገረዝ አደረ
ገው ፤ ይህንንም ያደረገው በዚያ ስፍራ በነበ
ሩት አይሁዳውያን ምክንያት ነው ፤ ምክንያ
ቱም እነርሱ የጢሞቴዎስ አባት ግሪካዊ መሆ
ኑን ያውቁ ስለነበር ነው ። 4 ጳውሎስና ሲላስ
በየከተማው ሲያልፉ በኢየሩሳሌም ባሉት ሐዋ
ርያትና ሽማግሌዎች የተወሰነውን ደንብ ለአማ
ኞች ያስታውቁ ነበር ፤ በሥራ ላይ እንዲያውሉ
ትም ያሳስቡአቸው ነበር ። 5 ስለዚህ አብያተ
ክርስቲያናት በእምነት ጠነከሩ ፤ ቍጥራቸውም
በየቀኑ እየጨመረ ይሄድ ነበር ።

### ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ እንዲሄድ ተጠራ

6 ጳውሎስና ሲላስ በእስያ ቃሉን እንዳይና
ገሩ መንፈስ ቅዱስ ስለከለከላቸው በፍርግያና
በገላትያ አገር አድርገው አለፉ ፤ 7 ወደ ሚስያ
ድንበር በደረሱ ጊዜ ወደ ቢትኒያ ለመሄድ አስ
በው ነበር ፤ ነገር ግን የኢየሱስ መንፈስ ወደ
ዚያ እንዲሄዱ አልፈቀደላቸውም ። 8 ስለዚህ
በሚስያ በኩል አልፈው ወደ ጢሮአዳ ወረዱ ።
9 እዚያ በሌሊት አንድ የመቄዶንያ ሰው ቆሞ
“ወደ መቄዶንያ ተሻገርና ዕርዳን!” እያለ ሲለ
ምነው ጳውሎስ በራእይ አየ ። 10 ጳውሎስ ይህን
ራእይ ካየ በኋላ ወዲያውኑ ወደ መቄዶንያ
ለመሄድ ፈለግን ፤ ምክንያቱም ለመቄዶንያ ሰዎ
ችም መልካሙን ዜና እንድናበሥር እግዚአብ
ሔር እንደጠራን ስለተረዳን ነው ።

### ልድያ በክርስቶስ አመነች

11 ከጢሮአዳ በመርከብ ተሳፍረን በቀጥታ
ወደ ሳሞት ራቄ ሄድን ፤ በማግሥቱም ወደ

6* 15፥33 አንዳንድ የጥንት መጻሕፍት በ34 ቍጥር የሚገኘውን ይጨምራሉ ፤ “34 ሲላስ ግን እዚያው መቅረት ፈለገ ።”
15፥38 ፦ ሐ.ሥ. 13፥13 ።

ናጶሌ ሄድን ። 12 ከዚያም ተነሥተን ወደ ፊል
ጵስዩስ ደረስን ፤ ፊልጵስዩስ በመቄዶንያ የምት
ገኝ ታላቅ ከተማና የሮማውያን ቅኝ አገር ነበ
ረች ፤ በዚህችም ከተማ ጥቂት ቀኖች አሳለፍን ።
13 በሰንበትም ቀን አይሁዳውያን ለጸሎት የሚሰ
በሰቡበት ስለመሰለን ከከተማው ወጥተን ወደ
ወንዝ ዳር ሄድን ፤ እዚያም ተቀምጠን ለተሰበሰ
ቡት ሴቶች ቃሉን አስተማርን ። 14 ይሰሙን ከነ
በሩትም ሴቶች አንድዋ የትያጥሮን ከተማ ተወ
ላጅ የሆነች የቀይ ልብስ ነጋዴ ፣ ልድያ የምት
ባል ሴት ነበረች ፤ እርስዋ እግዚአብሔርን የም
ታመልክ ሴት ነበረች ፤ ጌታም ልቡናዋን ስለከፈ
ተላት ጳውሎስ የሚናገረውን ቃል ታዳምጥ
ነበር ፤ 15 እርስዋና በቤትዋ ያሉ ሰዎች ሁሉ
ከተጠመቁ በኋላ "በጌታ የማምን መሆኔን ካረጋ
ገጣችሁልኝ ወደ ቤቴ መጥታችሁ ተቀመጡ"
ስትል አጥብቃ ለመነችን ።

በፊልጵስዩስ ከተማ
ጳውሎስና ሲላስ ታሰሩ

16 አንድ ቀን ወደ ጸሎት ቦታ ስንሄድ ወደ
ፊት የሚሆነውን ነገር በጥንቈላ የሚያናግር
ርኩስ መንፈስ ያደረባት አንዲት አገልጋይ ልጃ
ገረድ በመንገድ አገኘችን ፤ ይህች ልጃገረድ
በጥንቈላዋ ለአሳዳሪዎችዋ ብዙ ትርፍ ታስገኝላ
ቸው ነበር ። 17 እርስዋ ጳውሎስንና እኛን እየተ
ከተለች "እነዚህ ሰዎች የልዑል እግዚአብሔር
አገልጋዮች ናቸው! እነርሱ የደኅንነትን መን
ገድ ያበሥሩአችኋል" በማለት ትጮኽ ነበር ።
18 ይህንንም ብዙ ቀን እየደጋገመች ታደርግ
ነበር ፤ ጳውሎስ ግን ተበሳጨና ዞር ብሎ ርኩ
ሱን መንፈስ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከእርስዋ
እንድትወጣ አዝዝሃለሁ!" አለው ። ርኩሱም
መንፈስ ወዲያውኑ ወጣ ።
19 አሳዳሪዎችዋ ጥቅም የሚያገኙበት ተስፋ
እንደተቋረጠባቸው ባዩ ጊዜ ጳውሎስንና ሲላ
ስን ያዙአቸው ፤ እየጐተቱም ወደ አደባባይ
ወሰዱአቸውና በሹሞች ፊት አቀረቡአቸው ።
20 ወደ ሮማውያን ባለሥልጣኖችም አመጡአቸ
ውና እንዲህ አሉ ፤ "እነዚህ ሰዎች አይሁዳው
ያን ናቸው ፤ በከተማችንም ሁከት ያስነሣሉ ፤
21 እኛ የሮም ዜጋዎች ልንቀበለው ወይም ልና
ደርገው ያልተፈቀደልንን ሥርዓት ያስተም
ራሉ ።" 22 ሕዝቡም ሁሉ ተባብሮ በእነርሱ
ላይ ተነሣ ።
ባለሥልጣኖችም የጳውሎስንና የሲላስን
ልብስ ገፈፉና በዱላ እንዲደበድቡ አዘዙ ።
23 ብዙ ከተደበደቡም በኋላ ወደ ወህኒ ቤት አገ
ቡአቸው ፤ የወህኒ ቤቱም ጠባቂ በጥብቅ እንዲ
ጠብቃቸው ታዘዘ ። 24 ጠባቂው ይህን ትእዛዝ
ከተቀበለ በኋላ በወህኒ ቤቱ ውስጠኛ ክፍል አስ
ገባቸው ፤ እግሮቻቸውንም በግንድና ግንድ መካ
ከል አጣብቆ አሰራቸው ።

25 ወደ እኩለ ሌሊት ገደማ ጳውሎስና ሲላስ
በጸሎቱና በመዝሙር እግዚአብሔርን ያመሰግኑ
ነበር ፤ ሌሎችም እስረኞች ያዳምጡአቸው
ነበር ። 26 በድንገት የወህኒ ቤቱ መሠረት እስኪ
ናጋ ድረስ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ ፤ በሮ
ቹም ሁሉ በአንድ ጊዜ ተከፈቱ ፤ የእያንዳን
ዱም እስረኛ ሰንሰለት ተፈታ ። 27 ጠባቂው ከእ
ንቅልፉ ነቅቶ የወህኒ ቤቱ በሮች ተከፍተው
ባየ ጊዜ ፣ እስረኞቹ ያመለጡ መስሎት ሰይፉን
መዘዘና ራሱን ሊገድል ፈለገ ። 28 ነገር ግን ጳው
ሎስ ፣ "ሁላችንም እዚህ ነን! ስለዚህ በራስህ
ላይ ጕዳት አታድርስ!" ሲል በታላቅ ድምፅ
ጮኸ ።
29 በዚህ ጊዜ ጠባቂው መብራት አስመጥቶ
እየሮጠ ወደ ውስጥ ገባ ፤ እየተንቀጠቀጠም በጳ
ውሎስና በሲላስ እግር ሥር በግንባሩ ተደፋ ።
30 ወደ ውጪም አወጣቸውና "ጌቶቼ! ለመዳን
ምን ማድረግ ይገባኛል?" አላቸው ።
31 እነርሱም "በጌታ በኢየሱስ እመን ፣ ትድ
ናለህ ፤ ቤተሰቦችህም ይድናሉ" አሉት ። 32 የጌ
ታንም ቃል ለእርሱና በእርሱ ቤት ላሉትም
ሁሉ ተናገሩ ። 33 በዚያኑ ሰዓት በሌሊት የወህኒ
ቤቱ ጠባቂ ወሰዳቸውና ቍስላቸውን አጠበላ
ቸው ፤ ወዲያውኑ እርሱና ቤተሰቡ በሙሉ ተጠ
መቁ ። 34 ከዚህ በኋላ ጳውሎስንና ሲላስን ወደ
ቤቱ ወስዶ ምግብ አቀረበላቸው ፤ በእግዚአብ
ሔር ስላመነም ከቤተ ሰቡ ጋር ደስ አለው ።
35 በነጋም ጊዜ ባለሥልጣኖቹ "እነዚያ
ሰዎች ይለቀቁ" ብለው ፖሊሶችን ላኩ ።
36 የወህኒ ቤት ጠባቂውም "እናንተ እንድት
ለቀቁ ባለሥልጣኖቹ ሰው ልከዋልና እንግዲህ
ወጥታችሁ በሰላም ሂዱ" ሲል ለጳውሎስ ነገ
ረው ።
37 ጳውሎስ ግን "እኛ የሮም ዜጋዎች ስንሆን
ያለፍርድ በአደባባይ ገርፈው ወደ ወህኒ አስገቡ
ተውናል ። አሁን ደግሞ ከወህኒ ቤት በስውር
እንድንወጣ ያደርጋሉን? አይሆንም! እነርሱ
ራሳቸው መጥተው ያስወጡን?" ሲል መለሰ ።
38 ፖሊሶቹ ይህን ነገር ለባለሥልጣኖቹ
ነገሩ ፤ ባለሥልጣኖቹም ጳውሎስና ሲላስ የሮም
ዜጋዎች መሆናቸውን ባወቁ ጊዜ ፈሩ ። 39 ስለ
ዚህ መጥተው ይቅርታ ጠየቁአቸውና ከወህኒ
ቤት አስወጡአቸው ፤ ከከተማውም እንዲሄዱ
ለመኑአቸው ።
40 ጳውሎስና ሲላስም ከወህኒ ቤት ወጥተው
ወደ ልድያ ቤት ገቡ ፤ እዚያም ወንድሞችን አግ
ኝተው አጽናኑዋቸውና ከተማውን ለቀው ሄዱ ።

## ምዕራፍ 17

እነጳውሎስ በተሰሎንቄ

1 ጳውሎስና ሲላስ በአንፊጶሊስና በአጶሎንያ
አልፈው ወደ ተሰሎንቄ ሄዱ ፤ እዚያም የአይሁ
ዳውያን ምኵራብ ነበረ ። 2 ጳውሎስ እንደ



ልማዱ ወደ ምኵራብ ገባ ፤ ሦስት ሰንበትም ከቅ
ዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሰ ለሕዝብ ተናገረ ።
3 መሲሕ መከራ መቀበልና ከሞት መነሣት እን
ደሚገባው ገልጦ እያስረዳ "ይህ እኔ የማበሥራ
ችሁ ኢየሱስ መሲሕ ነው" ይል ነበር ። 4 ስለዚህ
ከእነርሱ አንዳንዶቹ ቃሉን ተረድተው ከጳውሎ
ስና ከሲላስ ጋር ተባበሩ ፤ እንዲሁም እግዚአብ
ሔርን የሚያመልኩ ብዙ ግሪካውያንና በከተ
ማው የታወቁ ሴቶች ቃሉን ተረድተው ተባ
በሩ ።
5 አይሁዳውያን ግን ቀንተው የሚበጠብጡ
ሥራ ፈቶችን ከየመንገዱ ሰበሰቡና አሳደሙ ።
በከተማው ውስጥ ብጥብጥ እንዲነሣ አደረጉ ፤
ጳውሎስንና ሲላስን አውጥተው ለሕዝቡ ለመስ
ጠትም የኢያሶንን ቤት ከበቡ ። 6 ነገር ግን እነር
ሱን ባጡአቸው ጊዜ ኢያሶንንና አንዳንድ አማኞ
ችን ለከተማው ባለሥልጣኖች ለማቅረብ እየጐ
ተቱ ወሰዱአቸው ፤ እንዲህም እያሉ ይጮኹ
ነበር ፣ "እነዚህ ዓለምን ሁሉ ያወኩ ሰዎች ፣
አሁን ደግሞ ወደዚህ መጥተዋል! 7 ኢያሶንም
ተቀብሎአቸዋል ፤ 'ኢየሱስ የሚባል ሌላ ንጉሥ
አለ' እያሉም የሮምን ንጉሠ ነገሥት የቄሳርን
ትእዛዝ ይቃወማሉ ።" 8 ሕዝቡና የከተማው ባለ
ሥልጣኖች ይህን በሰሙ ጊዜ ተሸበሩ ። 9 ኢያሶን
ንና ሌሎቹንም ዋስ አስጠርተው ለቀቁአቸው ።

እነጳውሎስ በቤርያ

10 ወንድሞች በቶሎ ጳውሎስንና ሲላስን በሌ
ሊት ወደ ቤርያ እንዲሄዱ አደረጉአቸው ፤
እዚያ በደረሱ ጊዜ ወደ አይሁዳውያን ምኵራብ
ገቡ ። 11 በቤርያ ያሉት አይሁዳውያን በተሰሎ
ንቄ ካሉት ይልቅ ቅን አመለካከት ያላቸው ስለነ
በሩ ፣ ቃሉን በታላቅ ደስታ ተቀበሉ ፤ የቃሉንም
እውነተኛነት ለማረጋገጥ በየቀኑ ቅዱሳት መጻሕ
ፍትን ይመረምሩ ነበር ። 12 ስለዚህ ከእነርሱ
ብዙዎች አመኑ ፤ ብዙዎች የግሪክ ሀብታሞች
ሴቶችና ብዙዎች ግሪካውያን ወንዶችም
አመኑ ። 13 ነገር ግን በተሰሎንቄ ያሉት አይሁዳ
ውያን ጳውሎስ በቤርያም የእግዚአብሔርን ቃል
እንዳበሠረ ባወቁ ጊዜ ወደዚያ መጡና ሕዝቡን
አሳድመው ብጥብጥ አስነሡ ። 14 በዚህ ጊዜ ወን
ድሞች በቶሎ ጳውሎስ ወደ ባሕሩ አጠገብ እን
ዲሄድ አደረጉት ፤ ሲላስና ጢሞቴዎስ ግን እዚ
ያው በቤርያ ቀሩ ። 15 ጳውሎስን የሸኙት ሰዎች
እስከ አቴና አደረሱት "ሲላስና ጢሞቴዎስ
በቶሎ ወደ እኔ ይምጡልኝ" የሚለውንም የጳው
ሎስን ትእዛዝ ይዘው ወደ ቤርያ ተመለሱ ።

ጳውሎስ በአቴና

16 ጳውሎስ በአቴና ሆኖ ሲላስንና ጢሞቴዎ
ስን ሲጠብቅ ሳለ ፣ በከተማዋ ጣዖት መሙላቱን
በተመለከተ ጊዜ በመንፈሱ ተበሳጨ ። 17 ስለ
ዚህ በምኵራብ ፣ ከአይሁዳውያንና እግዚአብሔ
ርንም ከሚያመልኩት ሰዎች ጋር ፣ በአደባባ
ይም በየቀኑ ከሚያገኛቸው ሰዎች ጋር ይከራ
ከር ነበር ። 18 ኤፒኩሮሳውያንና እስቶይኮች የተባሉ
ፈላስፎችም ወደ እርሱ እየመጡ ይከራከሩ
ነበር ። አንዳንዶቹ "ይህ ለፍላፊ ምን ማለት
ይፈልጋል?" ሲሉ ፣ ሌሎች ደግሞ "ስለ አዳ
ዲስ አማልክት የሚናገር ይመስላል" ይሉ
ነበር ። ይህንንም ያሉበት ምክንያት ጳውሎስ
የኢየሱስንና የትንሣኤውን መልካም ዜና ስላበ
ሠረ ነው ። 19 ስለዚህ ጳውሎስን አርዮስፖጎስ
በተባለው ስፍራ ወደሚሰበሰበው ጉባኤ አመጡ
ትና እንዲህ አሉት ፣ "ይህ አንተ የምታስተም
ረው አዲስ ትምህርት ምን እንደሆነ ማወቅ እን
ችላለንን? 20 አንዳንድ አዳዲስ ነገሮችን አሰምተ
ኸናል ፤ ስለዚህ እነዚህ ነገሮች ምን እንደሆኑ
ማወቅ እንፈልጋለን ።" 21 ይህንን ያሉት የአቴና
ነዋሪዎችና በአቴና የሚኖሩ የውጭ አገር
ሰዎች ሁሉ አዲስ ነገር በመናገርና በመስማት
ብቻ ጊዜያቸውን ማሳለፍ ይወድዱ ስለነበር
ነው ።
22 በዚህ ጊዜ ጳውሎስ በአርዮስፖጎስ በተሰበ
ሰበው ጉባኤ ፊት ቆመና እንዲህ አለ ፣ "የአ
ቴና ሰዎች ሆይ! በሁሉም በኩል በጣም ሃይማ
ኖተኞች መሆናችሁን ተረድቻለሁ ፤ 23 ምክንያ
ቱም በከተማችሁ እየተዘዋወርሁ የአምልኮ ስፍ
ራዎቻችሁን ስመለከት 'ለማይታወቅ አምላክ'
ተብሎ የተጻፈበትን የመሠዊያ ቦታ አገኘሁ ፤
እንግዲህ እኔ አሁን የምነግራችሁ ስለዚሁ ሳታ
ውቁ ስለምታመልኩት አምላክ ነው ። 24 እርሱ
ዓለምንና በዓለም ያለውንም ሁሉ የፈጠረ ነው ፤
የሰማይና የምድርም ጌታ ነው ፤ እርሱ በሰው
እጅ በተሠራ ቤተ መቅደስ አይኖርም ፤ 25 ሕይ
ወትንና እስትንፋስን ፣ ሌሎችንም ነገሮች
ለሰው ሁሉ የሚሰጥ እርሱ ስለሆነ ፣ ምንም
ነገር አይጐድለውም ፤ የሰውም ዕርዳታ አያስፈ
ልገውም ። 26 እርሱ የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ
ሰው ፈጠረ ፤ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩም
አደረገ ፤ የተወሰኑ ዘመኖችንና የሚኖሩባቸው
ንም ቦታዎች መደበላቸው ። 27 ይህንንም ያደረ
ገው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲፈልጉና በመ
መራመርም ፈልገው እርሱን ማግኘት እንዲ
ችሉ ነው ፤ ሆኖም እርሱ ከእኛ ከእያንዳንዳችን
ሩቅ ነው ማለት አይደለም ። 28 ምክንያቱም ፣
'ሕይወት የምናገኘውና
የምንንቀሳቀሰው ፣
የምንኖረውም በእርሱ ነው ፤'
ይህም የእናንተ ባለ ቅኔዎች
'እኛ ሁላችን የእርሱ ልጆች ነን'
እንዳሉት ነው ።

17፡24-25 ፣- 1ነገ. 8፡27 ፤ ኢሳ. 42፡5 ፤ ሐ.ሥ. 8፡47 ።

29 እንግዲህ እኛ የእርሱ ልጆች ከሆንን ‘እግዚአ
ብሔር በሰው ጥበብና አሳብ ከወርቅ ወይም
ከብር ወይም ከድንጋይ የተሠራውን ቅርጽ ይመ
ስላል’ ብለን ማሰብ አይገባንም ። 30 እንግዲህ
ሰዎች ባለማወቅ ያደረጉትን እግዚአብሔር ችላ
ብሎ አልፎታል ፤ አሁን ግን በየአገሩ ያሉ
ሰዎች ሁሉ ንስሓ እንዲገቡ አዞአል ፣ 31 እርሱ
በመረጠው ሰው አማካይነት በዓለም ሁሉ ላይ
በእውነት የሚፈርድበትን ቀን ወስኖአል ፤ ይህን
ንም ያረጋገጠው ያንን የመረጠውን ሰው ከሞት
በማስነሣቱ ነው ።”
32 “ከሞት መነሣት” የሚለውን ቃል
በሰሙ ጊዜ አንዳንዶች አፌዙበት ፤ ሌሎች ግን
“ስለዚህ ጉዳይ ስትናገር ሌላ ጊዜ እንሰማለን”
አሉት ። 33 ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ከጉባኤው
ወጥቶ ሄደ ፤ 34 አንዳንድ ሰዎች ግን ከእርሱ
ጋር ተባበሩና አመኑ ፤ ካመኑትም ሰዎች መካ
ከል የአርዮስፓጎስ ጉባኤ አባል የሆኑት ዲዮኒስ
ዮስ የተባለ ሰውና ደማሪስ የተባለች አንዲት
ሴት ፥ ሌሎችም ይገኙባቸዋል ።

## ምዕራፍ 18

### ጳውሎስ በቆሮንቶስ

1 ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ከአቴና ተነሥቶ ወደ
ቆሮንቶስ ሄደ ፤ 2 እዚያ የጳንጦስ ተወላጅ የሆነ
ውን አቂላ የሚባል አንድ አይሁዳዊ ሰው
አገኘ ። አቂላ ከሚስቱ ከጵርስቅላ ጋር ከኢጣ
ሊያ ገና መምጣቱ ነበር ፤ ምክንያቱም የሮም
ንጉሥ ነገሥት ቀላውዴዎስ አይሁዳውያን ሁሉ
ከሮም እንዲወጡ አዝዞ ስለነበር ነው ፤ ስለዚህ
ጳውሎስ ወደ እነርሱ ሄዶ ተዋወቃቸው ፤ 3 የእ
ርሱ ሥራ ልክ እንደ እነርሱ ድንኳን መስፋት
ስለነበር ፥ ከእነርሱ ጋር ተቀምጦ አብሮአቸው
ይሠራ ነበር ። 4 በየሰንበቱም በምኩራብ እየተ
ገኘ ንግግር በማድረግ አይሁዳውያንንና ግሪካው
ያንን ያስረዳ ነበር ።
5 ሲላስና ጢሞቴዎስ ከመቄዶንያ በመጡ
ጊዜ ጳውሎስ “ኢየሱስ መሲሕ ነው” በማለት
ለአይሁዳውያን እየመሰከረ በማስተማር ጊዜውን
ሁሉ ያሳልፍ ነበር ። 6 ነገር ግን አይሁዳውያን
በተቃወሙትና በሰደቡት ጊዜ የልብሱን ትቢያ
አራግፎ “እንግዲህ ቢፈረድባችሁ በራሳችሁ
ጥፋት ነው! እኔ ኀላፊነት የለብኝም ፤ ከእንግ
ዲህ ወዲህ ወደ አረማውያን እሄዳለሁ” አላ
ቸው ። 7 ስለዚህ ከእነርሱ ተለይቶ ቲቶስ ኢዮስ
ጦስ ወደተባለው ሰው ቤት ሄደ ፤ ይህ ሰው እግ
ዚአብሔርን የሚያመልክ ነበር ፤ ቤቱም በምኩ
ራብ አጠገብ ነበር ። 8 ቀርስጳስ የሚባል የምኩ
ራብ አለቃ ከቤተሰቡ ሁሉ ጋር በጌታ አመነ ፤
ብዙ የቆሮንቶስ ሰዎችም ጳውሎስ ሲናገር ሰም
ተው አመኑና ተጠመቁ ።
9 ጌታም ጳውሎስን ሌሊት በራእይ እንዲህ
አለው ፥ “አትፍራ ፥ ተናገር ፥ ዝም አትበል ፤
10 ምክንያቱም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ፤ በዚህች
ከተማ ብዙ ሰዎች አሉኝና ጉዳት ሊያደርስብህ
የሚችል ማንም የለም ።” 11 ስለዚህ ጳውሎስ
የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ እያስተማረ
አንድ ዓመት ተኩል እዚያ ቆየ ።
12 ጋልዮስ የአካይያ ገዢ ሆኖ በተሾመ ጊዜ
አይሁዳውያን በአንድነት ተባብረው በጳውሎስ
ላይ ተነሡ ፤ ወደ ፍርድ ሸንጎ ወሰዱትና ፤
13 “ይህ ሰው ሕግ በማይፈቅደው መንገድ
ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ያደር
ጋል” አሉ ።
14 ጳውሎስ መልስ ለመስጠት ተዘጋጅቶ
ሳለ ፥ ጋልዮስ አይሁዳውያንን እንዲህ አላቸው ፤
“እናንተ አይሁዳውያን! በደል ወይም ከባድ
ወንጀል ተፈጽሞባችሁ ቢሆን ኖሮ ክሳችሁን
በሰማሁ ነበር ፤ 15 ነገር ግን ስለ ቃላትና ስለ
ስሞች ፥ ስለ ሕጋችሁም የምትከራከሩ ከሆነ
የራሳችሁ ጉዳይ ነው ፤ እኔ በዚህ ነገር ላይ
መፍረድ አልፈልግም ።” 16 እንዲህም ብሎ
ከፍርድ ሸንጎው አስወጣቸው ። 17 በዚህ ጊዜ
ሁሉም የምኩራብ አለቃውን ሶስቴንስን ይዘው
በሸንጎው ፊት ደበደቡት ፤ ይህ ሁሉ ሲሆን
ጋልዮስ ደንታ አልነበረውም ።

### ጳውሎስ ወደ አንጾኪያ ተመለሰ

18 ጳውሎስ ከወንድሞቹ ጋር ብዙ ቀኖች
በቆሮንቶስ ከቆየ በኋላ ተሰናብቶአቸው ወደ
ሶርያ ሄደ ፤ ጵርስቅላና አቂላም ከእርሱ ጋር
ነበሩ ፤ ነገር ግን ስእለት ስለነበረበት ከመሄዱ
በፊት ክንክሬያ በሚባል ቦታ ራሱን ተላጨ ።
19 ወደ ኤፌሶን በደረሱ ጊዜ ጵርስቅላንና አቂ
ላን እዚያ ተዋቸው ፤ እርሱ ግን ወደ ምኩራብ
ገብቶ ለአይሁዳውያን ንግግር ያደርግ ነበር ።
20 ረዘም ላለ ጊዜ ከእነርሱ ጋር እንዲቆይ ቢለ
ምኑትም እሺ አላላቸውም ። 21 ነገር ግን “የእ
ግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን ሌላ ጊዜ ወደ እና
ንተ ተመልሼ እመጣለሁ” አላቸውና ከኤፌሶን
በመርከብ ተሳፍሮ ሄደ ።
22 ወደ ቂሳርያም በደረሰ ጊዜ ከዚያ ወደ
ኢየሩሳሌም ሄዶ ለቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሰላ
ምታ ከሰጠ በኋላ ተመልሶ ወደ አንጾኪያ
ወረደ ። 23 እዚያም ጥቂት ጊዜ ቆየ ፤ ከዚህ
በኋላ በገላትያና በፍርግያ አገሮች ከቦታ ወደ
ቦታ እየተዘዋወረ አማኞችን አበረታታ ።

### አጵሎስ በኤፌሶንና በቆሮንቶስ

24 የእስክንድርያ ተወላጅ የሆነ አጵሎስ የተ
ባለ አንድ አይሁዳዊ ወደ ኤፌሶን መጣ ፤ እርሱ
ቅዱሳት መጻሕፍትን ጠንቅቆ የተማረና ጥሩ

18፥18 ፦ ዘኁ. 6፥18 ።



የአነጋገር ችሎታ ያለው ሰው ነበረ ። 25 ስለ
ጌታ መንገድ የተማረና በመንፈስም የተቃጠለ
ሆኖ ስለ ኢየሱስ በትክክል ይሰብክና ያስተምር
ነበር ። ይሁን እንጂ እርሱ የሚያውቀው የዮሐ
ንስን ጥምቀት ብቻ ነበር ። 26 እርሱ በድፍረት
በምኩራብ መናገር ጀመረ ነገር ግን ጵርስቅላና
አቂላ በሰሙት ጊዜ ፥ ወደ ቤታቸው ወሰዱትና
የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ በትክ
ክል አብራርተው ገለጡለት ። 27 አጵሎስ ወደ
አካይያ ለመሄድ ባሰበ ጊዜ ወንድሞች አሳቡን
ደገፉ ፤ በአካይያ ያሉ ወንድሞች በመልካም
ሁኔታ እንዲቀበሉትም ደብዳቤ ጻፉለት ። እዚ
ያም በደረሰ ጊዜ በእግዚአብሔር ጸጋ አማኞች
ለመሆን የበቁትን በጣም ረዳቸው ። 28 ምክንያ
ቱም ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን በቅዱሳት መጻሕ
ፍት ቃል እያስረዳ በብርቱ ክርክር አይሁዳውያ
ንን ይረታቸው ነበር ።

## ምዕራፍ 19

### ጳውሎስ በኤፌሶን

1 አጵሎስ በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ ጳው
ሎስ በላይኛው አገር አልፎ ወደ ኤፌሶን
ደረሰ ፤ እዚያ ጥቂት አማኞችን አገኘና 2 “ባመ
ናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀብላችሁ ነበ
ርን?” ሲል ጠየቃቸው ። እነርሱም “አልተቀበ
ልንም ፥ መንፈስ ቅዱስ መኖሩን እንኳ ሰምተን
አናውቅም” ሲሉ መለሱለት ።
3 ጳውሎስም “ታዲያ ምን ዐይነት ጥምቀት
ነው የተጠመቃችሁት?” አላቸው ። እነርሱም
“የዮሐንስን ጥምቀት ነው” አሉት ።
4 ጳውሎስም “የዮሐንስ ጥምቀትማ ንስሓ
ስለመግባት የተፈጸመ ነው ፤ ለሕዝቡም የተናገ
ረው ‘ከእኔ በኋላ በሚመጣው እመኑ’ እያለ
ነበር ፤ እርሱም ኢየሱስ ነው” አላቸው ።
5 ይህን በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም
ተጠመቁ ። 6 ጳውሎስ እጁን በጫነባቸውም
ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወረደና በሌላ
ቋንቋዎች ተናገሩ ፤ ትንቢትንም መናገር
ጀመሩ ። 7 ሰዎቹም በአጠቃላይ ዐሥራ ሁለት
ያህል ነበሩ ።
8 ጳውሎስ ወደ ምኩራብ ሄዶ ለሦስት ወር
ያህል ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየተከራከ
ረና ሕዝቡን እያስረዳ በድፍረት ያስተምር
ነበር ። 9 አንዳንዶች ግን እልኸኞች በመሆን የጌ
ታን መንገድ በሕዝቡ ፊት እየተሳደቡ አናም
ንም ባሉ ጊዜ ከእነርሱ ራቀ ፤ አማኞችንም ለብ
ቻቸው ወስዶ በጢራኖስ አዳራሽ በየቀኑ ያስተ
ምር ነበር ። 10 ጳውሎስ ይህን ያደረገው ለሁለት
ዓመት ያህል ነው ፤ በዚያም ጊዜ በእስያ የሚ
ኖሩ አይሁዳውያንና አረማውያን ሁሉ የጌታን
ቃል ለመስማት ቻሉ ።

### እግዚአብሔር በጳውሎስ እጅ ያሳየው ተአምር

11 እግዚአብሔር በጣም አስደናቂ የሆኑ ተአ
ምራት በጳውሎስ እጅ ያደርግ ነበር ። 12 በዚ
ህም ምክንያት የጳውሎስን አካል የነካውን ልብ
ስና መሐረብ እየወሰዱ በሽተኞቹን ሲያስነኩአ
ቸው ከበሽታቸው ይፈወሱ ነበር ፤ ርኩሳን መና
ፍስትም ይወጡላቸው ነበር ። 13 አጋንንትን ከሰ
ዎች እያስወጡ በየቦታው የሚዞሩ አንዳንድ
አይሁዳውያን “ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ
ስም እንድትወጡ እናዛችኋለን” በማለት አጋንን
ትን ከሰዎች ለማስወጣት ይሞክሩ ነበር ። 14 የአ
ይሁድ ሊቀ ካህናት የሆነ የአስቄዋ ሰባት ልጆ
ችም እንዲሁ ያደርጉ ነበር ።
15 ነገር ግን ርኩሱ መንፈስ “ኢየሱስን ዐው
ቃለሁ! ጳውሎስንም ዐውቃለሁ! እረ እናንተ
እነማን ናችሁ?” አላቸው ።
16 ርኩስ መንፈስ ያደረበትም ሰው ዘሎ በማ
ነቅ በረታባቸው ፤ ቆስለውና ራቁታቸውን
ሆነው ከቤት ሸሽተው ወጡ ። 17 ይህም ነገር
በኤፌሶን በሚኖሩት አይሁዳውያንና አረማው
ያን ዘንድ ስለተሰማ ሁሉም ፈሩ ፤ የጌታ የኢየ
ሱስም ስም እጅግ የከበረ ሆነ ። 18 ከአማኞችም
ብዙዎቹ ክፉ ሥራቸውን በግልጥ እየተናዘዙ
ይመጡ ነበር ። 19 ብዙ አስማተኞችም የአስ
ማት መጻሕፍቶቻቸውን ሰብስበው በሕዝቡ
ሁሉ ፊት አቃጠሉአቸው ፤ የመጻሕፍቱም ዋጋ
ሲተመን ኀምሳ ሺ ብር ሆኖ ተገኘ ። 20 በዚህ
ዐይነት የጌታ ቃል በጣም እየተስፋፋና እያሸ
ነፈ ይሄድ ነበር ።

### በኤፌሶን ሁከት ተነሣ

21 ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ጳውሎስ በመቄዶን
ያና በአካይያ አድርጎ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ
በመንፈሱ አስቦ “እዚያ ከደረስሁ በኋላ ወደ
ሮም መሄድ አለብኝ” አለ ። 22 ስለዚህ ከሚያገ
ለግሉት ሰዎች ሁለቱን ፤ ጢሞቴዎስንና ኤራስ
ጦስን ወደ መቄዶንያ ልኮ እርሱ ራሱ በእስያ
ለጥቂት ቀኖች ቆየ ።
23 በዚያን ጊዜ በጌታ መንገድ ምክንያት
በኤፌሶን ታላቅ ሁከት ተነሣ ። 24 አንድ ድሜጥ
ሮስ የሚባል ብር አንጥረኛ ፥ የአርጤሚስን
ቤተ መቅደስ ምስል ከብር እየሠራ ለአንጥረ
ኞች ብዙ ትርፍ ያስገኝ ነበር ። 25 ስለዚህ ይህ
ሰው እነዚህን አንጥረኞችና የእነርሱ ዐይነት
ሥራ ያላቸውን ሌሎችንም ሰዎች ሰብስቦ እን
ዲህ አላቸው ፥ “እናንተ ሰዎች! እኛ ሀብት
የምናገኘው በዚህ ሥራ እንደሆነ ታውቃላ
ችሁ ፤ 26 ይህ ጳውሎስ ‘በሰው እጅ የተሠሩ
ምስሎች አማልክት አይደሉም’ እያለ በኤፌሶን
ብቻ ሳይሆን ፥ ከጥቂት አገሮች በቀር በመላዋ

19፥4 ፦ ማቴ. 3፥11 ፤ ማር. 1፥4 ፡7-8 ፤ ሉቃ. 3፥4 ፡16 ፤ ዮሐ. 1፥26-27 ።

እስያ ምን ያህል ብዙ ሕዝብ እንዳግባባና እንዳ
ሳመነ እናንተ ራሳችሁ ያያችሁትና የሰማችሁት
ነው ። 27በዚህ ዐይነት ይህ የእኛ ሥራ መናቁ
ነው ፤ ይህም ብቻ ሳይሆን በእስያና በመላው
ዓለም ሰው ሁሉ የሚያመልካት የታላቂቱ አም
ላክ የአርጤሚስ ቤተ መቅደስ ከንቱ ሆኖ መቅ
ረቱ ነው ፤ የእርስዋም ታላቅነት መሻሩ
ነው ።”

28ሰዎቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ተቈጥተው
“የኤፌሶን አርጤሚስ ታላቅ ናት!” እያሉ
ጮኹ ። 29ከተማዋም በሙሉ ታወከች ፤ ሕዝ
ቡም የመቄዶንያ ተወላጆች የሆኑትን ሁለቱን
የጳውሎስ ጓደኞች ፥ ጋይዮስንና አርስጥሮኮስን
ይዘው እየጐተቱ ወደ ሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታ
ሮጡ ። 30ጳውሎስ ወደ ሕዝቡ ለመሄድ ፈልጎ
ነበር ፤ አማኞች ግን እንዳይሄድ ከለከሉት ።
31ከእስያ አገር ባለሥልጣኖችም ወዳጆቹ የሆኑ
አንዳንዶቹ ወደ ጳውሎስ ሰው ልከው “ወደ
ሕዝብ መሰብሰቢያው ቦታ ሄደህ እንዳትታይ”
ሲሉ ለመኑት ። 32በሕዝቡ መካከል ታላቅ
ሁከት ስለነበር አብዛኞዎቹ ለምን እንደተሰበ
ሰቡ እንኳ አያውቁም ነበር ፤ በዚህ ምክንያት
አንዱ አንድ ነገር እያለ ሲጮኽ ፥ ሌላው ደግሞ
ሌላ ነገር እያለ ይጮኽ ነበር ። 33አንዳንድ አይ
ሁዳውያን እስክንድር የተባለውን ሰው ገፋፍ
ተው ወደ ፊት አቀረቡት ፤ ከሕዝቡም መካከል
አንዳንዶቹ በደንብ እንዲከራከርላቸው መከ
ሩት ፤ እስክንድርም ሕዝቡ ጸጥ እንዲል በእጁ
ጠቀሰና የመከላከያ ንግግር ለማድረግ ተዘጋጀ ።
34ነገር ግን እስክንድር አይሁዳዊ መሆኑን
ሕዝቡ ሁሉ ባወቁ ጊዜ “የኤፌሶን አርጤሚስ
ታላቅ ናት!” እያሉ ሁለት ሰዓት ያህል ሁሉም
በአንድ ድምፅ ጮኹ ።

35በመጨረሻ የከተማይቱ ዋና ጸሐፊ ሕዝ
ቡን ዝም አሰኝና እንዲህ አለ ፥ “የኤፌሶን
ሰዎች ሆይ! የኤፌሶን ከተማ ነዋሪዎች የታላቂ
ቱን አርጤሚስን ቤተ መቅደስና ከሰማይ የወረ
ደውን ምስልዋን እንደሚጠብቁ በሁሉም ዘንድ
የታወቀ ነው ። 36ይህን የሚክድ ማንም ስለሌለ
ጸጥ እንድትሉና በችኮላ ክፉ ነገር ከማድረግ
እንድትጠነቀቁ ይገባል ። 37ቤተ መቅደስን ያል
ዘረፉትንና በአምላካችን ላይ የስድብ ቃል ያል
ተናገሩትን ሰዎች ወደዚህ ይዛችሁ መጥ
ታችኋል ። 38ድሜጥሮስና ከእርሱ ጋር ያሉት
አንጥረኞች የሚከሱት ሰው ካለ ፥ ፍርድ የሚሰ
ጥባቸው ቀኖች አሉ ፤ ባለሥልጣኖችም አሉ ፤
እዚያ ይሟገቱ ። 39ሌላ የምትፈልጉት ነገር
ካለ ግን በሕጋዊ ሸንጎ ይታያል ። 40አለበለዚያ
ዛሬ በተደረገው ነገር ፥ ‘ሁከት አስነሥተዋል’
ተብለን እንዳንከሰስ ያስፈራል ፤ ‘ይህ ብጥብጥ
በምን ምክንያት ተነሣ’ ተብለን ብንጠየቅ ፥
የምንሰጠው መልስ የለንም” 41ይህንንም ብሎ
የተሰበሰቡት ሰዎች እንዲበተኑ አደረገ ።

## ምዕራፍ 20

### የጳውሎስ ጕዞ ወደ መቄዶንያና ግሪክ አገር

1ሁከቱ ጸጥ ካለ በኋላ ጳውሎስ አማኞቹን
በአንድነት አስጠርቶ በምክር ቃል አጽናና
ቸው ፤ ተሰናብቶአቸውም ወደ መቄዶንያ ሄደ ።
2በእነዚያ በሚያልፍባቸው ስፍራዎች አማኞ
ችን በብዙ ምክር እያበረታታ ወደ ግሪክ አገር
ሄደ ። 3እዚያም ሦስት ወር ቈየ ፤ ከዚህ በኋላ
በመርከብ ወደ ሶርያ ለመሄድ አሰበ ፤ ግን አይ
ሁዳውያን በእርሱ ላይ ሤራ ማድረጋቸውን
ባወቀ ጊዜ በመቄዶንያ በኩል አልፎ ለመሄድ
ወሰነ ።

4የጳጥሮስ ልጅ ሱሲ ጳጥሮስ ከቤርያ ፥ አርስ
ጥሮኮስና ሲኮንዱስ ከተሰሎንቄ ፥ ጋይዮስ ከደ
ርቤ ፥ ቲኪቆስና ጥሮፊሞስ ከእስያ ፥ ጢሞቴዎ
ስም አብረውት ሄዱ ። 5እነርሱ ቀድመውን
ሄደው በጢሮአዳ ቈዩን ። 6እኛ ግን ከቂጣ
በዓል በኋላ ከፊልጵስዩስ በመርከብ ተሳፍረን
በአምስት ቀን እነርሱ ወዳሉበት ወደ ጢሮአዳ
ደረስንና እዚያ ሰባት ቀን አሳለፍን ።

### የጳውሎስ መጨረሻ ጕብኝት በጢሮአዳ

7በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን[7*] እንጀራ ቈርሶ
ለመብላት በአንድነት ተሰበሰብን ፤ ጳውሎስ
በማግሥቱ መሄድ ስለነበረበት ለተሰበሰቡት
ሰዎች ይናገር ነበር ፤ ንግግሩንም እስከ እኩለ
ሌሊት አስረዘመ ። 8እኛ በተሰበሰብንበት ፎቅ
ብዙ መብራት ነበር ። 9ኤውጢኮስ የተባለ
አንድ ወጣት በመስኮት ላይ ተቀምጦ ነበር ፤
ጳውሎስ ንግግሩን በማስረዘሙ ወጣቱ ከባድ እን
ቅልፍ ያዘው ፤ እንቅልፍ ስላሸነፈውም ከሦስተ
ኛው ፎቅ ወደ ታች ወደቀ ፤ ሰዎች ባነሡት
ጊዜ ሞቶ አገኙት ። 10ነገር ግን ጳውሎስ ወርዶ
ወደ ልጁ ጐንበስ በማለት አቀፈውና “ገና በሕ
ይወት አለ ፤ አትደንግጡ” አለ ። 11ጳውሎስ
ወደ ፎቅ ተመልሶ ወጣና እንጀራ ቈርሶ ከአማ
ኞች ጋር በላ ። እስኪነጋም ድረስ ከሰዎቹ ጋር
ሲነጋገር ከቈየ በኋላ ሄደ ። 12ሰዎቹም የዳነ
ውን ወጣት ወደ ቤት ወሰዱት ፥ ደስ ብሎአ
ቸው ተጽናኑ ።

### ጳውሎስ ከጢሮአዳ ወደ ሚሊጢ ሄደ

13ጳውሎስን ለማሳፈር ስለ አሰብን እኛ ቀድ
መን በመርከብ ወደ አሶስ ሄድን ፤ ይህንንም
ያደረግነው ጳውሎስ እስከ አሶስ ድረስ በእግሩ
ለመሄድ ስለወሰነና እንዲህ እንድናደርግ ስለ
አዘዘን ነው ። 14ከእርሱ ጋር በአሶስ በተገናኘን

[7*] 20፥7 በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ፦ ቅዳሜ ማታ ለእሑድ አጥቢያ ማለቱ ነው ።



ጊዜ በመርከብ አሳፍረነው ወደ ሚጢሊኒ አብ
ረን ሄድን ። 15በማግሥቱ ከዚያ ተነሥተን በኪ
ዮስ ፊት ለፊት ወዳለው ስፍራ ደረስን ፤ በሚቀ
ጥለውም ቀን ወደ ሳሞስ ተሻገርንና በማግሥቱ
ወደ ሚሊጢ ደረስን ። 16ጳውሎስ በእስያ ጊዜ
እንዳያባክን ብሎ ኤፌሶንን አልፎ ለመሄድ
ፈለገ ፤ ምክንያቱም የአይሁድ ፋሲካ ባለፈ በኀ
ምሳኛው ቀን በሚከበረው በጰንጠቆስጤ በዓል
በተቻለ መጠን በኢየሩሳሌም ለመገኘት አስቦ
ስለነበር ነው ።

### ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች ያደረገው የመሰነባበቻ ንግግር

17ጳውሎስ ከሚሊጢን ወደ ኤፌሶን ሰው
ልኮ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን አስጠራ ፤
18ወደ እርሱ በመጡም ጊዜ እንዲህ አላቸው ፥
“ወደ እስያ ከገባሁበት ቀን ጀምሮ ዘወትር ከእ
ናንተ ጋር እንዴት እንደኖርሁ እናንተ ታውቃ
ላችሁ ፤ 19በአይሁዳውያን ሤራ ምክንያት
መከራ ቢደርስብኝም እንኳ በፍጹም ትሕትናና
በእንባ ጌታን አገለግላለሁ ። 20በአደባባይም ሆነ
በየቤታችሁ ሳስተምራችሁ የሚጠቅማችሁን
ሁሉ ነገርሁአችሁ እንጂ ምንም ነገር አላስቀረ
ሁባችሁም ። 21አይሁዳውያንም ሆኑ አረማው
ያን ንስሓ ገብተው ወደ እግዚአብሔር እንዲመ
ለሱና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ
አስጠነቀቅሁአቸው ። 22አሁንም እነሆ ስደርስ
ምን እንደሚደርስብኝ ሳላውቅ ፥ በመንፈስ
ቅዱስ ታዝዤ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዴ ነው ።
23ይሁን እንጂ እስራትና ችግር እንደሚገጥመኝ
በየከተማው መንፈስ ቅዱስ ነግሮኛል ። 24እኔ
ግን አገልግሎቴን እስከፈጽምና ጌታ ኢየሱስ
የሰጠኝን ሥራ እስካከናውን ድረስ ፥ ለገዛ ሕይ
ወቴ እንኳ አልሳሳም ፤ አገልግሎቴም የእግዚአ
ብሔርን የጸጋ ወንጌል ማብሠር ነው ።

25“እስከ አሁን በእናንተ ሁሉ መካከል እየ
ተዘዋወርሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት እሰ
ብክ ነበር ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ግን ከእናንተ
ማንም ከቶ ፊቴን እንደማያይ ዐውቃለሁ ።
26ስለዚህ ከእናንተ አንድ እንኳ ቢጠፋ ኀላፊ
ነት እንደሌለብኝ በዛሬው ቀን አስገነዝባችኋ
ለሁ ። 27ምክንያቱም የእግዚአብሔርን አሳብ
ሁሉ ነገርሁአችሁ እንጂ ምንም ያስቀረሁባችሁ
ነገር የለም ። 28መንፈስ ቅዱስ እናንተን የመን
ጋው ጠባቂ አድርጎ ሾሞአችኋል ፤ እንግዲህ
ለራሳችሁና ለመንጋው ተጠንቀቁ ፤ ጌታ በገዛ
ደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ ። 29እኔ
ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ እንደ
ተኵላ ጨካኞች የሆኑ ሰዎች እንደሚገቡባችሁ
ዐውቃለሁ ። 30እንዲሁም አንዳንድ ሰዎች ከመ
ካከላችሁ ተነሥተው ጠማማ ትምህርት በማስተ
ማር ብዙ አማኞችን ወደ እነርሱ ይስባሉ ።
31ስለዚህ እያንዳንዳችሁን ሦስት ዓመት ሌሊ
ትና ቀን እንባዬን እያፈሰስሁ እንደመከርሁአ
ችሁ እያስታወሳችሁ ተጠንቀቁ ።

32“አሁንም ለእግዚአብሔር ፥ ሊያንጻችሁና
በቅዱሳንም መካከል ርስት ሊሰጣችሁ ለሚች
ለው ለጸጋው ቃልም ዐደራ ሰጥቻችኋለሁ ።
33እኔ የማንንም ብር ወይም ልብስ አልተመኘ
ሁም ። 34በገዛ እጆቼ እየሠራሁ ራሴንም ሆነ
ጓደኞቼን እረዳ እንደነበር እናንተ ራሳችሁ
ታውቃላችሁ ። 35‘ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ
የተባረከ ነው’ የሚለውን የጌታ ኢየሱስን ቃል
በማስታወስ ፥ በእጃችን እየሠራን ደካሞችን
መርዳት እንደሚገባን በብዙ መንገድ አሳይቻ
ለሁ ።”

36ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ከሁሉም ጋር ተንበ
ርክኮ ጸለየ ። 37ሁሉም አለቀሱና ጳውሎስን
አቅፈው ሳሙት ። 38ይልቁንም በጣም ያዘኑት
“ከእንግዲህ ወዲህ ፊቴን አታዩም” ብሎአቸው
ስለነበር ነው ። እስከ መርከብ ድረስም ሸኙት ።

## ምዕራፍ 21

### ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ

1ከእነርሱ ከተለየን በኋላ በመርከብ ተሳፈር
ንና በቀጥታ ቆስ ወደምትባል ደሴት ሄድን ፤
በማግሥቱም ወደ ሩድ ደሴት ደረስን ፤ ከዚያም
ወደ ጳጥራ ከተማ ሄድን ። 2እዚያም ወደ ፊንቄ
አገር የምትሄድ መርከብ አገኘንና በእርስዋ ተሳ
ፍረን ጕዞአችንን ቀጠልን ። 3የቆጵሮስን ደሴት
በስተግራችን ትተን ወደ ሶርያ አገር ተጓዝንና
ወደ ጢሮስ ወደብ ሄድን ፤ ምክንያቱም መርከ
ቢቱ ጭነትዋን እዚያ ማራገፍ ነበረባት ።
4እዚያ አማኞችን ፈልገን አገኘንና ከእነርሱ
ጋር ሰባት ቀን ቈየን ። እነርሱም በመንፈስ
ቅዱስ ተመርተው ጳውሎስን “ወደ ኢየሩሳሌም
አትሂድ” ብለው ነገሩት ። 5እዚያ የምንቈይበት
ጊዜ ሲያልቅ ተለይተናቸው ጕዞአችንን ቀጠ
ልን ፤ ሁሉም ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው
ጋር ሆነው እስከ ከተማው ውጪ ድረስ ሸኙን ፤
በባሕሩም ዳር ተንበርክከን ከጸለይን በኋላ ተሰነ
ባበትን ። 6ከዚህ በኋላ እኛ በመርከብ ስንሳፈር
እነርሱ ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

7ከጢሮስ ተነሥተን የባሕር ጕዞአችንን
ከጨረስን በኋላ ወደ ጴጤሌማይስ ደረስን ፤
እዚያ ከአማኞች ጋር ተገናኝተን ሰላምታ ከተለ
ዋወጥን በኋላ ከእነርሱ ጋር አንድ ቀን አሳለ
ፍን ። 8በማግሥቱ ከዚያ ወጥተን ወደ ቂሳርያ
ሄድን ፤ እዚያ ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ ወደ
ሆነው ወደ ወንጌላዊው ፊልጶስ ቤት ገባንና
ከእርሱ ጋር ተቀመጥን ። 9እርሱ ትንቢት የመ
ናገር ስጦታ ያላቸው አራት ያላገቡ ሴቶች

20፥24 ፦ 2ጢሞ. 4፥7 ። 21፥8 ፦ ሐ.ሥ. 6፥5 ፤ 8፥5 ።

ልጆች ነበሩት ። 10 ለብዙ ቀኖች እዚያ በተቀ
መጥንበት ጊዜ አጋቦስ የሚባል ነቢይ ከይሁዳ
አገር መጣ ። 11 ይህ ነቢይ ወደ እኛ ቀረበ ፤ የጳ
ውሎስን መታጠቂያ ወስዶ የገዛ እግሮቹን አስ
ረና "መንፈስ ቅዱስ የዚህን መታጠቂያ ባለቤት
በኢየሩሳሌም ያሉ አይሁዳውያን እንደዚህ አስ
ረው ለአረማውያን አሳልፈው ይሰጡታል
ይላል" አለ ።
12 ይህንን በሰማን ጊዜ እኛም እዚያ የነበሩ
ሰዎችም ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ
ለመንነው ። 13 ጳውሎስ ግን "እንደዚህ እያለቀ
ሳችሁ ስለምን ልቤን በሐዘን ትሰብሩታላችሁ?
እኔ ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም በኢየሩሳሌም ለመታ
ሰር ብቻ ሳይሆን ለመሞትም ዝግጁ ነኝ" ሲል
መለሰ ።
14 ምክራችንን አልቀበልም ባለን ጊዜ "እን
ግዲህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን" ብለን
ተውነው ።
15 እዚያ ጥቂት ቀኖች ከቆየን በኋላ ዕቃች
ንን አዘጋጅተን ወደ ኢየሩሳሌም ሄድን ። 16 በቂ
ሳርያ የነበሩ አንዳንድ አማኞችም አብረውን
መጡ ፤ እነርሱም በምናሶን ቤት እንድንቀመጥ
ወደ ምናሶን መሩን ። ይህ ሰው ቀደም ብሎ
ያመነ የቆጵሮስ ተወላጅ ነበር ።

ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ያዕቆብን ጐበኘ

17 ኢየሩሳሌም በደረስን ጊዜ አማኞች በደ
ስታ ተቀበሉን ። 18 በማግሥቱ ጳውሎስ ከእኛ
ጋር ወደ ያዕቆብ ሄደ ፤ የቤተ ክርስቲያን ሽማግ
ሌዎች እዚያ ነበሩ ። 19 ጳውሎስ ለሁሉም ሰላ
ምታ ከሰጠ በኋላ በእርሱ አማካይነት እግዚአብ
ሔር በአረማውያን መካከል ያደረገውን ሁሉ
አንድ በአንድ ተረከላቸው ። 20 ይህን በሰሙ
ጊዜ ሁሉም እግዚአብሔርን አመሰገኑ ፤ ጳውሎ
ስንም እንዲህ አሉት ፡ "ወንድም ሆይ! በብዙ
ሺ የሚቈጠሩ አማኞች በአይሁዳውያን መካከል
እንዳሉና ሁሉም ለሙሴ ሕግ ቀናተኞች እንደ
ሆኑ ታውቃለህ ፤ 21 አንተ በአረማውያን መካ
ከል የሚኖሩትን አይሁዳውያን ሁሉ 'ልጆቻች
ሁን እትግረዙ ወይም ሥርዓቶችን አትፈጽሙ'
እያልክ በማስተማር የሙሴን ሕግ እንዲሽሩ
ታደርጋለህ እየተባለ የሚወራውን ሰምተዋል ።
22 እንግዲህ ምን ማድረግ ይሻላል? መምጣት
ህን በእርግጥ ይሰማሉ ፤ 23 ስለዚህ እኛ የምንል
ህን አድርግ ፤ በእኛ መካከል ስእለት ያለባቸው
አራት ሰዎች አሉ ። 24 እነርሱን ውሰድና ከእነ
ርሱ ጋር ሆነህ ራስህን አንጻ ፤ ጠጕራቸውንም
እንዲላጩ ለቤተ መቅደስ የሚሰጠውን የመባ
ገንዘብ ክፈልላቸው ፤ ይህን ብታደርግ በአንተ
ላይ የተወራው ሁሉ ከንቱ መሆኑንና አንተም
ራስህ የሙሴን ሕግ ፈጻሚ መሆንህን ሁሉም
ያውቃሉ ። 25 አማኞች ስለሆኑት አረማውያን
ግን 'ለጣዖት በመሠዋቱ ምክንያት የረከሰ
ምግብ አትብሉ ፤ ደምም አትብሉ ፤ ሳይታረድና
ደሙ ሳይፈስ ታንቆ የሞተ እንስሳ አትብሉ ፤
ከዝሙት ራቁ' የሚለውን ውሳኔ የያዘ ደብዳቤ
ጽፈን ልከንላቸዋል ።"
26 ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ሰዎቹን ወሰደና በማ
ግሥቱ ከእነርሱ ጋር ሰውነቱን አነጻ ፤ የሚነጹ
ባቸው ቀኖች ምን ያህል እንደሆኑና ስለያንዳ
ንዱ የሚሰጠው የመባ ገንዘብ የሚከፈልበት
ጊዜ መቼ እንደሚሆን ለማስታወቅ ወደ ቤተ
መቅደስ ገባ ።

ጳውሎስ በቤተ መቅደስ ተያዘ

27 ሰባቱ ቀን ሊፈጸም ሲቃረብ ከእስያ
የመጡ አይሁዳውያን ጳውሎስን በቤተ መቅደስ
በማየታቸው ሕዝቡን ሁሉ አሳድመው ያዙት ፤
28 "የእስራኤል ሰዎች ሆይ! እርዱን ፤ ሕዝባች
ንንና ሕጋችንን ፡ ይህንንም ስፍራ እየተሳደበ
በየአገሩ ያለውን ሕዝብ ሁሉ የሚያስተምር
ይህ ሰው ነው ፤ ይህም አልበቃ ብሎት አረማው
ያንን ወደ ቤተ መቅደስ በማስገባት ይህን የተቀ
ደሰ ስፍራ አርክሶአል" እያሉ ጮኹ ። 29 ይህን
ንም ያሉበት ምክንያት ከዚህ ቀደም የኤፌሶኑን
ተወላጅ ጥሮፊሞስን ከእርሱ ጋር በከተማ አይተ
ውት ስለነበር እርሱን ጳውሎስ ወደ ቤተ መቅ
ደስ ይዞት የገባ መስሎአቸው ነበር ።
30 ከተማዋ በሙሉ ታወከች ፤ ሕዝቡም ሁሉ
እየሮጠ በአንድነት መጡና ጳውሎስን ይዘው
እየጐተቱ ከቤተ መቅደስ አወጡት ፤ የቤተ
መቅደሱ በሮችም ወዲያውኑ ተዘጉ ። 31 ሰዎቹ
ጳውሎስን ሊገድሉት በፈለጉ ጊዜ "የኢየሩሳ
ሌም ከተማ በሙሉ ታውካለች" የሚል መልእ
ክት ለሮማውያኑ ጦር አዛዥ ደረሰ ። 32 ስለዚህ
እርሱ ወታደሮችንና የመቶ አለቆችን አስከትሎ
በፍጥነት እየሮጠ ወደ ሰዎቹ ሄደ ። ሰዎቹም
አዛዡንና ወታደሮቹን ባዩ ጊዜ ጳውሎስን መደ
ብደብ ተዉ ። 33 አዛዡም ቀርቦ ጳውሎስን ያዘ
ውና በሁለት ሰንሰለት እንዲታሰር አዘዘ ። ከዚህ
በኋላ ማን መሆኑንና ምን እንዳደረገ ለማወቅ
ፈልጎ ጠየቀ ። 34 ሕዝቡም አንዳንዶቹ አንድ
ነገር ሲሉ ፡ ሌሎች ሌላ ነገር ይሉ ነበር ፤
አዛዡ ከሕዝቡ ጩኸት የተነሣ እርግጠኛውን
ነገር ለማወቅ ስላልቻለ ጳውሎስን ወደ ወታደ
ሮቹ ሰፈር እንዲወስዱት አዘዘ ። 35 ጳውሎስ
ወደ ደረጃው በደረሰ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ በብርቱ
ቍጣ ተነሣሥቶ አደጋ ሊያደርስበት በመፈለጉ
ወታደሮቹ ተሸክመውት ሄዱ ። 36 ሕዝቡም
"ግደሉት" እያሉ በመጮኽ ይከተሉት ነበር ።

21፡10 ፦ ሐ.ሥ. 11፡28 ። 21፡23-24 ፦ ዘኍ. 6፡13-21 ። 21፡25 ፦ ሐ.ሥ. 15፡29 ። 21፡29 ፦ ሐ.ሥ. 20፡4 ።



ጳውሎስ የመከላከያ ንግግር አደረገ

37 ወታደሮች ወደ ሰፈራቸው ሊያስገቡት
በቀረቡ ጊዜ ጳውሎስ የጦር አዛዡን "አንድ
ነገር እንድነግርህ ትፈቅድልኛለህን?" አለው ።
አዛዡም "የግሪክ ቋንቋ ታውቃለህን? 38 ታዲያ
አሁን በቅርቡ ብጥብጥ አስነሥቶና አራት ሺ
ነፍሰ ገዳዮች ይዞ ወደ በረሓ የሸሸው ግብጻ
ዊው አንተ አይደለህምን?" አለ ።
39 ጳውሎስም "እኔ በኪልቅያ በምትገኘውና
ዝነኛ በሆነችው በጠርሴስ ከተማ የተወለድሁ
አይሁዳዊ ነኝ ፤ እባክህ ለሕዝቡ እንድናገር
ፍቀድልኝ" አለው ።
40 እንዲናገር በፈቀደለት ጊዜ ጳውሎስ በደ
ረጃ ላይ ቆሞ ሕዝቡ ዝም እንዲል በእጁ
ጠቀሰ ፤ ሕዝቡ ጸጥ ባለ ጊዜ በዕብራይስጥ ቋንቋ
እንዲህ ሲል መናገር ጀመረ ፤

## ምዕራፍ 22

1 "ወንድሞቼና አባቶቼ ሆይ እነሆ አሁን
የማቀርብላችሁን መከላከያ ስሙኝ ፤" 2 በዕብራ
ይስጥ ቋንቋ ሲናገር በሰሙ ጊዜ በይበልጥ ጸጥ
አሉ ፤ ጳውሎስም ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ
አለ ፦
3 "እኔ በኪልቅያ በምትገኘው በጠርሴስ
ከተማ የተወለድሁ አይሁዳዊ ነኝ ፤ ያደግሁት
ግን በዚህች በኢየሩሳሌም ከተማ ነው ። አስተማ
ሪዬም ገማልያል ነበር ፤ የአባቶችን ሕግ ጠን
ቅቄ የተማርሁና ልክ ዛሬ እናንተ እንደምታደር
ጉት እግዚአብሔርን በመንፈሳዊ ቅንአት የማገለ
ግል ነበርሁ ። 4 ይህንንም መንገድ የሚከተሉ
ትን ሁሉ እስከ ሞት የማሳድድ ሰው ነበርሁ ፤
ወንዶችንና ሴቶችን እያሰርሁ ወደ ወህኒ ቤት
እንዲገቡ የማደርግ ነበርሁ ። 5 ይህም እውነት
መሆኑን ሊቀ ካህናቱና የሽማግሌዎች ሸንጎ
በሙሉ ይመሰክሩልኛል ። እንዲያውም በደማ
ስቆ ያሉትን እነዚህን ሰዎች አስሬ ወደ ኢየሩሳ
ሌም ለማምጣትና ለማስቀጣት የሚያስችለኝን
በደማስቆ ወደሚገኙት ወገኖቻቸው የጻፉትን
ደብዳቤ የተቀበልሁት ከእነርሱ ነው ።

ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ እንዴት
እንደተመለሰ ተረከ
(ሐ.ሥ. 9፡1-19፤ 26፡12-18)

6 "እኔ ወደ ደማስቆ ስሄድና ወደ ከተማው
ስቀርብ እኩለ ቀን ላይ በድንገት ታላቅ ብርሃን
ከሰማይ በዙሪያዬ አንጸባረቀ ። 7 በዚያን ጊዜ
በመሬት ላይ ወደቅሁ ፤ 'ሳውል! ሳውል!
ለምን ታሳድደኛለህ?' የሚል ድምፅ ሰማሁ ።
8 እኔም 'ጌታ ሆይ! አንተ ማን ነህ?' አልሁ ፤
እርሱም 'እኔ አንተ የምታሳድደኝ የናዝሬቱ
ኢየሱስ ነኝ' አለኝ ። 9 ከእኔ ጋር የነበሩት
ሰዎች ብርሃኑን አዩ እንጂ እርሱ ሲያነጋግረኝ
ድምፁን አልሰሙም ። 10 እኔም 'ጌታ ሆይ!
ምን ላድርግ?' አልሁ ። ጌታም 'ተነሥተህ ወደ
ደማስቆ ሂድ ፤ ልታደርገው የታቀደልህ ነገር
ሁሉ እዚያ ይነገርሃል' አለኝ ። 11 ከብርሃኑ ግን
ጸባረቅ የተነሣ ማየት ስላልቻልሁ አብረውኝ
የነበሩት ሰዎች እጄን ይዘው እየመሩኝ ወደ
ደማስቆ አደረሱኝ ።
12 "እዚያ ሐናንያ የሚባል አንድ ሰው
ነበረ ፤ ይህ ሰው በደማስቆ የሚኖሩ አይሁዳው
ያን ሁሉ የሚያመሰግኑት ፡ ሕግ አክባሪና መን
ፈሳዊ ሰው ነበረ ። 13 እርሱ ወደ እኔ መጥቶ
አጠገቤ ቆመና ፡ 'ወንድሜ ሳውል ሆይ! ዐይ
ንህ እንደገና ይይልህ' አለኝ ፤ በዚያኑ ቅጽበት
ዐይኔ አየ ፤ እርሱንም ተመለከትሁት ። 14 እር
ሱም እንዲህ አለኝ ፡ 'የአባቶቻችን አምላክ
ፈቃዱን እንድታውቅ ፡ ጻድቁን እንድታይና
ድምፁንም እንድትሰማ አስቀድሞ መርጦሃል ።
15 ይህንንም ያደረገው ስላየኸውና ስለሰማኸው
በሰው ሁሉ ፊት የእርሱ ምስክር እንድትሆን
ነው ። 16 ታዲያ አሁን ለምን ትዘገያለህ? ተነ
ሥና የእርሱን ስም በመጥራት ተጠመቅ ፤ ከኃ
ጢአትህም ታጠብ ።'
17 "ከዚህ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሼ
በቤተ መቅደስ በምጸልይበት ጊዜ በተመስጦ
ራእይ አየሁ ። 18 ጌታም ተገልጦልኝ 'አንተ ስለ
እኔ የምትሰጠውን ምስክርነት ስለማይቀበሉ
ሳትዘገይ በፍጥነት ከኢየሩሳሌም ውጣ!'
አለኝ ፤ 19 እኔም እንዲህ አልሁ ፡ 'ጌታ ሆይ!
በየምኵራቡ እየሄድሁ በአንተ ያመኑትን ሁሉ
እንዳሰርሁና እንደደበደብሁ እነርሱ ራሳቸው
ያውቃሉ ። 20 የአንተ ምስክር የነበረው እስጢፋ
ኖስ በተገደለ ጊዜ ፡ እኔም ራሴ በገዳዮቹ አጠ
ገብ ቆሜ ከእነርሱ ጋር በነገሩ ተስማምቼ
ነበር ፤ ልብሳቸውንም እጠብቅ ነበር ፤'
21 ጌታም 'በሩቅ ወዳሉ አረማውያን ስለምልክህ
ተነሥና ሂድ' አለኝ ።"

ጳውሎስ የሮም ዜጋ መሆኑን ገለጠ

22 እስከዚህ ድረስ ሕዝቡ ሁሉ የጳውሎስን
ንግግር ያዳምጡ ነበር ፤ ከዚህ በኋላ ድምፃቸ
ውን ከፍ አድርገው "እንዲህ ዐይነቱ ሰው ከም
ድር ላይ ይወገድ! እንዲህ ዐይነቱ ሰው በሕይ
ወት መኖር አይገባውም!" እያሉ ጮኹ ።
23 እነርሱ እየጮኹ ልብሳቸውን ያውለበልቡና
ዐፈር ወደ ሰማይ ይበትኑ ነበር ። 24 አዛዡ ይህን
ባየ ጊዜ ጳውሎስን ወደ ወታደሮች ሰፈር እንዲ
ያስገቡት አዘዘ ፤ ሕዝቡ በእርሱ ላይ ስለምን
ይህን ያህል እንደሚጮኹ ለማወቅም እየተገ
ረፈ እንዲመረመር አዘዘ ። 25 ነገር ግን በጠፍር

22፡3 ፦ ሐ.ሥ. 5፡34-39 ። 22፡4-5 ፦ ሐ.ሥ. 8፡3 ፤ 26፡9-11 ። 22፡20 ፦ ሐ.ሥ. 7፡58 ።

ወጥረው ሊገርፉት ሲዘጋጁ፥ ጳውሎስ አጠገቡ
የቆመውን የመቶ አለቃ “የሮም ዜግነት ያለ
ውን ሰው ያለ ፍርድ ልትገርፉት ተፈቅዶላችኋ
ልን?” አለው።
26 የመቶ አለቃው ይህን በሰማ ጊዜ ወደ
አዛዡ ሄደና “ምን ልታደርግ ነው? ይህ ሰው
እኮ የሮም ዜጋ ነው” አለው።
27 ስለዚህ አዛዡ ወደ ጳውሎስ ቀረብ አለና
“እስቲ ንገረኝ፤ አንተ የሮም ዜጋ ነህን?”
አለው፤ እርሱም “አዎ ነኝ” አለ።
28 አዛዡም “እኔ ይህን ዜግነት የገዛሁት
በብዙ ገንዘብ ነው” አለ፤ ጳውሎስም “እኔ ግን
በሮም ዜግነት ተወልጃለሁ” አለ።
29 ስለዚህ እነዚያ ሊመረምሩት ተዘጋጅተው
የነበሩት ሰዎች ወዲያውኑ ከእርሱ ራቁ፤ አዛ
ዡም የሮም ዜጋ የሆነውን ሰው በሰንሰለት ማሰ
ሩን በተገነዘበ ጊዜ ፈራ።

ጳውሎስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቀረበ

30 በማግሥቱ አዛዡ፥ አይሁዳውያን ጳውሎ
ስን የከሰሱበት ትክክለኛ ምክንያት ምን እንደ
ሆነ ለማወቅ ፈለገ፤ የካህናት አለቆችና የሸን
ጎው አባሎች በሙሉ እንዲሰበሰቡ አዘዘ፤ ጳው
ሎስንም ከእስራቱ ፈትቶ ወሰደና በፊታቸው
አቀረበው።

## ምዕራፍ 23

1 ጳውሎስም ሸንጎውን ትኩር ብሎ ተመለከ
ተና “ወንድሞቼ ሆይ! እስከ ዛሬ ድረስ ሁል
ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት የኖርሁት በመልካም
ኅሊና ነው” አለ። 2 ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ ግን
ጳውሎስን አፉን እንዲመቱት በጳውሎስ አጠ
ገብ የቆሙትን ሰዎች አዘዘ። 3 በዚህ ጊዜ ጳው
ሎስ ሐናንያን “አንተ በኖራ የተለሰንህ ግድ
ግዳ! አንተንም እግዚአብሔር ይመታሃል!
በሕግ መሠረት ልትፈርድ ተቀምጠህ ሳለ ያለ
ሕግ እንዲመቱኝ ታዛለህን?”
4 እዚያ የነበሩ ሰዎች ጳውሎስን “የእግዚአ
ብሔርን ሊቀ ካህናት ትሳደባለህን?” አሉት።
5 ጳውሎስም “ወንድሞቼ ሆይ! ሊቀ ካህ
ናት መሆኑን አላወቅሁም ነበር፤ ምክንያቱም
‘በሕዝብህ አለቃ ላይ ክፉ ቃል አትናገር’
የሚል ተጽፎአል” አለ።
6 ጳውሎስ እዚያ ከነበሩት ሰዎች፥ እኩሌ
ቶቹ ፈሪሳውያን መሆናቸውን ዐውቆ “ወንድ
ሞቼ ሆይ እኔ ከፈሪሳዊ የተወለድሁ ፈሪሳዊ
ነኝ፤ እነሆ አሁን በፍርድ ፊት የቀረብሁት
ሙታን እንደሚነሡ ተስፋ በማድረጌ ነው”
ሲል ድምፁን ከፍ አድርጎ በሸንጎው መካከል
ተናገረ።
7 ጳውሎስ ይህን በተናገረ ጊዜ በፈሪሳውያንና
በሰዱቃውያን መካከል ጠብ ተነሥቶ ሸንጎው
ለሁለት ተከፈለ። 8 ምክንያቱም ሰዱቃውያን
“ትንሣኤ የለም፤ መላእክትም የሉም፤ መንፈ
ስም የለም” ሲሉ፥ ፈሪሳውያን ግን “እነዚህ
ሁሉ አሉ” ብለው ያምናሉ። 9 በዚህ ጊዜ
ታላቅ ሁካታ ሆነ፤ ከፈሪሳውያን ወገን የሆኑ
አንዳንድ የሙሴ ሕግ መምህራንም ተነሡና
“እኛ በዚህ ሰው ላይ ምንም ክፉ ነገር አላገኘ
ንበትም፤ መንፈስ ወይም መልአክ ተናግሮት
ይሆናል፤ እኛ ምን እናውቃለን?” በማለት ተከ
ራከሩ።
10 ጠቡ እየከረረ ስለሄደ ሰዎቹ ጳውሎስን
እንዳይቦጫጭቁት ፈርቶ አዛዡ “ውረዱና ጳው
ሎስን ከሰዎቹ መካከል ነጥቃችሁ አምጡ፤
ወደ ጦሩ ሰፈርም ውሰዱት!” በማለት ወታደር
ቹን አዘዘ።
11 በማግሥቱ ሌሊት ጌታ በጳውሎስ አጠገብ
ቆሞ “አይዞህ! በኢየሩሳሌም፥ እንደመሰከርህ
ልኝ እንዲሁም በሮም ልትመሰክርልኝ ይገባ
ሃል” አለው።

ጳውሎስን ለመግደል የተደረገ ሤራ

12 በነጋ ጊዜ አይሁዳውያን ተሰበሰቡና
“ጳውሎስን ሳንገድል እህል አንበላም፥ ውሃም
አንጠጣም” ብለው ተማማሉ። 13 በዚህ ሤራ
የተስማሙ ሰዎች ቍጥራቸው ከአርባ በላይ
ነበር። 14 እነርሱ ወደ ካህናት አለቆችና ወደ
ሽማግሌዎች ሄደው እንዲህ ሲሉ ነገሩአቸው፥
“ጳውሎስን ሳንገድል እህል እንዳንቀምስ በጥ
ብቅ ተማምለናል፤ 15 ስለዚህ እናንተ ከሸንጎው
ጋር ተስማምታችሁ፥ በጥብቅ የምትመረምሩት
ነገር እንዳለ በማስመሰል፥ ጳውሎስን እንዲያመ
ጡላችሁ አዛዡን ጠይቁት፤ እኛም እዚህ ከመ
ድረሱ በፊት ልንገድለው ተዘጋጅተናል።”
16 ነገር ግን የጳውሎስ የእኅት ልጅ ይህን
ሤራ ስለ ሰማ፥ ወደ ወታደሮች ሰፈር ሄዶ
ገባና ለጳውሎስ ነገረው። 17 ጳውሎስም ከመቶ
አለቆች አንዱን ጠርቶ “ይህ ልጅ ለጦር አዛዡ
የሚናገረው ነገር ስላለው ወደ እርሱ አቅር
በው” አለው። 18 የመቶ አለቃውም ልጁን ወደ
አዛዡ ይዞ ገባና “እስረኛው ጳውሎስ ጠርቶኝ፥
ይህ ልጅ ለአንተ የሚነግርህ ነገር ስላለው ወደ
አንተ እንዳቀርበው ለመነኝ” አለ።
19 አዛዡም የልጁን እጅ ይዞ ገለል አደረገ
ውና “የምትነግረኝ ነገር ምንድን ነው?” ሲል
ለብቻው ጠየቀው።
20 ልጁም እንዲህ አለ፥ “አይሁዳውያን የጳ
ውሎስን ነገር በጥብቅ የሚመረምሩ መስለው
ነገ ወደ ሸንጎው እንድታቀርብላቸው ሊጠይቁህ

23፥3 ፦ ማቴ. 23፥27-28። 23፥5 ፦ ዘጸ. 22፥28። 23፥6 ፦ ሐ.ሥ. 26፥5፤ ፊል. 3፥5። 23፥8 ፦ ማቴ. 22፥23፤
ማር. 12፥18፤ ሉቃ. 20፥27።



ተስማምተዋል። 21 ነገር ግን እሺ አትበላቸው፤
ምክንያቱም እርሱን ሳንገድል እህል አንበላም፣
ውሃም አንጠጣም፣ በማለት የተማማሉ ከአርባ
የሚበልጡ ሰዎች እርሱን ለመግደል አድፍጠ
ዋል፤ አሁን እነርሱ የሚጠብቁት የአንተን
መልስ ብቻ ነው።” 22 አዛዡም “ይህን ነገር
ለእኔ መንገርህን ለማንም አትግለጥ” ብሎ
ልጁን አሰናበተው።

ጳውሎስ በአገረ ገዢው በፊልክስ ፊት ቀረበ

23 ከዚህ በኋላ የጦር አዛዡ ከመቶ አለቆቹ
ሁለቱን ጠርቶ “ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን
ወደ ቂሳርያ የሚሄዱ ሁለት መቶ ወታደሮችና
ሰባ ፈረሰኞች፣ ሁለት መቶ ጦር ወርዋሪዎችም
አዘጋጁ፤ 24 ለጳውሎስም ፈረስ አዘጋጁለትና
ወደ አገረ ገዢው ወደ ፊልክስ በደህና እንዲደ
ርስ አድርጉት” አላቸው። 25 እንዲህ የሚል
ደብዳቤም ጻፈ፤

26 “ለክቡር አገረ ገዥ ፊልክስ፤
ከቀላውዴዎስ ሉስዮስ፣ ሰላም ለአንተ
ይሁን፤ 27 ይህን ሰው አይሁዳውያን ይዘው
ሊገድሉት ነበር፣ እኔ ግን የሮም ዜጋ መሆ
ኑን ስላወቅሁ ከወታደሮች ጋር ደርሼ አዳን
ሁት። 28 በምን ምክንያት እንደ ከሰሱት
ለማወቅ ፈልጌም ወደ ሸንጎአቸው አቅር
ቤው ነበር። 29 የከሰሱትም ሕጋቸውን በሚ
መለከት ነገር መሆኑን ተረዳሁ፤ ነገር ግን
ለሞት ወይም ለእስራት የሚያደርሰው ነገር
የለም። 30 ይህን ሰው ለመግደል ሤራ እንደ
ተደረገ በሰማሁ ጊዜ ወዲያውኑ ወደ አንተ
ላክሁት፤ ከሳሾቹም በአንተ ፊት ክሳቸውን
እንዲያቀርቡ ነግሬአቸዋለሁ።”

31 ስለዚህ ወታደሮቹ በታዘዙት መሠረት ጳውሎ
ስን በሌሊት ወስደው አንቲጳጥሪስ አደረሱት።
32 በማግሥቱ ፈረሰኞቹ ከጳውሎስ ጋር ጕዞአቸ
ውን እንዲቀጥሉ አድርገው እነርሱ ወደ ሰፈር
ተመለሱ። 33 ፈረሰኞቹ ወደ ቂሳርያ በደረሱ
ጊዜ ደብዳቤውን ለአገረ ገዥው ሰጡና ጳውሎ
ስን በፊቱ አቀረቡት። 34 አገረ ገዥው ደብዳቤ
ውን ካነበበ በኋላ ጳውሎስን “ከየትኛው ክፍለ
ሀገር ነህ?” ሲል ጠየቀው፤ የኪልቅያ ሰው
መሆኑን ባወቀ ጊዜ፥ 35 “ከሳሾችህ ሲመጡ
ጉዳይህን እሰማለሁ” አለው። በሄሮድስ ግቢ
ውስጥ እንዲጠበቅም አዘዘ።

## ምዕራፍ 24

ጳውሎስ በአይሁዳውያን ተከሰሰ

1 ከአምስት ቀን በኋላ ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ
ከአንዳንድ ሽማግሌዎችና ጠርጠሉስ ከሚባል
ጠበቃ ጋር ወደ ቂሳርያ ሄደ፤ እነርሱም ወደ
አገረ ገዥው ወደ ፊልክስ ቀርበው ጳውሎስን
ከሰሱ፤ 2 ጳውሎስ ተጠርቶ በመጣ ጊዜ ጠርጠ
ሉስ እንዲህ ሲል ክሱን ጀመረ፥
“ክቡር ፊልክስ ሆይ! በአንተ አማካይነት
ብዙ ሰላም አግኝተናል፣ በመልካም አስተዳደር
ህም ለሕዝባችን መሻሻል ተገኝቶአል፣ 3 ይህን
መልካም አድራጎትህን በየቦታውና በየጊዜው
የምንቀበለው ከፍ ካለ ምስጋና ጋር ነው።
4 አሁን ግን ጊዜህን ሳላባክንና ሳላደክምህ
ባጭሩ የምነግርህን በቸርነትህ እንድትሰማን
እለምንሃለሁ፤ 5 ይህ ሰው መጥፎ በሽታ ሆኖብ
ናል፣ በዓለም ባሉት አይሁዳውያን ሁሉ ላይ
ሁከት ያስነሣል፣ ናዝራውያን ለሚባሉት መና
ፍቃን መሪያቸው ነው። 6 ቤተ መቅደስንም
ሊያረክስ ሲሞክር ይዘነዋል፣ [በሕጋችንም
መሠረት ልንፈርድበት አስበን ነበር፤ 7 ነገር
ግን የጦር አዛዡ ሉስዮስ መጥቶ በታላቅ ኀይል
ከእጃችን ነጥቆ ወሰደው። 8 ከሳሾቹም ወደ
አንተ እንዲመጡ አዘዘ፤] ይህ በእርሱ ላይ ያቀ
ረብነው ክስ ሁሉ እውነት መሆኑን አንተ ራስህ
እርሱን መርምረህ መረዳት ትችላለህ።” 9 አይ
ሁዳውያን “ይህ ሁሉ ነገር እውነት ነው”
እያሉ በክሱ ተስማሙ።

ጳውሎስ በፊልክስ ፊት
የመከላከያ ንግግር አደረገ

10 አገረ ገዥው ፊልክስ በእጁ ጠቅሶ ጳው
ሎስ እንዲናገር ፈቀደለት፤ ጳውሎስም እንዲህ
ሲል መለሰ፥
“ለብዙ ዓመታት የዚህ አገር ገዥ መሆንህን
ስለማውቅ ለቀረበብኝ ክስ መከላከያዬን በአንተ
ፊት ሳቀርብ በጣም ደስ እያለኝ ነው፤ 11 ለመስ
ገድ ወደ ኢየሩሳሌም ከሄድሁ ከዓሥራ ሁለት
ቀን እንደማይበልጥ አንተ ራስህ ማረጋገጥ ትች
ላለህ፤ 12 በቤተ መቅደስም ሆነ በምኵራብ
ወይም በከተማ ውስጥ ከማንም ጋር ስከራከር
ወይም ሕዝቡን ለሁከት ሳነሣሣ አላገኙኝም፤
13 አሁን ለቀረበብኝ ክስ ሁሉ ምንም ማስረጃ
ሊያቀርቡልህ አይችሉም። 14 ነገር ግን ይህን
ልገልጥልህ እወዳለሁ፤ እነርሱ መናፍቅነት
በሚሉት በጌታ መንገድ የአባቶቻችንን አምላክ
አመልካለሁ፤ በሙሴ ሕግና በነቢያት መጻሕ
ፍት የተጻፈውንም ሁሉ አምናለሁ። 15 እነር
ሱም ተስፋ እንደሚያደርጉት እኔም ጻድቃንና
ኃጥአን ከሞት እንደሚነሡ በእግዚአብሔር
ተስፋ አደርጋለሁ። 16 ስለዚህ በእግዚአብሔርና
በሰው ፊት ንጹሕ ኅሊና እንዲኖረኝ ዘወትር
እተጋለሁ።
17 “ከኢየሩሳሌም ከወጣሁ ብዙ ዓመታት
ካለፉ በኋላ ለወገኖቼ የሚሆን የዕርዳታ ገንዘ
ብና ለእግዚአብሔር የሚሰጥ መባ ይዤ
መጣሁ። 18 በቤተ መቅደስም ያገኙኝ ይህንኑ

24፥17-18 ፦ ሐ.ሥ. 21፥17-28።

ሳደርግ ነው ፤ በዚያን ጊዜ የመንጻትን ሥርዓት
ፈጽሜ ነበር ፡ ከእኔ ጋር ብዙ ሕዝብ አልነበ
ረም ፤ ሁከትም አልተነሣም ። 19 ነገር ግን ከእ
ስያ የመጡ አንዳንድ አይሁዳውያን እዚያ
ነበሩ ፤ እነርሱ በእኔ ላይ የክስ ምክንያት ካላ
ቸው በአንተ ፊት ቀርበው ይናገሩ ። 20 ከዚህ
በኋላ በሸንጎው ፊት ስቀርብ ያደረግሁት በደል
እንዳለ እነዚህ ሰዎች ይናገሩ ። 21 እርግጥ በመ
ካከላቸው ቆሜ ‘የሙታን ትንሣኤ አለ በማለቴ
ዛሬ ለፍርድ በፊታችሁ ቀርቤአለሁ’ ብዬ ከፍ
ባለ ድምፅ ተናግሬአለሁ ፤ ከዚህ በቀር ሌላ ያደ
ረግሁት ነገር የለም ።”

22 ፊልክስ ግን ስለ ጌታ መንገድ በደንብ
ያውቅ ስለ ነበር “የጦር አዛዡ ሉስዮስ በመጣ
ጊዜ ስለ ጉዳያችሁ ውሳኔ እሰጣለሁ” ብሎ አሰ
ናበታቸው ። 23 ጳውሎስን ይጠብቅ የነበረውንም
መቶ አለቃ “እምብዛም ነፃነት ሳትከለክለው
በጥንቃቄ ጠብቀው ፤ ወዳጆቹም የሚያስፈልገ
ውን ሁሉ ይዘውለት ሲመጡ አትከልክልበት”
አለው ።

ጳውሎስ በፊልክስና በድሩሲላ ፊት ቀረበ

24 ከጥቂት ቀኖች በኋላ ፊልክስ ዱሩሲላ ከተ
ባለች አይሁዳዊት ሚስቱ ጋር መጣ ፤ ጳውሎስ
ንም አስጠርቶ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለማመን ሲና
ገር ሰማ ። 25 ጳውሎስ ስለ ጽድቅና ራስን ስለመ
ግዛት ስለሚመጣውም ፍርድ በተናገረ ጊዜ ፊል
ክስ ፈርቶ “አሁን ሂድ ፤ ሲመቸኝ ሌላ ጊዜ አስ
ጠራሃለሁ” አለው ። 26 ፊልክስ ከጳውሎስ ጉቦ
ለመቀበል ተስፋ ያደርግ ነበር ፤ ስለዚህ ብዙ
ጊዜ ጳውሎስን እያስጠራ ያነጋግረው ነበር ።

27 ከሁለት ዓመት በኋላ ጶርቅዮስ ፊስጦስ
በፊልክስ ቦታ ተተካ ፤ ፊልክስ አይሁዳውያንን
ደስ ለማሰኘት ፈልጎ ጳውሎስን እንደታሰረ
ተወው ።

## ምዕራፍ 25

ጳውሎስ ወደ ሮም ንጉሠ ነገሥት ይግባኝ አለ

1 ፊስጦስ ወደ ግዛቱ ወደ ቂሣርያ ገብቶ ሦስት
ቀን ከቆየ በኋላ ከዚያ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ።
2-3 እዚያም የካህናት አለቆችና አንዳንድ ታላላቅ
አይሁዳውያን በጳውሎስ ላይ ክሳቸውን አቀ
ረቡ ፤ “ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም በማስመጣት
ለእኛ መልካም ነገር አድርግልን” ሲሉም ለመ
ኑት ፤ ይህንንም ያሉበት ምክንያት ጳውሎስን
በመንገድ ጠብቀው ሊገድሉት ስለፈለጉ ነው ።
4 ፊስጦስ ግን “ጳውሎስ በቂሳርያ በእስር ቤት
እየተጠበቀ ነው ፤ እኔም አሁን በቶሎ ተመልሼ
ወደዚያ እሄዳለሁ ፤ 5 ባለሥልጣኖቻችሁ ከእኔ
ጋር ወደ ቂሳርያ ይሂዱ ፤ ጳውሎስ ያደረገው
በደል ካለ እዚያ ይክሰሱት” አላቸው ።

6 ፊስጦስ ከስምንት ወይም ከዐሥር ቀኖች
ያልበለጠ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ካሳለፈ በኋላ ወደ
ቂሳርያ ሄደ ፤ እዚያ በደረሰ ጊዜ በማግሥቱ በፍ
ርድ ወንበር ላይ ተቀመጠና ጳውሎስን እንዲያ
ቀርቡት አዘዘ ። 7 ጳውሎስ በቀረበ ጊዜ ከኢየሩሳ
ሌም የመጡት አይሁዳውያን ከብበውት ቆሙና
ማስረጃ ሊያገኙለት የማይችሉትን ብዙ ከባድ
ክስ አቀረቡበት ፤ 8 ጳውሎስም “እኔ በአይሁድ
ሕግ ላይም ሆነ በቤተ መቅደስ ወይም በሮም
ንጉሠ ነገሥት በቄሳርም ላይ ያደረግሁት በደል
የለም” ሲል የመከላከያ መልሱን ሰጠ ።

9 ፊስጦስ ግን አይሁዳውያንን ደስ ለማሰኘት
ፈልጎ ጳውሎስን “ወደ ኢየሩሳሌም ሄደህ ስለ
ዚህ ጉዳይ እዚያ በእኔ ፊት ልትፋረድ ትፈልጋ
ለህን?” አለው ። 10 ጳውሎስ ግን እንዲህ ሲል
መልስ ሰጠ ፤ “እነሆ እኔ ልፋረድበት በሚገባኝ
በቄሳር የፍርድ ወንበር ፊት ቆሜአለሁ ፤ አን
ተም በደንብ እንደምታውቀው በአይሁዳውያን
ላይ ያደረግሁት ምንም በደል የለም ፤ 11 በደ
ለኛ ከሆንሁ ወይም በሞት የሚያስቀጣ በደል
ካደረግሁ ከሞት ልዳን አልልም ፤ ነገር ግን የእ
ነርሱ ክስ ከንቱ ከሆነ ማንም ለእነርሱ አሳልፎ
ሊሰጠኝ አይችልም ፤ እኔ ወደ ቄሳር ይግባኝ
ብያለሁ ።”

12 በዚያን ጊዜ ፊስጦስ ከአማካሪዎቹ ጋር
ተነጋገረና “ወደ ቄሳር ይግባኝ ካልህ ወደ
ቄሳር ትሄዳለህ” አለው ።

ጳውሎስ በአግሪጳና
በበርኒቄ ፊት ቀረበ

13 ከጥቂት ቀን በኋላ ንጉሥ አግሪጳና በርኒቄ
ፊስጦስን “እንኳን ደህና መጣህ” ለማለት ወደ
ቂሳርያ መጡ ። 14 እዚያም ብዙ ቀን በመቀመ
ጣቸው ፊስጦስ የጳውሎስን ጉዳይ እንዲህ ሲል
ለንጉሥ አግሪጳ ገለጠ ፤ “ፊልክስ እስሮ የተ
ወው እዚህ አንድ ሰው አለ ፤ 15 እኔ በኢየሩሳ
ሌም በነበርሁበት ጊዜ የካህናት አለቆችና የአይ
ሁድ ሽማግሌዎች የዚህን ሰው ጉዳይ ካመለከ
ቱኝ በኋላ እንድፈርድበት ጠየቁኝ ። 16 እኔ ግን
‘ተከሳሽ ከከሳሾች ፊት ቆሞ ለተከሰሰበት ነገር
የመከላከያ መልስ ሳይሰጥ ተከሳሹን አሳልፎ
መስጠት የሮማውያን ሥርዓት አይደለም’ ብዬ
መለስሁላቸው ። 17 ስለዚህ ከሳሾቹ ተሰብስበው
ወደዚህ በመጡ ጊዜ ሳልዘገይ በማግሥቱ በፍ
ርድ ወንበር ተቀመጥሁና ጳውሎስን በፊቴ እን
ዲያቀርቡት አዘዝሁ ፤ 18 ከሳሾቹም አጠገቡ
በቆሙ ጊዜ እኔ ክፉ ነገር ሠርቶአል ብዬ የገመ
ትሁትን ያህል ለክስ የሚያበቃ ምንም ነገር አላ
ቀረቡበትም ። 19 ነገር ግን ከእርሱ ጋር ይከራከ
ሩበት የነበረው ስለ ሃይማኖታቸውና ሞቶ ስለነ
በረው ፤ ጳውሎስ ግን ‘ሕያው ነው’ ስለሚለው

24፡21 ፦ ሐ.ሥ. 23፡6 ።



ኢየሱስ ነው ። 20 እኔም እንዲህ ዐይነቱን ነገር
መመርመር ስለቸገረኝ ጳውሎስን ‘ወደ ኢየሩሳ
ሌም ሄደህ እዚያ በዚህ ነገር ልትፋረድ ትወዳ
ለህን?’ አልሁት ። 21 እርሱ ግን ጉዳዩ በሮም
ንጉሠ ነገሥት እንዲታይለት ፈልጎ ወደ ቄሳር
ይግባኝ በማለቱ ወደ ቄሳር እስክልከው ድረስ
በእስር ቤት እንዲቆይ አዘዝሁ ።”

22 አግሪጳም ፊስጦስን “እኔም ይህ ሰው ሲና
ገር መስማት እፈልጋለሁ” አለው ። ፊስጦስም
“ነገ ትሰማዋለህ” አለው ።

23 ስለዚህ በማግሥቱ አግሪጳና በርኒቄ ልብሰ
መንግሥታቸውን ለብሰውና በታላቅ ግርማ
ሆነው በጦር አለቆችና በከተማው ታላላቅ ሰዎ
ችም ታጅበው መጡና ወደ ፍርድ አዳራሽ
ገቡ ፤ ከዚያም በኋላ ፊስጦስ ጳውሎስን አስ
ጠራ ። 24 እንዲህም አለ ፤ “ንጉሥ አግሪጳ
ሆይ! እናንተም ከእኛ ጋር ያላችሁ ሰዎች
ሁሉ! አይሁዳውያን ‘ይህ ሰው ከእንግዲህ
ወዲህ በሕይወት መኖር አይገባውም’ በማለት
እየጮኹ በኢየሩሳሌምም ፤ በዚህም እንዲፈረድ
በት የጠየቁኝ ይህ የምታዩት ሰው ነው ። 25 እኔ
ግን በሞት የሚያስቀጣው ምንም በደል አላገኘ
ሁበትም ፤ እርሱ ወደ ሮም ንጉሠ ነገሥት ይግ
ባኝ በማለቱ ወደዚያ ልልከው ወሰንሁ ።
26 ይሁን እንጂ ስለ እርሱ ለጌታዬ የምጽፈው
የተረጋገጠ ነገር የለኝም ፤ ስለዚህ ከተመረመረ
በኋላ የምጽፈው ነገር እንዳገኝ ብዬ በፊታ
ችሁ ፤ ይልቁንም ንጉሥ አግሪጳ ሆይ! በፊትህ
አቅርቤዋለሁ ። 27 ምክንያቱም እስረኛ ወደ
በላይ ሲላክ የተከሰሰበትን ምክንያት አለመግለጥ
ሞኝነት መስሎ ታይቶኛል ።”

## ምዕራፍ 26

ጳውሎስ በአግሪጳ ፊት ያደረገው ንግግር

1 አግሪጳ ጳውሎስን “ስለ ራስህ እንድትና
ገር ተፈቅዶልሃል” አለው ፤ ጳውሎስም እጁን
ዘረጋና እንዲህ ሲል የመከላከያ መልሱን
ሰጠ ፤

2 “ንጉሥ አግሪጳ ሆይ! አይሁዳውያን በከሰ
ሱኝ ነገር ሁሉ ዛሬ በአንተ ፊት የመከላከያ
መልስ ስሰጥ እጅግ ደስ ይለኛል ። 3 ምክንያ
ቱም አንተ የአይሁዳውያንን ሥርዓትና ክርክር
ሁሉ ጠንቅቀህ ታውቃለህ ፤ ስለዚህ በትዕግሥት
እንድታዳምጠኝ እለምንሃለሁ ።

4 “ከልጅነቴ ጀምሮ እንዴት እንደኖርሁ
አይሁዳውያን ያውቃሉ ፤ ከመጀመሪያ አንሥቶ
በሕዝቤ መካከልና በኢየሩሳሌም የኖርሁትን
ሕይወቴን ያውቁታል ። 5 ደግሞም ሊመሰክሩ
ቢፈቅዱ ከሃይማኖታችን በጣም ወግ አጥባቂ
ከሆነው ክፍል ፈሪሳዊ ሆኜ እንደኖርሁ ከመጀ
መሪያው አንሥቶ ያውቃሉ ። 6 አሁን ግን ለፍ
ርድ እዚህ የቆምሁት እግዚአብሔር ለአባቶቻ
ችን ስለሰጠው የቃል ኪዳን ተስፋ ነው ። 7 ወደ
ዚህ ተስፋ ለመድረስ ዐሥራ ሁለቱ ነገዶቻችን
እግዚአብሔርን ቀንና ሌሊት እያመለኩ ይጠባ
በቁ ነበር ፤ ንጉሥ ሆይ! እኔም በአይሁዳውያን
የተከሰስሁበት በዚህ ተስፋ ምክንያት ነው ።
8 እግዚአብሔር ሙታንን የሚያስነሣ መሆኑ ስለ
ምን በእናንተ በአይሁዳውያን ዘንድ ሊታመን
የማይቻል ሆነ?

9 “እኔ ራሴ የናዝሬቱን የኢየሱስን ስም የተ
ቃለኝን ያህል መቃወም አለብኝ ብዬ አስብ
ነበር ። 10 በኢየሩሳሌም ያደረግሁትም ይህንኑ
ነበር ፤ ከካህናት አለቆች በተቀበልሁት ሥልጣን
ከአማኞች ብዙዎቹ ወደ ወህኒ ቤት እንዲገቡ
አድርጌአለሁ ፤ ሲገድሉአቸውም ከገዳዮቻቸው
ጋር ተስማምቻለሁ ። 11 ብዙ ጊዜ በየምኩራቡ
እንዲቀጡና እምነታቸውን እንዲክዱ አድርጌአ
ለሁ ፤ በእነርሱ ላይ በጣም ተቈጥቼም ወደ
ሌሎች ከተሞች እንኳ ወጥቼ እየሄድሁ አሳድዳ
ቸው ነበር ።

ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ እንዴት
እንደተመለሰ ተረክ
(ሐ.ሥ. 9፡1-19፤ 22፡6-16)

12 “ለዚሁ ጉዳይ ከካህናት አለቆች ሙሉ
ሥልጣንና ትእዛዝ ተቀብዬ ወደ ደማስቆ እሄድ
ነበር ፤ 13 ንጉሥ ሆይ! በመንገድ ሳለሁ ልክ
እኩለ ቀን ሲሆን ከፀሐይ ብርሃን የሚበልጥ
ብርሃን አየሁ ፤ ይህም ብርሃን በእኔና ከእኔ ጋር
በሚጓዙት ሰዎች ዙሪያ ከሰማይ አበራ ።
14 ሁላችንም በመሬት ላይ ወድቀን ሳለ በአይ
ሁድ ቋንቋ ፤ ‘ሳውል! ሳውል! ስለምን ታሳድ
ደኛለህ? በሰይፍ ስለት ላይ ብትቆም ራስህን
ትጐዳለህ’ የሚል ድምፅ ሰማሁ ። 15 እኔም
‘ጌታ ሆይ! አንተ ማን ነህ?’ አልሁ ፤ ጌታም
እንዲህ አለኝ ፤ ‘እኔ አንተ የምታሳድደኝ ኢየ
ሱስ ነኝ ። 16 አሁን ግን ተነሥና በእግርህ
ቁም ፤ እኔ የተገለጥሁልህ ፤ አሁን እኔን ባየህበ
ትና ወደፊትም እኔ ለአንተ በምገለጥበት ነገር
አገልጋይና ምስክር እንድትሆነኝ ልሾምህ
ፈልጌ ነው ። 17 ከእስራኤል ሕዝብና ወደ እነ
ርሱ ከምልክህ አሕዛብ እጅ አድንሃ
ለሁ ። 18 ዐይናቸውን እንድትከፍትላቸውና
ከጨለማ ወደ ብርሃን እንድታወጣቸው ከሰይጣ
ንም ግዛት ወደ እግዚአብሔር እንድትመልሳ
ቸው አደርግሃለሁ ፤ እነርሱም በእኔ በማመና
ቸው ምክንያት የኃጢአታቸውን ይቅርታ ያገ
ኛሉ ፤ በተመረጡት መካከልም ርስትን ይካፈ
ላሉ ።’

26፡5 ፦ ሐ.ሥ. 23፡6 ፤ ፊል. 3፡5 ። 26፡9-11 ፦ ሐ.ሥ. 8፡3 ፤ 22፡4-5 ።

### ጳውሎስ ስለ ሥራው ሁኔታ አስረዳ

19 “ስለዚህ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ! ከሰማይ ለተ
ሰጠኝ ራእይ ታዛዥ ሆኜአለሁ ። 20 ነገር ግን አስ
ቀድሜ በደማስቆ ያሉት ሰዎች ፥ ቀጥሎም በኢየ
ሩሳሌምና በይሁዳ አገር ሁሉ ያሉት እንዲሁም
አረማውያን ጭምር ንስሓ ገብተው ወደ እግዚአ
ብሔር እንዲመለሱ አስተማርሁአቸው ፤ ንስሓ
መግባታቸውን የሚያመለክት ነገር እንዲያደር
ጉም ነገርሁአቸው ። 21 በዚህ ምክንያት አይሁዳ
ውያን በቤተ መቅደስ እንዳለሁ ያዙኝና ሊገድ
ሉኝ ፈለጉ ። 22 እስከ ዛሬ ድረስ የእግዚአብሔር
ዕርዳታ አልተለየኝም ፤ ስለዚህ ለትንሹም ለትል
ቁም እየመሰከርሁ እዚህ ቆሜአለሁ ፤ ነቢያትና
ሙሴ አስቀድመው እንዲህ ይሆናል ያሉትን
ከመናገር በቀር ሌላ ምንም አልተናገርሁም ።
23 እነርሱም የተናገሩት ‘መሲሕ መከራ ይቀበ
ላል ፤ ከሞት በመነሣትም የመጀመሪያ ሆኖ የደ
ኅንነትን ብርሃን ለእስራኤል ሕዝብና ለአረማው
ያን ይገልጣል’ ብለው ነው ።”
24 ጳውሎስ ይህንን ሲናገር ሳለ ፊስጦስ “ጳው
ሎስ ሆይ! አሁንስ አበድህ ፤ ብዙ መማርህ ወደ
እብደት አድርሶሃል!” ሲል ጮኾ ተናገረ ።
25 ጳውሎስ ግን እንዲህ ሲል መለሰ ፦
“ክቡር ፊስጦስ ሆይ! እውነተኛውንና ትክክለ
ኛውን ነገር እናገራለሁ እንጂ አላበድሁም ።
26 በፊቱ በግልጥ የተናገርሁት ንጉሥ ይህን
ነገር ያውቃል ። ይህም በስውር ያልተደረገ ስለ
ሆነ ንጉሡ እንደሚረዳው እርግጠኛ ነኝ ።
27 ንጉሥ አግሪጳ ሆይ! ነቢያትን ታምን የለ
ምን? እንደምታምን ዐውቃለሁ ።”
28 አግሪጳም ጳውሎስን “አንተ እኮ በዚህ በአ
ጭር ጊዜ ውስጥ ክርስቲያን ልታደርገኝ ነው!”
አለው ። 29 ጳውሎስም “በአጭር ጊዜም ይሁን
በረዥም ጊዜ አንተ ብቻ ሳትሆን ዛሬ ንግግሬን
የሰሙ ሁሉ ከዚህ ከእስራቴ በቀር እንደ እኔ እን
ዲሆኑ እግዚአብሔርን እለምናለሁ” አለ ።
30 ከዚህ በኋላ ንጉሡ ፥ ገዥውና በርኒቄ ፥
ከእነርሱ ጋር ተቀምጠው የነበሩትም ሰዎች
ሁሉ ተነሡ ። 31 ከዚያም ወጥተው ሲሄዱ
“ይህ ሰው ለሞት ወይም ለእስራት የሚያበ
ቃው ምንም ነገር አላደረገም” ተባባሉ ።
32 አግሪጳም ፊስጦስን “ይህ ሰው ወደ ቄሳር
ይግባኝ ባይል ኖሮ በነፃ በተለቀቀ ነበር” አለ ።

## ምዕራፍ 27

### የጳውሎስ ጉዞ ወደ ሮም

1 ወደ ኢጣሊያ በመርከብ እንድንሄድ በተወ
ሰነ ጊዜ ጳውሎስንና ሌሎችንም እስረኞች በን
ጉሡ ንጉሥቱ በአውግስጦስ ክፍለ ጦር ውስጥ
ለነበረው ዩልዮስ ለሚባለው መቶ አለቃ አስረከ
ቡአቸው ። 2 በእስያ የባሕር ዳርቻ ወዳሉት
ወደቦች በሚሄደው አድራሚጥዮን መርከብ ተሳ
ፍረን ተጓዝን ፤ በተሰሎንቄ የሚኖረው የመቄዶ
ንያው ሰው አርስጥሮኮስም ከእኛ ጋር ነበረ ።
3 በማግሥቱ ወደ ሲዶና ደረስን ፤ ዩልዮስ ለጳው
ሎስ ደግ ስለነበረ ወደ ወዳጆቹ ሄዶ የሚያስፈ
ልገውን ዕርዳታ እንዲያደርጉለት ፈቀደለት ።
4 ከዚያም ተነሥተን ነፋሱ ፊት ለፊት ይነፍስ
ብን ስለ ነበር ፥ የቆጵሮስን ደሴት ተገን አድር
ገን በመርከብ ጉዞአችንን ቀጠልን ። 5 በኪልቅ
ያና በጵንፍልያ አጠገብ ያለውን ባሕር ከተሻገ
ርን በኋላ በሊቅያ አገር ወዳለው ወደ ሙራ
ከተማ ደረስን ። 6 እዚያ የመቶ አለቃው ወደ
ኢጣሊያ የሚሄድ የእስክንድርያ መርከብ አገ
ኝና በእርሱ ላይ እንድንሳፈር አደረገ ።
7 ብዙ ቀን ቀስ እያልን ተጓዝን ፤ በብዙ
ችግር ወደ ቀኒዶስ ከተማ አጠገብ ደረስን ፤ ነፋ
ሱም ወደፊት እንዳንሄድ ስለከለከለን በሰልሞና
ሜፍ አጠገብ አለፍንና የቀርጤስን ደሴት ተገን
አድርገን ሄድን ። 8 በብዙ ችግር ጥግ ጥጉን ካለ
ፍን በኋላ በላሲያ ከተማ አጠገብ ወደምትገኘው
“መልካም ወደብ” ወደምትባለው ስፍራ ደረ
ስን ።
9 በጉዞአችን ላይ ብዙ ጊዜ በመባከኑና
የጾም ጊዜ በማለፉ ምክንያት በዚህ ጊዜ በባ
ሕር ላይ መጓዝ አደገኛ ስለነበር ጳውሎስ ለሰ
ዎቹ እንዲህ ሲል አስጠነቀቃቸው ፥ 10 “እና
ንተ ሰዎች! ከእንግዲህ ወዲህ ያለው ጉዞአችን
አደጋ እንዳለበት ይታየኛል ፤ በጭነቱና በመር
ከቡ ላይ ብቻ ሳይሆን በሰው ሕይወትም ላይ
ብርቱ ጉዳትና ጥፋት ይደርሳል ።” 11 የመቶ
አለቃው ግን ከጳውሎስ ምክር ይልቅ የመርከቡ
አዛዥና የመርከቡ ባለቤት የሚሉትን ይሰማ
ነበር ። 12 ያ ወደብ ለክረምት ማሳለፊያ ምቹ
ስላልነበረ አብዛኞዎቹ ሰዎች “ጉዞአችውን
ቀጥለው የሚቻል ቢሆን በሰሜን ምዕራብና በደ
ቡብ ምዕራብ በር ወዳለው ፊንቄ ወደሚባለው
የቀርጤስ ወደብ ደርሰን ክረምቱን እዚያ እናሳ
ልፍ” ብለው አሳብ አቀረቡ ።

### በባሕሩ ላይ ማዕበል ተነሣ

13 እነስተኛ የደቡብ ነፋስ ሲነፍስ ባዩ ጊዜ
እንዳሰቡት የሆነላቸው መስሎአቸው ጉዞአቸ
ውን ለመቀጠል ተነሡ ፤ ከወደቡም ተነሥተው
በቀርጤስ አጠገብ አድርገው ጥግ ጥጉን አለፉ ።
14 ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ “የሰሜናዊ
ምሥራቅ ዐውሎ ነፋስ” የሚባል ኀይለኛ ነፋስ
ከደሴቲቱ ተነሥቶ ወደ ባሕሩ መጣባቸው ።
15 መርከቡም ስለተገፋና ነፋሱን መቋቋም ስላ
ልቻለ ዝም ብለን በነፋሱ እየተነዳን ሄድን ።
16 ቄዳ የተባለችውን ደሴት ተገን አድርገን
ስንጓዝ በታላቅ ችግር የመርከቡን ጀልባ ይዘን
በቍጥጥራችን ሥር ለማድረግ ቻልን ። 17 መርከ
በኞቹ ጀልባውን ወደ መርከቡ ሰበው ካወጡት
በኋላ በመርከቡ ዙሪያ ገመድ ጠመጠሙ ፤ መር
ከቡ ሱርቲስ ወደምትባል አሸዋማ ስፍራ እንዳይ
ወድቅ ፈርተው ሸራውን አወረዱና በነፋስ እየተ
ነዱ ሄዱ ። 18 ዐውሎ ነፋሱ እየበረታብን ስለሄደ
በማግሥቱ በመርከቡ ላይ ከተጫኑት ዕቃዎች
እያንዳንዱን ወደ ባሕር መጣል ጀመሩ ። 19 በሦ
ስተኛው ቀን ለመርከቡ የሚያገለግሉትን ዕቃ
ዎች በገዛ እጃቸው እየወረወሩ ጣሉ ፤ 20 ለብዙ
ቀን ፀሐይም ሆነ ፤ ከዋክብት ስላልታዩና ነፋ
ሱም እየበረታብን ስለሄደ ከእንግዲህ ወዲህ
መዳን አንችልም ብለን ተስፋ ቈረጥን ።
21 ሰዎቹ ምንም ምግብ ሳይበሉ ብዙ ቀን
ቆዩ ፤ ስለዚህ ጳውሎስ በመካከላቸው ቆሞ እን
ዲህ አለ ፥ “እናንተ ሰዎች! እኔ ያልሁአችሁን
ሰምታችሁ ከቀርጤስ ባትነሡ ኖሮ ይህ ሁሉ
ጉዳትና ጥፋት ባልደረሰባችሁም ነበር ። 22 አሁ
ንም መርከቡ ብቻ ይጐዳል እንጂ ከእናንተ በማ
ንም ላይ ጥፋት አይደርስም ፤ ስለዚህ አይዞአ
ችሁ ፥ አትፍሩ ፥ ብዬ እመክራችኋለሁ ። 23 ባለ
ፈው ሌሊት የእርሱ የሆንሁ ፥ የማመልከው አም
ላክ የላከው መልአክ በአጠገቤ ቆሞ ፥ 24 ‘ጳው
ሎስ ሆይ! አትፍራ ፤ በቄሳር ፊት መቆም ይገባ
ሃል ፤ እነሆ ከአንተ ጋር የሚጓዙትንም ሁሉ እግ
ዚአብሔር ለአንተ ብሎ ከሞት ያድናቸዋል’
ብሎ ነግሮኛል ። 25 ስለዚህ እናንተ ሰዎች አይዞ
አችሁ ፤ እግዚአብሔር ይህንን የነገረኝን እንደሚ
ፈጽም አምንዋለሁ ። 26 ሆኖም ነፋሱ ወደ አን
ዲት ደሴት ዳርቻ ወስዶ ይጥለናል ።”
27 በዐሥራ አራተኛው ሌሊት በሜድትራን
ያን ባሕር መካከል ላይ በነፋስ እየተንገላታን ስን
ሄድ እኩለ ሌሊት ላይ መርከበኞች ወደ ምድር
የቀረቡ መሰላቸው ። 28 ስለዚህ የባሕር ጥልቀት
መለኪያ ገመድ ሲጥሉ ፥ የባሕሩ ጥልቀት አርባ
ሜትር ያህል ሆኖ ተገኘ ፤ ጥቂት ቆይተው መለ
ኪያውን እንደገና በጣሉ ጊዜ ሠላሳ ሜትር
ያህል ጥልቀት አገኙ ። 29 መርከባችን በባሕሩ
ዳር ካሉ ድንጋዮች እንዳይጋጭ ፈርተው ከመር
ከቡ በስተኋላ አራት መልሕቆች ወደ ባሕሩ አወ
ረዱ ፤ ከዚህ በኋላ ሌሊቱ አልፎ ቀን እንዲመጣ
ላቸው ይጸልዩ ጀመር ። 30 መርከበኞቹ ከመር
ከቡ ወጥተው ለመሸሽ ፈልገው ስለነበር በመር
ከቡ በስተፊት መልሕቆችን የሚጥሉ መስለው
በመርከቡ ላይ የነበረችውን ጀልባ ወደ ባሕሩ
ጣሉ ። 31 በዚህ ጊዜ ጳውሎስ መቶ አለቃውንና
ወታደሮቹን “እነዚህ መርከበኞች በመርከቡ
ላይ ዐርፈው ካልተቀመጡ እናንተ ለመዳን አት
ችሉም” አላቸው ። 32 ስለዚህ ወታደሮቹ ጀልባ
ውን የያዘውን ገመድ ቈረጡና እንድትንሳፈፍ
ተዉአት ። 33 ቀኑ ሊነጋ ሲል ሁሉም ምግብ እን
ዲመገቡ ጳውሎስ ለመናቸው ፤ እንዲህም አላ
ቸው ፥ “ምንም ምግብ ሳትበሉ በመጠባበቅ ከሰ
ነበታችሁ ዛሬ ዐሥራ አራተኛ ቀናችሁ ነው ።
34 ስለዚህ እህል እንድትበሉ እለምናችኋለሁ ።
ይህም ብርታት ይሰጣችኋል ፤ ከቶም ምንም ዐይ
ነት ጉዳት አይደርስባችሁም ።” 35 ይህንንም
ካለ በኋላ እንጀራ አንሥቶ በሁሉ ፊት እግዚአብ
ሔርን አመስገነ ፤ ቈርሶም መብላት ጀመረ ።
36 በዚህ ጊዜ ሁሉም ተጽናኑና ምግብ በሉ ።
37 በመርከቡ ውስጥ በጠቅላላው ሁለት መቶ ሰባ
ስድስት ሰዎች ነበርን ። 38 ሁሉም በልተው ከጠ
ገቡ በኋላ የተጫነውን ስንዴ ወደ ባሕር በመ
ጣል የመርከቡን ክብደት አቃለሉ ።

### መርከቡ ተሰበረ

39 በነጋም ጊዜ የደረሱበትን ቦታ አላወቁ
ትም ፤ ነገር ግን የአሸዋ ዳርቻ ያለውን የባሕር
ሰርጥ አዩ ፤ የሚቻል ቢሆን መርከቡን ወደዚያ
ለመግፋት አሰቡ ። 40 መልሕቆቹን ፈትተው
በባሕር ውስጥ ለቀቁአቸው ፤ በዚያን ጊዜም
የመቅዘፊያውን ገመዶች ፈቱ ፤ ከዚህ በኩል
ያለውን ሸራ ወደ ነፋሱ ከፍ አድርገው ወደ
ባሕሩ ዳርቻ ለመውጣት ሄዱ ። 41 ነገር ግን
መርከቡ ከአሸዋ ቍልል ጋር በመጋጨቱ ቁል
ቁል ተደፋ ፤ በስተፊቱም ወደ ታች ተተክሎ
የማይነቃነቅ ሆነ ፤ በስተኋላው ግን ከማዕበሉ
ግፊት የተነሣ ይሰባበር ጀመር ።
42 ከእስረኞቹ አንድ እንኳ ዋኝቶ እንዳያመ
ልጥ ወታደሮቹ ሊገድሉዋቸው አሰቡ ።
43 የመቶ አለቃው ግን ጳውሎስን ለማዳን ስለፈ
ለገ አሳባቸውን አልተቀበለም ፤ ይልቁንም መዋ
ኘት የሚችሉ አስቀድመው ከመርከቡ ወደ
ባሕር እየዘለሉ ወደ ምድር እንዲወጡ አዘዘ ።
44 የቀሩት ደግሞ በሳንቃዎችና በመርከቡ
ስብርባሪዎች ላይ ሆነው እንዲወጡ አዘዘ ፤ በዚህ
ሁኔታ ሁሉም በደኅና ወደ ምድር ደረሱ ።

## ምዕራፍ 28

### ጳውሎስ በማልታ ደሴት

1 ወደ ምድር በደኅና ከደረስን በኋላ የደረስን
ባት ደሴት ማልታ የምትባል መሆንዋን ዐወቅን ።
2 የዚያች ደሴት ነዋሪዎች የሚያስደንቅ ደግነት
አደረጉልን ፤ በዚያን ጊዜም ዝናም ስለዘነመና
ብርድ ስለሆነ እሳት አንድደው ተቀበሉን ፤ 3 ጳው
ሎስ ጭራሮ ሰብስቦ ወደ እሳቱ ሲጥል ከሙቀቱ
የተነሣ አንድ እባብ ወጣና በእጁ ላይ ተጣብቆ
ተንጠለጠለ ፤ 4 የማልታ ሰዎች እባብ በጳውሎስ
እጅ ላይ ተንጠልጥሎ ባዩ ጊዜ “ይህ ሰው በእር
ግጥ ነፍሰ ገዳይ ነው! ምክንያቱም ከባሕሩ ማዕ
በል በደኅና ቢወጣም ከፍርድ አምላክ አምልጦ
በሕይወት ለመኖር አልቻለም” ተባባሉ ። 5 ጳው
ሎስ ግን እባቡን ወደ እሳቱ አራግፎ ጣለውና
ምንም ጉዳት ሳያገኘው ቀረ ። 6 ሰዎቹም “ከአ
ሁን አሁን ሰውነቱ ያብጣል ወይም በድንገት



26፡20 ፦ ሐ.ሥ. 9፡20 ፡28-29 ። 26፡23 ፦ ኢሳ. 42፡6 ፤ 49፡6 ፤ 1ቆሮ. 15፡20 ።

ሞቶ ይወድቃል” በማለት ይጠባበቁ ነበር ። ነገር
ግን ብዙ ጊዜ ተጠባብቀውት ምንም ጉዳት እንዳ
ልደረሰበት ባዩ ጊዜ አሳባቸውን ለወጡና “ይህስ
አምላክ ነው!” አሉ ።
7 በዚያ በነበርንበት ስፍራ አጠገብ ፣ የደሴ
ቲቱ ገዥ የፑፕልዮስ መሬት ነበር ፤ ይህ ሰው
በቤቱ ተቀብሎን ሦስት ቀን በጥሩ ሁኔታ አስተና
ገደን ። 8 በዚያን ጊዜ የፑፕልዮስ አባት ትኩሳ
ትና ተቅማጥ ይዞት ታሞ ተኝቶ ነበር ፤ ጳውሎስ
ወደ እርሱ ገብቶ ጸለየለት ፤ እጁንም ጫነበትና
ፈወሰው ። 9 ይህ ከሆነ በኋላ በደሴቲቱ የሚኖሩት
ሌሎች በሽተኞች መጡና ተፈወሱ ። 10 ሰዎቹ
ብዙ ስጦታ አመጡልንና አክብሮታቸውን ገለጡ
ልን ፤ በመርከብ ለመሄድ በተነሣንም ጊዜ የሚያ
ስፈልገንን ሁሉ በመርከብ ላይ ጫኑልን ።

### የጳውሎስ ጉዞ ከማልታ ወደ ሮም

11 ሦስት ወር በማልታ ከቆየን በኋላ ክረምቱን
በደሴቲቱ ባሳለፈው በእስክንድርያው መርከብ
ተሳፍረን ተነሣን ፤ መርከቡ ዲዮስቆሮስ የተባሉ
የመንታ አማልክት አርማ ነበረበት ። 12 ወደ ስራ
ኩስ ከተማ በደረስን ጊዜ እዚያ ሦስት ቀን ተቀመ
ጥን ። 13 ከዚያም በባሕሩ ተጕዘን ወደ ሬጊዩም
ደረስን ፤ እዚያ አንድ ቀን ካሳለፍን በኋላ የደቡብ
ነፋስ ስለነፈሰ በሁለተኛው ቀን ወደ ፑቲዮሉስ
ሄድን ። 14 እዚያ አማኞችን አገኘንና ከእነርሱ
ጋር ሰባት ቀን እንድንቀመጥ ለመኑን ፤ ከዚህ
በኋላ ወደ ሮም ሄድን ። 15 በሮም ያሉ አማኞች
ስለ እኛ በሰሙ ጊዜ እስከ አፍዮስ ገበያና “ሦስት
ማደሪያዎች” እስከሚባለው ቦታ ድረስ ሊቀበሉን
መጡ ፤ ጳውሎስ እነርሱን ባየ ጊዜ እግዚአብሔ
ርን አመሰገነና ተጽናና ።

### ጳውሎስ በሮም

16 ወደ ሮም በገባን ጊዜ ጳውሎስ አንድ
የሚጠብቀው ወታደር ተሰጠውና ብቻውን እን
ዲኖር ተፈቀደለት ።
17 ከሦስት ቀን በኋላ ጳውሎስ በሮም የሚኖሩ
ትን የአይሁዳውያንን ታላላቅ ሰዎች አስጠራ ፤
በተሰበሰቡም ጊዜ እንዲህ አላቸው ፣ “ወንድ
ሞቼ ሆይ! በእስራኤል ሕዝብ ላይና በአባቶች
ሥርዓት ላይ ያደረግሁት ምንም በደል የለም ፤
ይሁን እንጂ በኢየሩሳሌም ታስሬ ለሮማውያን
ተሰጠሁ ። 18 ሮማውያን ከመረመሩኝ በኋላ
በሞት የሚያስቀጣ ምክንያት ስላላገኙብኝ በነፃ
ሊለቅቁኝ አስበው ነበር ። 19 አይሁዳውያን ግን
የእኔን በነፃ መለቀቅ በተቃወሙ ጊዜ ወደ ቄሳር
ይግባኝ ለማለት ተገደድሁ ፤ ሆኖም ሕዝቤን
የምከስበት ነገር አልነበረኝም ። 20 አሁንም ያስ
ጠራኋችሁ እንዳያችሁና ይህንንም እንድነግራ
ችሁ ነው ፤ እኔ በዚህ በሰንሰለት የታሰርሁት ለእ
ስራኤል በተሰጠው ተስፋ ምክንያት ነው ።”
21 እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱለት ፣ “ከይ
ሁዳ አገር ስለ አንተ ጉዳይ የተጻፈ ደብዳቤ
አልደረሰንም ፤ ወደዚህ ከመጡ ሰዎች ማንም
ስለ አንተ ክፉ ያወራ ወይም የተናገረ የለም ።
22 ይህን አንተ የምትከተለውን የሃይማኖት
ክፍል በየቦታው ሰዎች እንደሚቃወሙት እና
ውቃለን ፤ ስለዚህ የአንተ አሳብ ምን እንደሆነ
መስማት እንፈልጋለን ።”
23 ቀን ከቀጠሩለትም በኋላ ብዙ ሆነው ወደ
መኖሪያ ቤቱ መጡ ፤ እርሱም ከጠዋት እስከ
ማታ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት በመመስከር
አሳቡን ገለጠላቸው ፤ ከሙሴ ሕግና ከነቢያት
መጻሕፍት እየጠቀሰም ስለ ኢየሱስ አስረዳቸው ።
24 አንዳንዶቹ የተናገረውን ቃል አመኑ ፤ ሌሎች
ግን አላመኑም ። 25 እነርሱም እርስ በርሳቸው
ሳይስማሙ ተለያዩ ። ጳውሎስ ለመጨረሻ ጊዜ
ሲናገር እንዲህ አለ ፣ “መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ
በኢሳይያስ አማካይነት ለአባቶቻችሁ የተናገረው
ልክ ነበር ፤ 26 የተናገረውም ቃል ይህ ነው ፤

‘ወደዚህ ሕዝብ ሂድና
መስማትስ ትሰማላችሁ ፤ ግን
አታስተውሉም ፤
ማየትስ ታያላችሁ ፤ ግን ልብ
አታደርጉም በላቸው ፤
27 ምክንያቱም የእነዚህ ሰዎች ልብ
ደንድኖአል ፤
ጆሮአቸውም ተደፍኖአል ፤
ዐይናቸውም ተዘግቶአል ፤
እንዲህስ ባይሆን ኖሮ ፣
በዐይናቸው አይተው ፣
በጆሮአቸው ሰምተው ፣
በልባቸው አስተውለው ፣
ወደ እኔ በተመለሱና
በፈወስኩአቸው ነበር ።’

28 “እንግዲህ የእግዚአብሔር የደኅንነት
መልእክት ለአረማውያን እንደተላከ ዕወቁ ፤ እነ
ርሱም እሺ ብለው ይቀበሉታል ።”[a*]
30 ጳውሎስ በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት
ሙሉ ተቀመጠ ፤ ወደ እርሱ የሚመጡትን ሰዎች
ሁሉ ይቀበል ነበር ፤ 31 የእግዚአብሔርንም መን
ግሥት በመስበክ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ
ማንም ሳይከለክለው በድፍረት ያስተምር ነበር ።

[a*] 28፥28 አንዳንድ የጥንት መጻሕፍት የሚከተለውን ይጨምራሉ ፤ ቍ. 29 “ጳውሎስ ይህን ከተናገረ በኋላ አይሁዳውያን በብርቱ እየተከራከሩ ከዚያ ወጥተው ሄዱ ።”

28፥19 ፦ ሐ.ሥ. 25፥11 ። 28፥26-27 ፦ ኢሳ. 6፥9-10 ።

# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
# ወደ ሮም ሰዎች

## መግቢያ

የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮም ሰዎች የተጻፈው ጳውሎስ በሮም የምትገኘውን ቤተ ክርስቲያን ለመጐብኘት ዕቅድ ስለነበረው ተዘጋጅተው እንዲጠብቁት ለማድረግ ነው ። የጳውሎስ ዕቅድ በሮም ከሚገኙት ምእመናን ጋር ለጥቂት ጊዜ ከሠራ በኋላ በእነርሱ ረዳትነት ወደ ስፔን ለመሄድ ነበር ፤ ስለ ክርስትና እምነት የተረዳውንና ክርስቲያኖች በሕወታቸው ተግባራዊ ስለሚያደርጉበትም ሁኔታ በመዘርዘር ጽፎአል ፤ የጳውሎስ መልእክት በተሟላ ሁኔታ የሚገኘው በዚህ መልእክት ነው ።

ጳውሎስ በሮም ለሚገኙት ምእመናን ሰላምታውን ካስተላለፈና እንደሚጸልይላቸውም ተስፋ ከሰጣቸው በኋላ የመልእክቱ ማእከላዊ አሳብ “የወንጌል ቃል እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያጸድቀው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት መሆኑን ይገልጣል” (1፥17) የሚለው ቃል መሆኑን ያመለክታል ።

ከዚህ በኋላ ጳውሎስ ይህንኑ አሳብ በማስፋፋት ይጽፋል ፤ አይሁዳውያንም ሆኑ አረማውያን ሰዎች ሁሉ የኃጢአት ተገዥዎች ስለሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ይኖርባቸዋል ፤ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ሊታረቁ የሚችሉትም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው ፤ የዚህም ከእግዚአብሔር ጋር የሚመሠረቱት አዲስ ኅብረት ውጤት አዲስ ሕይወት ስለመሆኑ ጳውሎስ በሰፊው ያስረዳል ። አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ይኖረዋል ፤ በእግዚአብሔርም መንፈስ አማካይነት ከኃጢአትና ከሞት ኀይል ነፃ ወጥቶአል ፤ ከም. 5-8 ጳውሎስ የእግዚአብሔርና በአማኞች ሕይወት የሚሠራው የእግዚአብሔር መንፈስ ኀይል ዓላማው ምን እንደሆነ ይገልጣል ፤ ከዚህም በመቀጠል ጳውሎስ “እግዚአብሔር ለሰው ዘር ባለው ዕቅድ ውስጥ አይሁዳውያንና አረማውያን እንዴት ሊጣመሩ ይችላሉ?” ከሚለው ጥያቄ ጋር በመታገል ላይ ይገኛል ።

እንደገናም አይሁዳውያን ኢየሱስን ሳይቀበሉ መቅረታቸው የእግዚአብሔር ዕቅድ መሆኑን ይገልጣል ፤ ምክንያቱም በዚህ ሁኔታ የሰው ዘር ሁሉ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በገለጠው ጸጋ ውስጥ ሊታቀፍ ይችላል ፤ ይሁን እንጂ አይሁዳውያን ኢየሱስን የሚቀበሉበት ጊዜ እንደሚመጣ ጳውሎስ ያምናል ፤ በመጨረሻ ጳውሎስ የክርስትናን ሕይወት እንዴት መኖር እንደሚገባ ፣ በተለይም ምእመናን እርስ በርስ ባላቸው ግንኙነት የፍቅርን መንገድ መከተል እንደሚገባቸው ያስረዳል ፤ እግዚአብሔርን ስለማገልገል ፣ ክርስቲያኖች ለአገራቸውና እርስ በርሳቸውም ስላላቸው ኀላፊነትና ፣ በኅሊና ምክንያት ስለሚነሡ ጥያቄዎች በመዘርዘር ያስረዳል ።

---

## ምዕራፍ 1

1 የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ከሆነው ፣ ለሐ
ዋርያነት ከተጠራው ፤ የምሥራቹን ቃል ለማብ
ሠር ከተመረጠው ከጳውሎስ የተላከ ።
2 ይህ የምሥራች ቃል እግዚአብሔር በነቢ
ያት አማካይነት በቅዱሳት መጻሕፍት አስቀ
ድሞ የሰጠው የተስፋ ቃል ነው ። 3 የምሥራ
ቹም ቃል የእግዚአብሔር ልጅ በሰብአዊነቱ
በኩል ፣ ከዳዊት ዘር መወለዱን የሚያበሥር
ነው ፤ 4 እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
በቅድስናው መንፈስ በኩል በታላቅ ኀይል
ከሞት በመነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን
የሚያበሥር ነው ። 5 በእርሱ አማካይነት ለሐዋ
ርያነት የሚያበቃኝን ጸጋ ተቀብያለሁ ፤ ስለዚህ
ስለ እርሱ ስም አረማውያን ሁሉ እንዲያምኑና
እንዲታዘዙ አደርጋለሁ ፤ 6 እናንተም የኢየሱስ
ክርስቶስ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ከጠራቸው
ወገን ናችሁ ።
7 ስለዚህ በሮም ለምትኖሩ ፣ እግዚአብሔር
ለወደዳችሁና ወገኖቹ እንድትሆኑ ለጠራችሁ
ሁሉ ።
ከአባታችን ከእግዚአብሔርና ከጌታ ከኢየሱስ
ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን ።

### የምስጋና ጸሎት

8 የእምነታችሁ ዝና በዓለም ሁሉ ስለ
ተሰማ ፣ ከሁሉ አስቀድሜ በኢየሱስ ክርስቶስ
አማካይነት ስለ ሁላችሁ አምላኬን አመሰግና
ለሁ ። 9 ዘወትር በጸሎቴ እንደማስባችሁ ፣ የል

ጁን የምሥራች ቃል በማብሠር በሙሉ ልቤ
የማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነው ።
10 ደግሞ አሁን በመጨረሻ ወደ እናንተ ከመም
ጣት የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ መንገዱ እን
ዲቃናልኝ ሁልጊዜ እጸልያለሁ ። 11 ምክንያ
ቱም በእምነት እንድትጸኑ የሚያደርጋችሁን
መንፈሳዊ ስጦታ ላካፍላችሁ ስለምፈልግ ላያ
ችሁ እመኛለሁ ። 12 ይህንንም ማለቴ እኔ በእና
ንተ እምነት ፣ እናንተም በእኔ እምነት እርስ
በእርሳችን እንድንጽናና ነው ።
13 ወንድሞቼ ሆይ! በሌሎች አረማውያን
መካከል አስተምሬ ብዙ አማኞችን እንዳገኘ
ሁ ፤ እንዲሁም በእናንተ መካከል አስተምሬ
አማኞችን ለማግኘት ፈልጌ ነበር ፤ ነገር ግን
ወደ እናንተ ለመምጣት ብዙ ጊዜ ዐቅጄ እስከ
አሁን ያልተሳካልኝ መሆኑን እንድታውቁ እወ
ዳለሁ ። 14 ምክንያቱም የሠለጠኑትንም ሆነ
ያልሠለጠኑትን ፣ የተማሩትንም ሆነ ያልተማሩ
ትን ሕዝቦች የማስተማር ግዴታ አለብኝ ።
15 ስለዚህ ለእናንተም በሮም ለምትኖሩ የምሥ
ራቹን ቃል ላበሥራችሁ እመኛለሁ ።

የወንጌል ቃል የእግዚአብሔር ኀይል ነው

16 እኔ በወንጌል ቃል አላፍርም ፤ ምክንያ
ቱም የወንጌል ቃል በመጀመሪያ አይሁዳውያ
ንን ፣ ቀጥሎም አረማውያንን ፣ የሚያምኑትን
ሰዎች ሁሉ ማዳን የሚችል የእግዚአብሔር
ኀይል ነው ። 17 ይህም የወንጌል ቃል እግዚአብ
ሔር ሰዎችን የሚያጸድቀው ከመጀመሪያ እስከ
መጨረሻ በእምነት መሆኑን ይገልጣል ፤ ምክን
ያቱም "ጻድቅ ሰው በእምነት ሕይወትን ያገ
ኛል" ተብሎ ተጽፎአል ።

የሰዎች ክፋት

18 ሰዎች በክፋታቸው እውነት እንዳይታወቅ
ሲያደርጉ በኀጢአታቸውና በክፋታቸው ምክን
ያት የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጥባቸ
ዋል ። 19 የሚቀጣቸውም ስለ እግዚአብሔር
ማወቅ የሚገባቸውን እግዚአብሔር ራሱ ገልጦ
ላቸው ያውቁ ስለነበር ነው ። 20 ዓለም ከተፈ
ጠረ ጀምሮ ለሰዎች የማይታየው የእግዚአብ
ሔር ባሕርይ ፣ ይኸውም ዘላለማዊው ኀይሉና
አምላክነቱ ፣ እርሱ በፈጠራቸው ነገሮች ግልጥ
ሆኖ ታይቶአል ፤ ስለዚህ እንደእነዚህ ያሉት የዐ
ዋቂ አጥፊዎች የሚያመካኙት የላቸውም ።
21 ምክንያቱም እነርሱ እግዚአብሔርን ዐውቀ
ውት ሳለ ለእርሱ የሚገባውን ክብርና ምስጋና
አልሰጡትም ፤ በአሳባቸውም ከንቱ ሆኑ ፤ የማያ
ስተውል ልቦናቸውም ጨለመ ፤ 22 "ጥበበኞች
ነን" ሲሉ ሞኞች ሆኑ ። 23 ዘላለማዊ የሆነውን
እግዚአብሔርን በማምለክ ፈንታ አላፊና ጠፊ
በሆኑት በሰው ፣ በወፍ ፣ በእንስሳ ፣ በመሬት
ላይ በሚሳቡ ፍጥረቶች መልክ የተሠሩትን ምስ
ሎች ማምለክ ጀመሩ ።
24 ስለዚህ እርስ በርሳቸው አሳፋሪ ድርጊቶ
ችን እንዲፈጽሙ ፣ እግዚአብሔር ርኵሰት ለሞ
ላበት ለክፉ ምኞታቸው ተገዥዎች እንዲሆኑ
ተዋቸው ። 25 ይህም የሆነው የእግዚአብሔርን
እውነት በሐሰት ስለለወጡ ፣ በፈጣሪ ፈንታ
ፍጡርን ስላመለኩና ስለአገለገሉ ነው ፤ እግዚአ
ብሔር ግን ለዘላለም የተመሰገነ ነው ፤ አሜን ።
26 ሰዎች ይህን በማድረጋቸው ምክንያት እግ
ዚአብሔር ለማይገባ አስነዋሪ ምኞት አሳልፎ
ሰጣቸው ፤ ሴቶቻቸው እንኳ የተለመደውን የግ
ብረ ሥጋ ግንኙነት ባልተለመደ የግብረ ሥጋ
ግንኙነት ለወጡ ። 27 እንዲሁም ወንዶቹ የተለ
መደውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሴቶች ጋር
ማድረግን ትተው እርስ በርሳቸው በግብረ ሥጋ
ለመገናኘት በብርቱ ተመኙ ፤ ስለዚህ ወንዶች
ከወንዶች ጋር አሳፋሪ ነገር ፈጸሙ ፤ በስሕተታ
ቸውም ምክንያት የሚገባቸውን ቅጣት በሥጋ
ቸው ይቀበላሉ ።
28 ሰዎች እግዚአብሔርን ለማወቅ ስላልፈ
ለጉ ፣ አስነዋሪ ነገር እንዲያደርጉ እግዚአብሔር
ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው ። 29 ስለዚህ
በግፍ ፣ በክፋት ፣ በስስት ፣ በቂም ፣ በምቀኝ
ነት ፣ በነፍሰገዳይነት ፣ በጥል ፣ በአታላይነት ፣
በክፉ ጠባይ ሁሉ የተሞሉ ናቸው ፤ እንዲሁም
ሐሜተኞች ፣ 30 የሰውን ስም የሚያጠፉ ፣ እግዚ
አብሔርን የሚጠሉ ፣ ሰውን የሚያዋርዱ ፣ ትዕ
ቢተኞች ፣ ትምክሕተኞች ፣ ክፋትን ለማድረግ
ዘዴ የሚፈልጉ ፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ ፣
31 የማያስተውሉ ፣ ውል የሚያፈርሱ ፣ ፍቅር
የሌላቸው ፣ ጨካኞች ናቸው ። 32 "እነዚህን ነገ
ሮች የሚያደርጉ ሁሉ ሞት ይገባቸዋል" የሚለ
ውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ ይህን ሁሉ
ያደርጋሉ ፤ ማድረግ ብቻ ሳይሆን እንዲህ የሚያ
ደርጉትንም ሰዎች ያበረታታሉ ።

## ምዕራፍ 2

የእግዚአብሔር ፍርድ

1 በሌላው ሰው ላይ የምትፈርድ አንተ ፣ ለራ
ስህ የምታመካኘው የለህም ፤ ምክንያቱም በሌ
ላው ሰው ስትፈርድ በራስህ ላይ ትፈርዳለህ ፤
አንተ በሰው ላይ እየፈረድህ ያ የፈረድህበት
ሰው የሚያደርገውን ታደርጋለህ ። 2 ይህን በሚ
ያደርጉ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር በሚገባ እንደ
ሚፈርድባቸው እናውቃለን ። 3 አንተ ሰው! እን
ዲህ በሚያደርጉት ሰዎች ላይ እየፈረድህ ፣ እነ
ርሱ የሚያደርጉትን ስታደርግ ከእግዚአብሔር





ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሃልን? 4 ወይስ የእ
ግዚአብሔርን የደግነቱንና የቻይነቱን ፣ የታጋሽ
ነቱንም ብዛት ትንቃለህን? እግዚአብሔር ደግነ
ቱን ያበዛልህ አንተን ወደ ንስሓ ለመጥራት እን
ደሆነ አታውቅምን? 5 እንግዲህ አንተ ንስሓ ባለ
መግባትህና እልኸኛ በመሆንህ የእግዚአብሔር
ቍጣና ትክክለኛ ፍርድ በሚገለጥበት ቀን ቅጣ
ትህ እንዲበዛ ታደርጋለህ ። 6 ምክንያቱም እግዚ
አብሔር ለእያንዳንዱ እንደየሥራው ይሰጠ
ዋል ። 7 በመልካም ሥራ በመጽናት ምስጋናና
ክብርን የማይጠፋ ሕይወትንም ለሚፈልጉ ፣
እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸ
ዋል ። 8 ነገር ግን የራሳቸውን ጥቅም በሚፈ
ልጉ ፣ ዐመፀኞች በሆኑትና ትክክለኛ የሆነውን
መልካም ነገር ትተው ክፋትን በሚከተሉት
ላይ የእግዚአብሔር ቍጣና መቅሠፍት ይመጣ
ባቸዋል ። 9 በመጀመሪያ በአይሁዳውያን ፣ ቀጥ
ሎም በአረማውያን ፣ ክፋት በሚያደርጉ ሰዎች
ላይ መከራና ጭንቀት ይመጣባቸዋል ። 10 ነገር
ግን ለአይሁዳውያንም ሆነ ለአረማውያን ፣ መል
ካም ነገርን ለሚያደርጉ ሰዎች ሁሉ ምስጋናና
ክብር ሰላምም ይሰጣቸዋል ። 11 ምክንያቱም
እግዚአብሔር በሰዎች መካከል አያዳላም ።
12 የሙሴ ሕግ ሳይኖራቸው ኀጢአት የሚ
ሠሩ ሁሉ ሕጉ ባይኖራቸውም ይጠፋሉ ፤
የሙሴ ሕግ እያላቸው ኀጢአት የሚሠሩ ሁሉ
ግን ሕጉን በማፍረሳቸው ይፈረድባቸዋል ።
13 ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት የሚጸድቁ
ሕጉን ሰምተው በሥራ ላይ የሚያውሉት
ናቸው እንጂ ሕጉን ሰምተው በሥራ ላይ የማያ
ውሉት አይደሉም ። 14 የሙሴ ሕግ የሌላቸው
አረማውያን በተፈጥሮአቸው ሕግ የሚያዝዘውን
ነገር ይፈጽማሉ ፤ በዚህ ምክንያት የሙሴ ሕግ
ባይኖራቸውም የራሳቸው የተፈጥሮ ሕግ ስላላ
ቸው ማድረግ የሚገባቸውን ያውቃሉ ።
15 ይህም ሁኔታቸው የሙሴ ሕግ የሚያዝዘው
ነገር ሁሉ በልባቸው የተጻፈ መሆኑን ያሳያል ፤
ደግሞም ኅሊናቸው ይመሰክርባቸዋል ፤ ምክንያ
ቱም ኅሊናቸው አንዳንዴ ይወቅሳቸዋል ፤ አንዳ
ንዴም ይደግፉቸዋል ። 16 ይህም የሚሆነው እኔ
በማበሥረው የወንጌል ቃል መሠረት ፣ እግዚአ
ብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ፣ ሰዎች
በሠሩት ስውር ነገር ላይ በሚፈርድበት ቀን
ነው ።

አይሁዳውያንና የሙሴ ሕግ

17 እነሆ አንተ "አይሁዳዊ ነኝ" ትላለህ ፤
በሙሴ ሕግ ትደገፋለህ ፤ የእግዚአብሔር በመሆ
ንህም ትመካለህ ። 18 አንተ የእግዚአብሔርን
ፈቃድ ታውቃለህ ፤ የሙሴን ሕግ ስለተማርህ
መልካም ማድረግን ታውቃለህ ። 19 አንተ "የዕ
ውሮች መሪ ነኝ ፤ በጨለማ ላሉትም ብርሃን
ነኝ" ትላለህ ። 20 አንተ "ያልተማሩትን አሠለጥ
ናለሁ ፤ ሕፃናትን አስተምራለሁ" ትላለህ ፤ እን
ዲሁም "ሕግ ፣ ዕውቀትና እውነት የሞላበት
ነው" ትላለህ ። 21 ሌሎችን የምታስተምር ስት
ሆን ታዲያ ራስህን ለምን አታስተምርም?
"አትስረቁ" ትላለህ ፣ አንተ ግን ትሰርቃለህ ፤
22 "አታመንዝሩ" ትላለህ ፤ አንተ ግን ታመነዝ
ራለህ ፤ አንተ ጣዖቶችን ትጸየፋለህ ፤ ቤተ መቅ
ደሶቻቸውን ግን ትዘርፋለህ ። 23 አንተ በእግዚአ
ብሔር ሕግ ትመካለህ ፤ ነገር ግን ሕጉን በማፍ
ረስ እግዚአብሔርን ትንቃለህ ። 24 ይህም ፣
"በእናንተ በአይሁዳውያን ሰበብ የእግዚአብ
ሔር ስም በአረማውያን ዘንድ ይሰደባል"
ተብሎ እንደተጻፈው ነው ።
25 መገረዝ የሚጠቅምህ ሕግን ብትፈጽም
ነው ፤ ሕግን የምታፈርስ ከሆነ ግን መገረዝህ
እንደ አለመገረዝ ይቈጠራል ። 26 ስለዚህ ያልተ
ገረዘው አረማዊ የሕግን ትእዛዝ የሚፈጽም
ከሆነ አለመገረዙ እንደ መገረዝ ይቈጠርለት የለ
ምን? 27 አንተ ሕግ እያለህና የተገረዝህም ሆነህ
ሕግን ብታፈርስ ፣ በሥጋ ያልተገረዘ ሆኖ ሕግን
የሚፈጽም አረማዊ ይፈርድብሃል ። 28 እንግዲህ
በስም ብቻ አይሁዳዊ የሆነ ፣ እውነተኛ አይሁ
ዳዊ አይደለም እንዲሁም በውጭ የሚታይ
የሥጋ መገረዝ እውነተኛ መገረዝ አይደለም ።
29 እውነተኛ አይሁዳዊ ፣ በውስጥ አይሁዳዊ
የሆነ ነው ፤ እውነተኛ መገረዝ ፣ በእግዚአብ
ሔር መንፈስ የሚሆን የልብ መገረዝ ነው
እንጂ በሙሴ ሕግ በተጻፈው መሠረት የሥጋ
መገረዝ አይደለም ። እንዲህ ዐይነቱም ሰው
ምስጋናን የሚቀበለው ከእግዚአብሔር ነው
እንጂ ከሰው አይደለም ።

## ምዕራፍ 3

አይሁዳውያን ባለማመናቸው በድለዋል

1 እንግዲህ አይሁዳዊ ከአረማዊ የሚበልጠው
በምንድን ነው? የመገረዝስ ጥቅም ምንድን
ነው? 2 በእርግጥ አይሁዳዊ መሆን በብዙ መን
ገድ ብልጫ አለው ፤ ዋናው ነገር ፣ እግዚአብ
ሔር ቃሉን ለአይሁዳውያን ዐደራ መስጠቱ
ነው ። 3 ታዲያ ከአይሁዳውያን አንዳንዶቹ ታማ
ኞች ሆነው ባይገኙ ፣ የእነርሱ ታማኞች አለመ
ሆን የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን?
4 ከቶ አያስቀርም!
"ከቃልህ የተነሣ እውነተኛ ትሆናለህ ፤
ባላጋራህንም በፍርድ ትረታለህ"
ተብሎ እንደተጻፈው ፣ ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ቢሆ
ንም እግዚአብሔር እውነተኛ ነው ።

2፥6 ፦ መዝ. 62፥12 ፤ ምሳ. 24፥12 ። 2፥11 ፦ ዘዳ. 10፥17 ። 2፥24 ፦ ኢሳ. 52፥5 ። 2፥29 ፦ ዘዳ. 30፥6 ።
3፥4 ፦ መዝ. 51፥4 ።

5 ነገር ግን የእኛ ኃጢአት የእግዚአብሔርን
ጽድቅ የሚያሳይ ከሆነ እንግዲህ ምን እንላለን?
እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችን ቢቀጣን ትክክ
ለኛ ፈራጅ አይደለም ማለት ነውን? እዚህ ላይ
የምናገረው እንደ ሰው አስተሳሰብ ነው ።
6 “እግዚአብሔር ትክክለኛ ፈራጅ አይደለም”
ማለት ከቶ አይቻልም ፤ እንዲህ ከሆነማ እግዚአ
ብሔር በዓለም ላይ እንዴት ይፈርዳል?
7 ነገር ግን የእኔ ሐሰተኛነት የእግዚአብሔ
ርን እውነት በመግለጥ የክብሩን ብዛት የሚያ
ሳይ ከሆነ ፥ ታዲያ እኔ እንደ ኃጢአተኛ የሚፈ
ረድብኝ ስለ ምንድን ነው? 8 አንዳንድ ሰዎች
“መልካም ነገር እንድናገኝ ክፉ ነገር እናድ
ርግ” እያልሁ የማስተምር አስመስለው ይከሱ
ኛል ፤ ስለዚህ በእነርሱ ላይ የሚፈረድባቸው
ፍርድ ትክክለኛ ነው ።

### ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ነው

9 ታዲያ እኛ አይሁዳውያን ከአረማውያን
እንበልጣለን ማለት ነውን? ከቶ አይደለም! አይ
ሁዳውያንም ሆኑ አረማውያን ፥ ሰዎች ሁሉ
ኃጢአተኞች መሆናቸውን ቀደም ብዬ አስረድ
ቻለሁ ። 10 ምክንያቱም እንዲህ ተብሎ ተጽፎ
አል ፦

“አንድ እንኳ ጻድቅ ሰው የለም ፤
11 አስተዋይም የለም ፤
እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም ።
12 ሁሉም ከእውነት መንገድ ወጥተው
ተሳስተዋል ፤
ደግ ሥራ የሚሠራ አንድ ሰው እንኳ
የለም ።
13 ሰውን የሚጐዳ ክፉ ቃል ለመናገር
አፋቸው እንደ መቃብር የተከፈተ
ነው ፤
በምላሳቸው ያታልላሉ ፤
የከንፈራቸውም ንግግር እንደ እባብ
መርዝ የሚጐዳ ነው ፤
14 አፋቸው በመራራ እርግማን የተሞላ
ነው ።
15 እግራቸው ሰውን ለመግደል የፈጠነ
ነው ፤
16 በመንገዳቸው የሚገኘው ጥፋትና
መከራ ነው ።
17 የሰላምን መንገድ አያውቁም ፤
18 እግዚአብሔርን ከቶ አይፈሩም ።”

19 የሕግ ትእዛዝ የሚመለከተው ከሕግ
በታች ያሉትን እንደሆነ እናውቃለን ፤ በዚህ
ምክንያት ሰዎች የሚያመካኙት አጥተው አፋ
ቸውን ይይዛሉ ፤ ዓለሙም ሁሉ በእግዚአብሔር
ፍርድ ሥር ይሆናል ። 20 ስለዚህ ማንም ሰው
በእግዚአብሔር ፊት የሙሴን ሕግ በመፈጸም
አይጸድቅም ፤ ምክንያቱም ሕግ የሚያሳየው ፥
ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን ነው ።

### ሰው ሁሉ የሚጸድቀው በእምነት ነው

21 አሁን ግን እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያጸ
ድቅበት መንገድ ከሕግ ነፃ ሆኖ ተገልጦአል ፤
ይህም በሙሴ ሕግና በነቢያት ተመስክሮአል ።
22 ስለዚህ እግዚአብሔር ምንም ልዩነት ሳያደ
ርግ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ጽድ
ቅን ይሰጣል ። 23 ምክንያቱም ሰዎች ሁሉ ኃጢ
አት ሠርተዋል ፤ እግዚአብሔር የሰጣቸውንም
ክብር አጥተዋል ። 24 ስለዚህ ሰዎች ኢየሱስ ክር
ስቶስ በፈጸመው በአዳኝነት ሥራ ፥ በእግዚአብ
ሔር ጸጋ ብቻ ይጸድቃሉ ። 25 እግዚአብሔር
ኢየሱስ ክርስቶስን መሥዋዕት አድርጎ ያቀረ
በው ፤ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ በደሙ የኃጢአ
ታቸውን ይቅርታ እንዲያገኙ ነው ፤ እግዚአብ
ሔር ይህን ማድረጉ የቀድሞውን ኃጢአት እን
ዳልነበረ በመቍጠር የራሱን የጽድቅ መንገድ
ለመግለጥ ነው ። 26 በአሁኑም ዘመን እግዚአብ
ሔር ራሱ ጻድቅ መሆኑን የሚያሳየው በኢየሱስ
የሚያምኑትን ሁሉ በማጽደቅ ነው ።
27 እንግዲህ የምንመካበት ነገር ምን አለ?
በምንም አንመካም ፤ የማንመካበትስ ምክንያት
ምንድን ነው? ሕግን ስለምንፈጽም ነውን? አይ
ደለም ፤ ነገር ግን በእምነት ብቻ ነው ። 28 ስለ
ዚህ እግዚአብሔር ሰውን የሚያጸድቀው ፥ ሰው
የሕግን ሥራ በመፈጸሙ ሳይሆን ፥ በእምነት
መሆኑን እንገነዘባለን ። 29 ወይስ እግዚአብሔር
የአይሁዳውያን ብቻ አምላክ ነውን? የአረማው
ያንስ አምላክ አይደለምን? በእርግጥ የአረማው
ያንም አምላክ ነው ። 30 እግዚአብሔር አንድ
ነው ፤ አይሁዳውያንንም ሆነ አረማውያንን ፥
በእምነት የሚያጸድቅ እርሱ ነው ። 31 ታዲያ
በእምነት ምክንያት ሕግን እንሽራለን ማለት
ነውን? አይደለም! ይልቁንም ሕግን እጥብቀን
እንይዛለን ።

## ምዕራፍ 4

### አብርሃም በእምነት ጸደቀ

1 እንግዲህ የቀድሞው አባታችን አብርሃም
አገኘ የምንለው ምንድን ነው? 2 አብርሃም የጸ
ደቀው በሥራ ቢሆን ኖሮ የሚመካበት ነገር
ባገኘ ነበር ፤ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ፊት
መመካት አይችልም ። 3 ምክንያቱም “አብር
ሃም በእግዚአብሔር ስላመነ እምነቱ ጽድቅ

3፥10-12 ፡- መዝ. 14፥1-3 ፤ 53፥1-3 ። 3፥13 ፡- መዝ. 5፥9 ፤ 140፥3 ። 3፥14 ፡- መዝ. 10፥7 ።
3፥15-17 ፡- ኢሳ. 59፥7-8 ። 3፥18 ፡- መዝ. 36፥1 ። 3፥20 ፡- መዝ. 143፥2 ፤ ገላ. 2፥16 ። 3፥22 ፡- ገላ. 2፥16 ።
3፥30 ፡- ዘዳ. 6፥4 ፤ ገላ. 3፥20 ። 4፥3 ፡- ዘፍ. 15፥6 ፤ ገላ. 3፥6 ።



ሆኖ ተቈጠረለት” ተብሎ ተጽፎአል ። 4 የሚ
ሠራ ሰው የሚያገኘው ደመወዝ ፥ ተገቢ የጕል
በቱን ዋጋ ነው እንጂ ስጦታ አይደለም ። 5 ሰው
መልካም ሥራ ባይኖረው እንኳ ኃጢአተኞችን
በሚያጸድቅ አምላክ ካመነ ፥ እምነቱ ጽድቅ
ሆኖ ይቈጠርለታል ። 6 ዳዊትም በበኩሉ እግዚ
አብሔር ያለ መልካም ሥራ የሚያጸድቀው
ሰው ምን ያህል የተባረከ መሆኑን ሲገልጥ እን
ዲህ ብሎአል ፦
7 “በደላቸው ይቅር የተባለላቸውና
ኃጢአታቸው የተደመሰሰላቸው ሰዎች
የተባረኩ ናቸው!
8 እግዚአብሔር ኃጢአቱን የማይቈጥርበት
ሰው
የተባረከ ነው!”
9 ታዲያ ዳዊት የተናገረው ይህ በረከት ለተገ
ረዙት ብቻ ነውን ወይስ ላልተገረዙትም? ላል
ተገረዙትም ነው ፤ ምክንያቱም “አብርሃም በእ
ግዚአብሔር ስላመነ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ተቈ
ጠረለት” ብለናል ።
10 እንግዲህ አብርሃም እምነቱ ጽድቅ ሆኖ
የተቈጠረለት መቼ ነው? ከመገረዙ በፊት
ነውን ወይስ ከተገረዘ በኋላ? ከመገረዙ በፊት
ነው እንጂ ከተገረዘ በኋላ አይደለም ። 11 አብር
ሃም ገና ከመገረዙ በፊት እምነቱ ጽድቅ ሆኖ
እንደተቈጠረለት ማረጋገጫ ምልክት እንዲሆ
ነው ተገረዘ ፤ ስለዚህ አብርሃም ፥ ሳይገረዙ ለሚ
ያምኑና እምነታቸው ጽድቅ ሆኖ ለሚቈጠርላ
ቸው ሁሉ አባት ነው ። 12 እንዲሁም አብርሃም
ለተገረዙትም አባት ነው ፤ ለተገረዙት አባት
የሆነበትም ምክንያት በመገረዛቸው ብቻ ሳይ
ሆን ፥ እርሱ ከመገረዙ በፊት የነበረውን እም
ነት በመከተላቸው ነው ።

### ስለ እምነት የተሰጠ ተስፋ

13 አብርሃም ከነዘሩ ዓለምን እንደሚወርስ
እግዚአብሔር ተስፋ ሰጠው ፤ ይህም ተስፋ የተ
ገኘው አብርሃም ሕግን በመፈጸሙ ሳይሆን ስላ
መነና እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ስለተቈጠረለት
ነው ። 14 የተስፋው ወራሾች ሕግን የሚፈጽሙ
ሰዎች ከሆኑማ እምነት ዋጋ አይኖረውም ፤ ተስ
ፋም ከንቱ መሆኑ ነው ። 15 ሕግ የሚያመጣው
የእግዚአብሔርን ቍጣ ነው ፤ ሕግ ከሌለ ግን
ሕግን የመተላለፍ በደል አይኖርም ።
16 ተስፋም የተመሠረተው በእምነት ላይ
ነበር ፤ ስለዚህ የአብርሃም ዘሮች ሁሉ ይህን የተ
ረጋገጠ ተስፋ በጸጋ ይወርሳሉ ፤ ይህም ማለት
በሕግ የሚጸድቁት ብቻ ሳይሆኑ እንደ አብር
ሃም በእምነት የጸደቁትም ናቸው ፤ ምክንያ
ቱም አብርሃም በእምነት ረገድ የሁላችንም
አባት ነው ። 17 ይህም የሆነው “የብዙ ሕዝብ
አባት አድርጌሃለሁ” ተብሎ በተጻፈው መሠ
ረት ነው ። ስለዚህ አብርሃም ባመነው ፥ የሞቱ
ትን በሚያስነሣውና የሌለውን እንዲኖር በሚያ
ደርገው አምላክ ፊት ተስፋው የጸና ነው ።
18 አብርሃም ያመነውና ተስፋ ያደረገው ምንም
ተስፋ ባልነበረበት ጊዜ ነው ፤ ስለዚህ “ዘርህ
ይህን ያህል ይበዛል” ተብሎ በተጻፈው መሠ
ረት የብዙ ሕዝብ አባት ሆነ ። 19 ዕድሜው
መቶ ዓመት ያህል ስለነበረ በሥጋው መድከም
ምክንያት መውለድ እንደማይችልና ፥ ሣራም
መኻንና ያረጀች በመሆንዋ መውለድ እንደማት
ችል ቢያውቅም ፥ በእምነቱ ደካማ አልሆነም ።
20 በእምነቱ ብርቱ ሆኖ ለእግዚአብሔር ክብር
ሰጠ እንጂ እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ ባለማ
መን ከቶ አልተጠራጠረም ። 21 ምክንያቱም እግ
ዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ የሚፈጽም መሆኑን
ስለተረዳ ነው ። 22 እንግዲህ አብርሃም እምነቱ
ጽድቅ ሆኖ የተቈጠረለት ስለዚህ ነው ። 23 ነገር
ግን “ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት” የሚለው ቃል
የተጻፈው ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን ፥ 24 ለእኛም
ጭምር ነው ፤ ጌታችን ኢየሱስን ከሞት ባስነ
ሣው አምላክ ለምናምን ለእኛም ፥ እምነታችን
ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርልናል ። 25 ይህ ጌታችን
ኢየሱስም ስለ ኃጢአታችን ለሞት ተላልፎ የተ
ሰጠውና እኛንም ለማጽደቅ ከሞት የተነሣው
ነው ።

## ምዕራፍ 5

### በእምነት የሚገኝ ሰላምና ዕርቅ

1 እንግዲህ እኛ ጽድቅን ያገኘነው በእምነት
ስለሆነ ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአ
ብሔር ጋር ሰላም አለን ። 2 ወደዚህ አሁን ጸን
ተን ወደምንገኝበት ጸጋ በእምነት የገባነው በእ
ርሱ ነው ፤ በተስፋ የእግዚአብሔር ክብር ተካ
ፋዮች በመሆናችንም ደስታና ትምክሕት
አለን ። 3 በዚህ ብቻ ሳይሆን በመከራችንም እን
ደሰታለን ፥ እንመካለንም ፤ ምክንያቱም ከመከራ
ትዕግሥት እንደሚገኝ እናውቃለን ፤ 4 ከትዕግሥ
ትም መጽናት ፥ ከመጽናትም ተስፋ ይገኛል ።
5 በተሰጠን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የእግዚ
አብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ሞላ ተስፋው አያ
ሳፍርም ።
6 ገና ደካሞች ሆነን ሳለ ፥ እግዚአብሔር
በወሰነው ጊዜ ክርስቶስ ስለ ኃጢአተኞች
ሞተ ። 7 በጻድቅ ምትክ ሆኖ የሚሞት ሰው
ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው ፤ ሆኖም በደግ
ሰው ምትክ ለመሞት የሚደፍር ምናልባት
ይገኝ ይሆናል ። 8 ነገር ግን እኛ ኃጢአተኞች

4፥7-8 ፡- መዝ. 32፥1-2 ። 4፥11 ፡- ዘፍ. 17፥10 ። 4፥13 ፡- ዘፍ. 17፥4-6 ፤ 22፥17-18 ፤ ገላ. 3፥29 ። 4፥14 ፡- ገላ. 3፥18 ።
4፥16 ፡- ገላ. 3፥7 ። 4፥17 ፡- ዘፍ. 17፥5 ። 4፥18 ፡- ዘፍ. 15፥5 ። 4፥19 ፡- ዘፍ. 17፥17 ። 4፥25 ፡- ኢሳ. 53፥4-5 ።

ሆነን ሳለ ክርስቶስ በእኛ ምትክ ሞቶአል ፤
ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር ምን
ያህል ታላቅ መሆኑን ያስረዳል ። 9 እንግዲህ የጸ
ደቅነው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከሆነ ይበልጡ
ንም ከእግዚአብሔር ቍጣ የምንድነው በእርሱ
አማካይነት ነው ። 10 ምክንያቱም እኛ የእግዚአ
ብሔር ጠላቶች ሆነን ሳለ በልጁ ሞት ከእግዚአ
ብሔር ጋር ታርቀናል ፤ አሁን ከእግዚአብሔር
ጋር ከታረቅን በኋላ በሕያው ልጁ አማካይነት
ይበልጡን እንድናለን ። 11 ይህም ብቻ ሳይሆን
ዕርቅን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
አማካይነትም በእግዚአብሔር እንመካለን ።

### ሞት በአዳም ፥ ሕይወት በክርስቶስ

12 በአንድ ሰው ምክንያት ኃጢአት ወደ
ዓለም ገባ ፤ በኃጢአት ምክንያትም ሞት
መጣ ፤ ይኸውም ሰው ሁሉ ኃጢአት ስለሠራ
ሞት በሰው ሁሉ ላይ መጣ ፤ 13 ምክንያቱም
የሙሴ ሕግ ከመሰጠቱ በፊት ኃጢአት በዓለም
ነበር ፤ ይሁን እንጂ ሕግ በሌለበት ፥ ኃጢአት
ራሱ እንደ ኃጢአት አይቈጠርም ። 14 ሆኖም
እንደ አዳም ሕግን በመተላለፍ ኃጢአት ባልሠ
ሩት ላይ እንኳ ሳይቀር ፥ ሞት ከአዳም አንሥቶ
እስከ ሙሴ በሰው ሁሉ ላይ ሥልጣን አገኘ ።
ይህ አዳም ወደፊት ለሚመጣው ክርስቶስ
ምሳሌ ነበረ ። 15 ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ
ከሰው ኃጢአት ይበልጣል ፤ በአንድ ሰው ኃጢ
አት ምክንያት ብዙዎች እንደሞቱ ፥ እንዲሁም
በእግዚአብሔር ጸጋና በአንዱ በኢየሱስ ክርስ
ቶስ ምክንያት የተገኘው ስጦታ ለብዙዎች በይ
በልጥ ተሰጥቶአል ። 16 እንዲሁም የእግዚአብ
ሔር ጸጋ ውጤት ከሰው ኃጢአት ውጤት ይበ
ልጣል ፤ በአንድ ኃጢአት ምክንያት የተሰጠው
ፍርድ ቅጣትን አመጣ ፤ በብዙ ኃጢአት ምክን
ያት የተሰጠው ጸጋ ጽድቅን አመጣ ። 17 በአ
ንድ ሰው ኃጢአት ምክንያት ሞት በሰው ላይ
ሥልጣን ካገኘ ፥ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ
አማካይነት የእግዚአብሔርን ብዙ ጸጋ ተቀብ
ለው የጸደቁ ሁሉ ፥ በድል አድራጊነት ሕይወት
ይኖራሉ ።
18 እንግዲህ የአንዱ የአዳም ኃጢአት የቅጣ
ትን ፍርድ በሰው ሁሉ ላይ እንዳመጣ ፥ እንዲ
ሁም የአንዱ የክርስቶስ የጽድቅ ሥራ ብዙዎ
ችን ከቅጣት ነፃ አድርጎ ሕይወትን ይሰጣል ።
19 በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት ብዙዎች
ኃጢአተኞች እንደሆኑ ፥ እንዲሁም በክርስቶስ
መታዘዝ ምክንያት ብዙዎች ይጸድቃሉ ።
20 ኃጢአት ይበዛ ዘንድ ሕግ መጣ ፤ ነገር ግን
ኃጢአት በበዛ መጠን የእግዚአብሔር ጸጋ በይበ
ልጥ በዛ ። 21 ይህም የሆነው በሞት ምክንያት
ኃጢአት እንደነገሠ ሁሉ ፥ እንዲሁም የእግዚአ
ብሔር ጸጋ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካ
ይነት በሚገኘው ዘላለማዊ ሕይወት ጽድቅን
በመስጠት ይነግሣል ።

## ምዕራፍ 6

### ከኃጢአት ተለይቶ በክርስቶስ መኖር

1 እንግዲህ ምን እንላለን? የእግዚአብሔር
ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን?
2 አይደለም! እኛ በሞት የመለየትን ያህል ከኃ
ጢአት የተለየን ሆነን ሳለ እንዴት በኃጢአት
ጸንተን እንኖራለን! 3 ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር
አንድ ለመሆን የተጠመቅን ሁሉ ፥ የሞቱም
ተካፋዮች ለመሆን መጠመቃችንን አታውቁ
ምን? 4 በጥምቀት ከእርሱ ጋር በተቀበርን ጊዜ
የእርሱ ሞት ተካፋዮች ሆነናል ፤ ስለዚህ ክርስ
ቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደተነሣ ፥ እኛም
በአዲስ ሕይወት እንኖራለን ።
5 በሞቱ እርሱን በመምሰል ከተባበርን ፥ በት
ንሣኤውም እርሱን እንደምንመስል የተረጋገጠ
ነው ። 6 ኃጢአተኛው ሰውነታችን እንዲወገድና
የኃጢአት ባሪያዎች መሆናችን እንዲቀር ፥ አሮ
ጌው ሰውነታችን ከክርስቶስ ጋር መሰቀሉን እና
ውቃለን ። 7 ምክንያቱም የሞተ ሰው ለኃጢአት
ከመገዛት ነፃ ነው ። 8 እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር
ከሞትን ፥ ከእርሱ ጋር በሕይወት እንደምንኖር
እናምናለን ፤ 9 ክርስቶስ ከሞት በመነሣቱ ምክን
ያት ዳግመኛ እንደማይሞትና ሞትም በእርሱ
ላይ ሥልጣን እንደሌለው እናውቃለን ።
10 እርሱ በሞተ ጊዜ ፥ ኃጢአት በእርሱ ላይ
ሥልጣን እንዳይኖረው በማያዳግም ሁኔታ
አንድ ጊዜ ሞቶአል ፤ አሁንም በሕይወት ሲኖር
ለእግዚአብሔር ይኖራል ። 11 እንግዲህ በእናን
ተም ላይ ኃጢአት ሥልጣን እንደሌለውና በኢ
የሱስ ክርስቶስ አማካይነት ለእግዚአብሔር በሕ
ይወት እንደምትኖሩ አስቡ ።
12 ስለዚህ ፥ ኃጢአት በሚሞተው ሰውነታ
ችሁ ላይ ሥልጣን እንዲኖረውና ለሥጋ ምኞ
ትም ተገዥ እንዲያደርጋችሁ አትፍቀዱለት ።
13 እንዲሁም የሰውነታችሁን ክፍሎች የዐመፅ
መሣሪያ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታስገዙ ፤
ነገር ግን ከሞት እንደተነሣችሁ ራሳችሁን ለእግ
ዚአብሔር አቅርቡ ፤ የሰውነታችሁንም ክፍሎች
ሁሉ የጽድቅ መሣሪያ አድርጋችሁ ለእግዚአብ
ሔር አስገዙ ። 14 ምክንያቱም አሁን እናንተ
የምትኖሩት ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ስላ
ልሆነ ኃጢአት ሊገዛችሁ አይችልም ።

### የጽድቅ አገልጋዮች መሆን

15 እንግዲህ ምን እንላለን? ከሕግ በታች
መሆናችን ቀርቶ ከጸጋ በታች ስለሆንን ኃጢ
አት እንሥራ ማለት ነውን? ከቶ አይሆንም!





16 ለአንድ ሰው አገልጋዮች ሆናችሁ ለመታዘዝ
ራሳችሁን ስታቀርቡ ፥ ለዚያ ለምትታዘዙለት
ሰው አገልጋዮች መሆናችሁን ታውቃላችሁ ፤
እንዲሁም ለኃጢአት ብትታዘዙ ፥ ሞትን ለሚ
ያመጣባችሁ ኃጢአት አገልጋዮች ትሆናላ
ችሁ ፤ ለእግዚአብሔር ብትታዘዙ ግን ጽድቅን
ታገኛላችሁ ። 17 እናንተ አስቀድሞ የኃጢአት
ባሪያዎች ነበራችሁ ፤ አሁን ግን ለተቀበላችሁት
ትምህርት ከልብ በመታዘዛችሁ ለእግዚአብሔር
ምስጋና ይሁን ። 18 ከኃጢአት ባርነት ነፃ ወጥ
ታችሁ የጽድቅ አገልጋዮች ሆናችኋል ። 19 እኔ
እንዲህ ለሰው በሚገባ ቋንቋ የምናገረው ከአስተ
ሳሰባችሁ ደካማነት የተነሣ ነው ። አስቀድሞ
የሰውነት ክፍሎቻችሁን የርኵሰትና የዐመፅ አገ
ልጋዮች አድርጋችሁ እንዳቀረባችሁ ሁሉ ፥ እን
ዲሁም አሁን የሰውነት ክፍሎቻችሁ እንዲቀ
ደሱ የጽድቅ አገልጋዮች አድርጋችሁ አቅርቡ ።
20 የኃጢአት ባሪያዎች በነበራችሁበት ጊዜ
ጽድቅ የማድረግ ግዴታ አይሰማችሁም ነበር ።
21 ታዲያ በዚያን ጊዜ ምን ጥቅም አገኛችሁ?
አሁን ከሚያሳፍራችሁ ነገር በቀር ምንም
ጥቅም አላገኛችሁም ፤ የዚህም ነገር መጨረሻ
ሞት ነው ። 22 አሁን ግን ከኃጢአት ባርነት ነፃ
ወጥታችሁ የእግዚአብሔር አገልጋዮች በመሆና
ችሁ ቅድስናን ታገኛላችሁ ፤ የቅድስናም መጨ
ረሻ የዘላለም ሕይወት ነው ። 23 ምክንያቱም
ከኃጢአት የሚገኘው ዋጋ ሞት ነው ፤ ከእግዚ
አብሔር የሚሰጠው ስጦታ ግን በጌታችን በኢየ
ሱስ ክርስቶስ አማካይነት የሚገኘው የዘላለም
ሕይወት ነው ።

## ምዕራፍ 7

### ከሙሴ ሕግ ነፃ ስለመሆን

1 ወንድሞቼ ሆይ! ሁላችሁም ሕግን ስለም
ታውቁ ፤ ሕግ በሰው ላይ ሥልጣን የሚኖረው
ሰው በሕይወት እስካለ ድረስ ብቻ መሆኑን
ታውቃላችሁ ። 2 ለምሳሌ ፥ ያገባች ሴት ባልዋ
በሕይወት እስካለ ድረስ ከእርሱ ጋር በሕግ የታ
ሰረች ናት ፤ ባልዋ ከሞተ ግን ከታሰረችበት
ሕግ ነፃ ናት ። 3 ስለዚህ ባልዋ በሕይወት እያለ
ሌላ ወንድ ብታገባ አመንዝራ ትባላለች ። ባልዋ
ከሞተ ግን ከርሱ ጋር ከታሰረችበት ሕግ ነፃ
ትወጣለች ፤ ሌላ ወንድ ብታገባም አመንዝራ
አይደለችም ። 4 ወንድሞቼ ሆይ! የእናንተም
ሁኔታ እንደዚሁ ነው ፤ እናንተ የክርስቶስ
አካል ክፍል ስለሆናችሁ በሞት የመለየትን
ያህል ከሙሴ ሕግ ተለይታችኋል ። ስለዚህ ለእ
ግዚአብሔር አገልግሎት ፍሬ እንድናፈራ
ከሞት የተነሣው የክርስቶስ ወገኖች
ሆናችኋል ። 5 ምክንያቱም በሥጋ ፈቃድ እንመ
ላለስ በነበረበት ጊዜ በሕግ የሚቀሰቀሰው ክፉ
ምኞት ለሞት ፍሬ እንድናፈራ በሰውነታችን
ክፍሎች ይሠራ ነበር ። 6 አሁን ግን አስሮን ከነ
በረው ሕግ በሞት የመለየት ያህል ስለ ተለየን ፥
ከሕግ እስራት ነፃ ወጥተናል ። ስለዚህ ከእንግ
ዲህ ወዲህ የምናገለግለው በአዲሱ መንፈሳዊ
መመሪያ እንጂ አስቀድሞ በተጻፈው በአሮጌው
የሕግ መመሪያ አይደለም ።

### ሕግና ኃጢአት

7 እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ራሱ ኃጢ
አት ነውን? አይደለም! ነገር ግን ኃጢአት ምን
መሆኑን እንዳውቅ ያደረገኝ ሕግ ነው ። ምክን
ያቱም ሕግ “አትመኝ” ባይል ኖሮ ምኞት
ምን መሆኑን ባላወቅሁም ነበር ። 8 ኃጢአት
ምኞትን ሁሉ በኔ ውስጥ እንዲቀሰቀስ ያደረ
ገው ከሕግ በመጣው ትእዛዝ አጋጣሚ በማግ
ኘት ነው ። ሕግ ከሌለ ግን ኃጢአት የሞተ
ነገር ነው ። 9 ሕግ በእኔ ሕይወት ላይ ገና ሥል
ጣን ያላገኘበት ጊዜ ነበር ፤ የሕግን ትእዛዝ ባወ
ቅሁ ጊዜ ግን ኃጢአት ሕይወት አገኘ ፤
10 እኔም ሞትሁ ፤ ለሕይወት የተሰጠውም
የሕግ ትእዛዝ በእኔ ላይ ሞትን አመጣብኝ ።
11 ምክንያቱም ኃጢአት የሕግን ትእዛዝ ሰበብ
አድርጎ አታለለኝ ፤ በትእዛዝም አማካይነት ገደ
ለኝ ።
12 ስለዚህ ሕግ ቅዱስ ነው ፤ ትእዛዝም ቅዱ
ስና እውነት መልካምም ነው ። 13 ታዲያ ይህ
መልካም የሆነው ነገር በእኔ ሞትን አመጣብኝ
ማለት ነውን? አይደለም! ሞትን ያመጣብኝስ
ኃጢአት ነው ። ኃጢአት ምንነቱ እንዲገለጥ ፥
መልካም በሆነው ነገር አመካኝቶ ፥ በእኔ ላይ
ሞትን አመጣብኝ ። ስለዚህ የኃጢአት ክፋት
የሚገለጠው በሕግ ትእዛዝ አማካይነት ነው ።

### በሰው ሕይወት ውስጥ ያለ ትግል

14 እንግዲህ ሕግ መንፈሳዊ መሆኑን እናው
ቃለን ። እኔ ግን የኃጢአት ባሪያ ለመሆን የተሸ
ጥሁ ሥጋዊ ነኝ ። 15 እኔ የማደርገውን አላው
ቅም ፤ ምክንያቱም የምወደውን ነገር ማድረግ
ትቼ ፥ የምጠላውን ነገር አደርጋለሁ ። 16 እንግ
ዲህ እኔ የማደርገው የማልፈልገውን ነገር ከሆነ
ሕግ መልካም መሆኑን እገልጣለሁ ። 17 እንግ
ዲህ ማድረግ የማልፈልገውን ነገር የሚያደር
ገው ፥ በእኔ ውስጥ ያለው ኃጢአት ነው እንጂ
እኔ አይደለሁም ። 18 በእኔ ወይም በእኔ ሥጋዊ
ባሕርይ ምንም መልካም ነገር እንደሌለ ዐውቃ
ለሁ ፤ ምክንያቱም ምንም እንኳ መልካም ነገር
የማድረግ ፍላጎት ቢኖረኝም ያንን መልካም
ነገር የማድረግ ችሎታ የለኝም ። 19 ማድረግ
የምፈልገውን መልካም ነገር አላደርግም ፤ ዳሩ
ግን የማልፈልገውን ክፉ ነገር አደርጋለሁ ።

[20]እንግዲህ ማድረግ የማልፈልገውን ክፉ ነገር
የማደርግ ከሆንሁ፥ ይህን የሚያደርገው፥ በእኔ
ውስጥ ያለው ኃጢአት ነው እንጂ እኔ አይደለ
ሁም ማለት ነው።
[21]እንግዲህ መሠረታዊ ሐሳብ በሥራ ላይ
መሆኑን አያለሁ፤ ምክንያቱም መልካም ነገርን
ማድረግ ስፈልግ፥ ክፉ ነገርን ለማድረግ እገደዳ
ለሁ። [22]ውስጣዊ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ
ደስ ይለዋል። [23]ይሁን እንጂ ከአእምሮዬ ሕግ
ጋር እየተቃረነ በሰውነቴ ክፍሎች ውስጥ ለሚ
ሠራው የኃጢአት ሕግ እስረኛ የሚያደርገኝ
ሌላ ሕግ በሰውነቴ ክፍሎች ውስጥ መኖሩን
አያለሁ። [24]እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ! ወደ
ሞት ከሚወስደኝ ከዚህ ሰውነትስ ማን ያድነ
ኛል? [25]በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአ
ብሔር ምስጋና ይሁን።
እንግዲህ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር
ሕግ ተገዥ ስሆን፥ በሥጋ ባሕርዩ ለኃጢአት
ሕግ ተገዥ ሆኛለሁ።

## ምዕራፍ 8

### ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ

[1]እንግዲህ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ኅብረት
ያላቸው አሁን ኵነኔ የለባቸውም። [2]ምክንያ
ቱም በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትን የሚሰጥ
የመንፈስ ቅዱስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ
ነፃ አውጥቶኛል። [3]ከሰው ባሕርይ ደካማነት
የተነሣ ሕግ ሊያደርገው ያልቻለውን እግዚአብ
ሔር አድርጎታል፤ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን
በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ ላከ፤ ለኃጢአት መሥ
ዋዕት ባደረገውም በዚሁ በልጁ ሥጋ የሰውን
ኃጢአት በፍርድ አስወግዶአል። [4]ይህንንም
ያደረገው በሥጋ ፈቃድ ሳይሆን በመንፈስ
ፈቃድ በምንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ እንዲ
ፈጸም ነው። [5]በሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ ሥጋዊ
ነገርን፥ በመንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን መንፈ
ሳዊ ነገርን ያስባሉ። [6]ሥጋዊ ነገርን ማሰብ
ሞትን ያመጣል፤ መንፈሳዊ ነገርን ማሰብ ግን
ሕይወትንና ሰላምን ይሰጣል። [7]ምክንያቱም
ሥጋዊ ነገርን የሚያስብ ሰው ለእግዚአብሔር
ሕግ ስለማይታዘዝና መታዘዝም ስለማይችል የእ
ግዚአብሔር ጠላት ይሆናል። [8]ለሥጋዊ ነገር
የሚገዙ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይች
ሉም።
[9]እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በውስ
ጣችሁ ካለ፥ በመንፈስ ፈቃድ እንጂ በሥጋ
ፈቃድ አትኖሩም፤ የክርስቶስ መንፈስ የሌለ
ውም ሰው የክርስቶስ ወገን አይደለም። [10]ክርስ
ቶስ በእናንተ ውስጥ ከሆነ፥ ምንም እንኳ ሥጋ
ችሁ በኃጢአት ምክንያት የሚሞት ቢሆንም
እግዚአብሔር ስላጸደቃችሁ መንፈሳችሁ
ሕያው ነው፤ [11]ኢየሱስን ከሞት ያስነሣው የእ
ግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ ቢኖር፥ ኢየ
ሱስ ክርስቶስን ከሞት ያስነሣው አምላክ በውስ
ጣችሁ በሚኖረው መንፈሱ አማካይነት፥
ለሟች ሥጋችሁ ሕይወትን ይሰጠዋል።
[12]ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ! በሕይወታችን
ግዴታ አለብን፤ ነገር ግን ይህ ግዴታ በሥጋ
ፈቃድ ለመኖር አይደለም። [13]በሥጋ ፈቃድ
ብትኖሩ ትሞታላችሁ፤ ነገር ግን በመንፈስ ዕር
ዳታ፥ ሥጋዊ ሥራችሁን ብትገድሉ በሕይወት
ትኖራላችሁ። [14]በእግዚአብሔር መንፈስ የሚ
መሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።
[15]ስለዚህ "አባባ" ብላችሁ የምትጠሩበትን የል
ጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ በፍርሃት ለመ
ኖር የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁም።
[16]የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኛ መንፈስ ጋር
ሆኖ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ይመሰ
ክራል። [17]እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆ
ንን፥ የእርሱ ወራሾች ነን፤ ከክርስቶስም ጋር
እንወርሳለን፤ አሁን የክርስቶስ መከራ ተካፋ
ዮች ብንሆን በኋላ የክብሩ ተካፋዮች እንሆና
ለን።

### የሚመጣው ክብር

[18]የአሁኑ ጊዜ መከራ ወደፊት ለእኛ ከሚገ
ለጥልን ክብር ጋር ቢመዛዘን በምንም ሊተካከል
እንደማይችል አድርጌ እቈጥረዋለሁ። [19]ፍጥ
ረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ በታ
ላቅ ናፍቆት ይጠባበቃል። [20]ፍጥረት ሁሉ
ዋጋቢስ እንዲሆን ተፈርዶበታል፤ ይኸውም
በራሱ ፈቃድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ
ነው፤ ይሁን እንጂ ይህ ተስፋ አለ፦ [21]ተስፋ
ውም ፍጥረት ራሱ ከጥፋት ባርነት ነፃ ወጥቶ
ከእግዚአብሔር ልጆች ጋር የነፃነትና የክብር
ተካፋይ እንደሚሆን ነው። [22]ፍጥረት ሁሉ
እስከ ዛሬ ድረስ በምጥ ጭንቀት ተይዞ በመቃ
ተት ላይ መኖሩን እናውቃለን። [23]ነገር ግን
በመቃተት ላይ ያለው ፍጥረት ብቻ አይደለም፤
የመጀመሪያውን ስጦታ መንፈስ ቅዱስን የተቀበ
ልን እኛም፥ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆ
ንና ሁለንተናችን ነፃ እንዲሆን በተስፋ እየተጠ
ባበቅን በውስጣዊ ሰውነታችን በመቃተት ላይ
እንገኛለን፤ [24]ምክንያቱም እኛ የዳንነው
በዚሁ ተስፋ ነው። ነገር ግን ተስፋ የምናደር
ገው ነገር የሚታይ ከሆነ ተስፋ መሆኑ ይቀ
ራል፤ የሚታየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል?
[25]የማናየውን ነገር ተስፋ ካደረግን ግን በትዕግ
ሥት እንጠባበቃለን።

8፡11 ፦ 1ቆሮ. 3፡16። 8፡15 ፦ ማር. 14፡36፤ ገላ. 4፡6። 8፡15-17 ፦ ገላ. 4፡5-7። 8፡20 ፦ ዘፍ. 3፡17-19።
8፡23 ፦ 2ቆሮ. 5፡2-4።



[26]እንዲሁም እንዴት መጸለይ እንደሚገባን
ስለማናውቅ መንፈስ ቅዱስ በድካማችን ጊዜ
ይረዳናል፤ በቃል ሊገለጥ በማይቻል መቃተት
ስለ እኛ ይጸልያል። [27]የሰውን ልብ የሚመረ
ምር አምላክ የመንፈስ ቅዱስ አሳብ ምን እንደ
ሆነ ያውቃል፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ስለ
ቅዱሳን የሚጸልየው እንደ እግዚአብሔር
ፈቃድ ነው።
[28]እግዚአብሔርን ለሚወዱና እንደፈቃዱም
ለተጠሩት ሰዎች፥ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር
ለጥቅማቸው እንደሚያደርግላቸው እናውቃ
ለን። [29]ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጅ
በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር እንዲሆን፤
እግዚአብሔር አስቀድሞ የመረጣቸውን የልጁን
መልክ እንዲመስሉ ስለ ወሰነ ነው። [30]አስቀ
ድሞ የወሰናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውንም
አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም አከበራቸው።

### የእግዚአብሔር ፍቅር

[31]እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግ
ዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ሊቃወመን
ይችላል? [32]እግዚአብሔር ለአንድ ልጁ ሳይ
ራራ ስለእኛ አሳልፎ ከሰጠው፥ ከልጁ ጋር
ሁሉን ነገር እንደሚሰጠን እርግጠኞች ነን።
[33]እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማንም ሊከሳ
ቸው አይችልም፤ ምክንያቱም ያጸደቃቸው
እርሱ ነው። [34]ሊፈርድባቸውስ የሚችል ማን
ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈርድባቸዋልን? እር
ሱስ አይፈርድባቸውም፤ ምክንያቱም እርሱ ስለ
እኛ የሞተ፥ ከሞት ተነሥቶ በእግዚአብሔር
አብ ቀኝ የተቀመጠ፥ ስለ እኛም የሚማልድ
ነው። [35]ስለዚህ ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን የሚ
ችል ማንም የለም፤ ችግር ወይም መከራ፥
ስደት ወይም ራብ፥ ራቁትነት ወይም አደጋ፥
ወይም ሰይፍ፥ ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን አይች
ልም። [36]ይህም፦
"ስለ አንተ ፍቅር በየቀኑ እንገደላለን፤
እንደሚታረዱ በጎችም ተቈጠርን"
ተብሎ እንደ ተጻፈው ነው። [37]እንግዲህ በወደ
ደን በክርስቶስ፥ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ድል
በመንሣት ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። [38]ስለ
ዚህ ሞትም ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእ
ክትም ቢሆኑ፥ ባለሥልጣኖችም ቢሆኑ፥ አሁን
ያለውም ቢሆን፤ በኋላ የሚመጣውም ቢሆን፥
የሰማይ ኀይሎችም ቢሆኑ፥ [39]ከፍታም
ቢሆን፤ ዝቅታም ቢሆን፥ ማንኛውም ፍጥረት
ቢሆን፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከተገለጠ
ልን ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን የሚችል
ምንም ነገር እንደሌለ እርግጠኛ ነኝ።

## ምዕራፍ 9

### እግዚአብሔር መርጦት የነበረው የእስራኤል ሕዝብ

[1]የክርስቶስ እንደመሆኔ መጠን እውነት እና
ገራለሁ እንጂ አልዋሽም፤ በመንፈስ ቅዱስ
የሚመራው ኅሊናዬም እንደማልዋሽ ይመሰክር
ልኛል። [2]ትልቅ ሐዘንና የማያቋርጥ ጭንቀት
በልቤ አለ፤ [3]በሥጋ ዘመዶቼ ስለሆኑት ወገኖቼ
ከክርስቶስ ተለይቼ የእግዚአብሔር እርግማን
ቢደርስብኝ በወደድሁ ነበር። [4]እስራኤላውያን
የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ ናቸው፤ እግዚአ
ብሔር እነርሱን ልጆቹ አደረጋቸው፤ ክብሩን
ገለጠላቸው፤ ቃል ኪዳን ገባላቸው፤ ሕግን
ሰጣቸው፤ እውነተኛውን አምልኮ አሳያቸው፤
የተስፋውንም ቃል ሰጣቸው። [5]እነርሱ በትው
ልዳቸው ከነገድ አባቶች የመጡ ናቸው፤ ክርስ
ቶስም በሥጋ የመጣው ከእነርሱ ነው፤ እርሱ
ከሁሉ በላይ የሆነና የተባረከ አምላክ ነው፤
አሜን።
[6]ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል ተሸሮ
አል ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም የእስራኤል
ዘር በሙሉ እውነተኞች እስራኤላውያን አይደ
ሉም። [7]እንዲሁም የአብርሃም ዘር ሁሉ የእግ
ዚአብሔር ልጆች ናቸው ማለት አይደለም፤
ምክንያቱም እግዚአብሔር አብርሃምን "ዘር
የሚወጣልህ በይስሐቅ ነው" ብሎት ስለነበር
ነው። [8]ስለዚህ በሥጋ የተወለዱት የእግዚአብ
ሔር ልጆች አይደሉም፤ ነገር ግን ዘር ሆነው
የሚቈጠሩት የተስፋው ቃል ልጆች ብቻ
ናቸው። [9]ይህም እግዚአብሔር የሰጠው የተ
ስፋ ቃል "የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ እመጣለሁ፤
ሣራም ወንድ ልጅ ትወልዳለች" የሚል ነው።
[10]ይህም ብቻ ሳይሆን ርብቃ የነገድ አባታ
ችን ከሆነው ከይስሐቅ መንታ ልጆችን በፀነሰች
ጊዜ፥ [11]የእግዚአብሔር ምርጫ በሥራ ሳይሆን
በጥሪ መሆኑን ለመግለጥ፥ ሁለቱ ልጆች ከመወ
ለዳቸውና ክፉና ደግ ከማድረጋቸው በፊት፥
[12]እግዚአብሔር ርብቃን "ታላቁ ለታናሹ
ተገዥ ይሆናል" አላት። [13]ይህም "ያዕቆብን
ወደድሁ፥ ዔሳውን ግን ጠላሁ" ተብሎ እንደተ
ጻፈው ነው።
[14]እንግዲህ ምን እንላለን? "እግዚአብሔር
ያዳላል" ማለት እንችላለንን? "እግዚአብሔር
ያዳላል" ማለትስ ከቶ አንችልም! [15]ምክንያ
ቱም እግዚአብሔር ሙሴን "ልምረው የምፈል
ገውን እምረዋለሁ፥ ልራራለት የምፈልገውንም
እራራለታለሁ" ብሎታል። [16]ስለዚህ የእግዚአ
ብሔር ምርጫ የሚገኘው በሰው ፈቃድና
በሰው ሥራ ሳይሆን በእግዚአብሔር ምሕረት

8፡36 ፦ መዝ. 44፡22። 9፡4 ፦ ዘጸ. 9፡4። 9፡7 ፦ ዘፍ. 21፡12። 9፡9 ፦ ዘፍ. 18፡10። 9፡12 ፦ ዘፍ. 25፡23።
9፡13 ፦ ሚል. 1፡2-3። 9፡15 ፦ ዘጸ. 33፡19።

ነው ። [17] በዚህ ምክንያት ስለ ፈርዖን “በአንተ
ኃይሌን ለማሳየትና ስሜም በዓለም ሁሉ ላይ
እንዲታወቅ ለማድረግ አነግሼሃለሁ” የሚል
ቃል ተጽፎአል ። [18] ስለዚህ እግዚአብሔር የሚ
ፈልገውን ይምረዋል ፤ የሚፈልገውንም እልኸኛ
ያደርገዋል ።

### የእግዚአብሔር ቍጣና ምሕረት

[19] እንግዲህ “የእግዚአብሔርን ፈቃድ መቃ
ወም የማይቻል ከሆነ ፥ ታዲያ እግዚአብሔር
ሰዎችን ለምን በክፉ ሥራቸው ይወቅሳቸ
ዋል?” የሚል ይኖር ይሆናል ። [20] አንተ ሰው!
ከእግዚአብሔር ጋር ለመከራከር ምን መብት
አለህ? የሸክላ ዕቃ ሠሪውን “ለምን እንዲህ
አድርገህ ሠራኸኝ?” ሊለው ይችላልን?
[21] ሸክላ ሠሪ ፥ ከአንድ ዐይነት የሸክላ ጭቃ
አንዱን ዕቃ ለክብር ፥ ሌላውንም ዕቃ ለውር
ደት አድርጎ ለመሥራት መብት የለውምን?
[22] እግዚአብሔር ቍጣውን ለማሳየትና ኀይ
ሉንም ለመግለጥ ፈልጎ ፥ ለጥፋት የተዘጋጁትን
የቍጣ ዕቃዎች ብዙ ታገሣቸው ። [23] ይህንንም
ያደረገው አስቀድሞ ለክብር ላዘጋጃቸው ለምሕ
ረት ዕቃዎች የክብሩን ብዛት ለመግለጥ ነው ።
[24] የምሕረት ዕቃዎቹም ከአይሁዳውያን ብቻ
ሳይሆን ከአረማውያንም የተጠራን እኛ ነን ።
[25] ይህም በነቢዩ በሆሴዕ እንዲህ እንደተባለ
ነው ፥

“የእኔ ሕዝብ ያልነበረውን ‘ሕዝቤ!’
ብዬ እጠራዋለሁ ፤
ያልተወደደውንም ሕዝብ ‘የተወደደ’
ብዬ እጠራዋለሁ ፤
[26] እነርሱ ‘ሕዝቤ አይደላችሁም’
በተባሉበት ስፍራ
የሕያው እግዚአብሔር ልጆች
ተብለው ይጠራሉ ።”

[27] ኢሳይያስም ስለ እስራኤል እንዲህ ሲል
ድምፁን ከፍ አድርጎ ይናገራል ፥ “የእስራኤል
ልጆች ቍጥር እንደ ባሕር አሸዋ ቢበዛ ፥ ከእነ
ርሱ የሚድኑት ጥቂቶች ብቻ ናቸው ። [28] ምክን
ያቱም እግዚአብሔር ሳይዘገይ በፍጥነት በዓለም
ላይ ፍርዱን ይሰጣል ።” [29] እንዲሁም ኢሳይያስ
“ኃያሉ እግዚአብሔር ዘር ባያስቀርልን ኖሮ ፥
የሰዶምና የገሞራ ከተሞች እንደጠፉ እኛም
በጠፋን ነበር” ሲል አስቀድሞ ተናግሮአል ።
[30] እንግዲህ ምን እንላለን? ጽድቅን ያልተከ
ተሉት አረማውያን ጽድቅን አገኙ ፤ ይህም
ጽድቅ ከእምነት የሚገኘው ነው ። [31] ነገር ግን
ከሕግ የሚገኘውን ጽድቅ ይከተሉ የነበሩት እስ
ራኤላውያን ሕግን ለመፈጸም ባለመቻላቸው
ወደ ጽድቅ አልደረሱም ። [32] “ስለምን ወደ
ጽድቅ አልደረሱም” ቢባል ፥ እነርሱ ጽድቅን
ለማግኘት የፈለጉት በእምነት ሳይሆን በሥራ
ስለሆነ ነው ፤ ስለዚህ በማሰናከያ ድንጋይ ተሰና
ከሉ ፤ [33] ይህም ፥

“እነሆ ሰዎችን የሚያሰናክል ድንጋይ
በጽዮን አኖራለሁ ፤
ይህም ድንጋይ ሰዎችን በማሰናከል
የሚጥል አለት ነው ፤
በእርሱ የሚያምን ግን አያፍርም”

ተብሎ እንደተጻፈው ነው ።

## ምዕራፍ 10

### እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን መንገድ አልተከተሉም

[1] ወንድሞቼ ሆይ! በልቤ ያለው ታላቅ ምኞ
ትና ለእግዚአብሔር የማቀርበው ጸሎት እስራኤ
ላውያን እንዲድኑ ነው ። [2] በትክክለኛ ዕውቀት
ላይ የተመሠረተ ባይሆንም እነርሱ ለእግዚአብሔር
መንፈሳዊ ቅንአት እንዳላቸው እኔ ራሴ እመሰክ
ርላቸዋለሁ ። [3] እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያጸድ
ቅበትን መንገድ ባለማወቃቸው የራሳቸውን የጽ
ድቅ መንገድ ተከተሉ እንጂ የእግዚአብሔርን
ጽድቅ አልተከተሉም ። [4] ሰው ሁሉ በእምነት
እንዲጸድቅ ፥ የሙሴ ሕግ በክርስቶስ አክትሞ
አል ።

### ደኅንነት ለሁሉም ነው

[5] ሕግን በመከተል ስለሚገኘው ጽድቅ ፥
ሙሴ የጻፈው “ሕግን የሚፈጽም ሁሉ በሕይ
ወት ይኖራል” የሚል ነው ። [6] እግዚአብሔር
ሰዎችን በእምነት ስለማጽደቁ ግን እንዲህ
ተብሎ ተጽፎአል ፥ “በልብህ ወደ ሰማይ ማን
ይወጣል?” አትበል ፥ ይህም ክርስቶስን ለማው
ረድ ነው ፤ [7] ወይም በልብህ “ወደ ሲኦል ማን
ይወርዳል?” አትበል ፥ ይህም ክርስቶስን ከሞት
ለማስነሣት ነው ።
[8] ደግሞም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል ፥ “የእ
ግዚአብሔር ቃል አጠገብህ ነው ፤ እንዲያውም
በአፍህና በልብህ ነው ፤” ይህም ቃል እኛ የም
ናበሥረው የእምነት ቃል ነው ።
[9] ኢየሱስ ጌታ መሆኑን በአፍህ ብትመሰክ
ርና እግዚአብሔር ከሞት እንዳስነሣውም በል
ብህ ብታምን ትድናለህ ። [10] ምክንያቱም ሰው
በልቡ ሲያምን ይጸድቃል ፤ በአፉም ሲመሰክር
ይድናል ፤ [11] ይህም “በእርሱ የሚያምን ሁሉ
አያፍርም” ተብሎ እንደ ተጻፈው ነው ።
[12] እንግዲህ አንዱ እግዚአብሔር የሁሉም ጌታ
ስለሆነ ፥ በአይሁዳዊና በአረማዊ መካከል

9፥17 ፦ ዘጸ. 9፥16 ። 9፥20 ፦ ኢሳ. 29፥16 ፤ 45፥9 ። 9፥25 ፦ ሆሴዕ 2፥23 ። 9፥26 ፦ ሆሴዕ 1፥10 ።
9፥27-28 ፦ ኢሳ. 10፥22-23 ። 9፥29 ፦ ኢሳ. 1፥9 ። 9፥33 ፦ ኢሳ. 28፥16 ። 10፥5 ፦ ዘሌ. 18፥5 ።
10፥6-8 ፦ ዘዳ. 30፥12-14 ። 10፥11 ፦ ኢሳ. 28፥16 ።



ምንም ልዩነት የለም ፤ እርሱም ባለጸጋ ስለ
ሆነ ፥ ለሚለምኑት ሁሉ በረከቱን አብዝቶ ይሰ
ጣል ፤ [13] ምክንያቱም “የጌታን ስም የሚጠራ
ሁሉ ይድናል” ተብሎአል ።
[14] ነገር ግን ሳያምኑበት እንዴት ሊጠሩት
ይችላሉ? ስለ እርሱ ሳይሰሙስ እንዴት ያም
ናሉ? የምሥራቹን ቃል የሚያበሥርላቸው ሳይ
ኖርስ እንዴት ሊሰሙ ይችላሉ? [15] የምሥራቹን
ቃል የሚያበሥሩ ካልተላኩስ እንዴት ሊያበ
ሥሩ ይችላሉ? ይህም “የመልካም ዜና አብሣሪ
ዎች መምጣት እንዴት ደስ ያሰኛል!” ተብሎ
እንደተጻፈው ነው ። [16] ነገር ግን ኢሳይያስ
“ጌታ ሆይ! የተናገርነውን ቃል ማንም አልተ
ቀበለም” ብሎ እንደተናገረ ሁሉም የምሥራ
ቹን ቃል አልተቀበሉም ። [17] ስለዚህ እምነት
የሚገኘው የምሥራቹን ቃል ከመስማት ነው ፤
የምሥራቹም ቃል ስለ ክርስቶስ የሚነገረው
ትምህርት ነው ። [18] እስቲ ልጠይቅ ፥ ታዲያ
ቃሉን አልሰሙም ማለት ነውን? በመጽሐፍ ፥

“ድምፃቸው በዓለም ሁሉ ተሰማ ፤
ቃላቸውም እስከ ምድር ዳርቻ ደረሰ”

ተብሎ እንደተጻፈው በእርግጥ ሰምተዋል ።
[19] ደግሞስ ፥ እስራኤላውያን ቃሉን አላወቁም
ማለት ነውን? ይህማ እንዳይባል ሙሴ አስቀ
ድሞ ፥

“በተናቀ ሕዝብ አስቀናችሁ
አስቈጫችኋለሁ ፤
በማያስተውል ሕዝብም
አስቈጣችኋለሁ” ብሎአል ።
[20] ኢሳይያስም ፥
“ላልፈለጉኝ ተገኘሁ ፥
‘እግዚአብሔር የት ነው?’ ብለው
ላልጠየቁኝም ተገለጥሁ”

በማለት ደፍሮ ተናግሮአል ። [21] ስለ እስራኤላው
ያን ግን “የማይታዘዝና ዐመፀኛ ሕዝብ ወደ እኔ
እንዲመጣ ቀኑን ሙሉ እጆቼን ዘረጋሁ” ይላል ።

## ምዕራፍ 11

### እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ጨርሶ አልጣለም

[1] እስቲ ደግሞ ልጠይቅ ፥ እግዚአብሔር የራ
ሱን ሕዝብ ጥሎአልን? ከቶ አልጣለውም!
እኔም ራሴ እኮ እስራኤላዊ ነኝ ፤ ከአብርሃም
ዘር የሆንሁ የብንያም ነገድ ነኝ ። [2] ስለዚህ እግ
ዚአብሔር አስቀድሞ የመረጠውን ሕዝብ አል
ጣለውም ፤ መጽሐፍ ስለ ኤልያስ ምን እንዳለ
አታስታውሱምን? ደግሞስ ኤልያስ የእስራኤ
ልን ሕዝብ በእግዚአብሔር ፊት ምን ብሎ እን
ደከሰሰ አታውቁምን? [3] በዚያን ጊዜ ኤልያስ
“ጌታ ሆይ! ነቢያትህን ገደሉ ፥ መሠዊያዎች
ህን አፈረሱ ፤ እኔ ብቻ ቀረሁ ፥ እኔንም ሊገድ
ሉኝ ይፈልጋሉ” ብሎ ነበር ። [4] ነገር ግን እግዚ
አብሔር ምን ብሎ መለሰለት? “ለሐሰተኛው
አምላክ ለባዓል ያልሰገዱትን ሰባት ሺ ሰዎች
ለራሴ አስቀርቻለሁ” ብሎታል ። [5] በአሁኑም
ዘመን ቢሆን በጸጋ ተመርጠው የቀሩ ጥቂት እስ
ራኤላውያን አሉ ። [6] ምርጫው በጸጋ ከሆነ
በሥራ አይደለም ማለት ነው ፤ በሥራ ከሆነማ
ጸጋ ዋጋቢስ በሆነ ነበር ።
[7] ታዲያ ውጤቱ ምን ሆነ? እስራኤላውያን
የፈለጉትን አላገኙም ፤ የተመረጡት ግን የፈለጉ
ትን አገኙ ፤ የቀሩት እውነትን ማየት አቃታ
ቸው ። [8] ይህም “እግዚአብሔር ልቡናቸውን
አደነዘዘ ፤ ስለዚህ እስከ ዛሬ ድረስ በዐይናቸው
አያዩም ፥ በጆሮአቸውም አይሰሙም” ተብሎ
እንደተጻፈው ነው ። [9] ዳዊትም ፦

“ማእዳቸው የሚይዝ ወጥመድ ፥
የሚጥል ጕድጓድ ሆኖ ያሠቃያቸው ፤
[10] ዐይናቸው እንዳያይ ይጨልም ፤
ወገባቸው በችግር ሁልጊዜ ይጕበጥ”
ብሎአል ።

[11] እስቲ እንደገና ልጠይቅ ፥ አይሁዳውያን
የተሰናከሉት ለዘላለም እስኪጠፉ ነውን? አይደ
ለም! በአይሁዳውያን በደል ምክንያት አረማው
ያን ደኅንነትን አገኙ ፤ ይህም የሆነው ፥ እነርሱ
በአረማውያን እንዲቀኑ ለማድረግ ነው ። [12] የአ
ይሁዳውያን በደል ለዓለም ብዙ በረከት አስገኝ
ቶአል ፤ የእነርሱም ውድቀት ለአረማውያን በረ
ከት ሆኖአል ፤ አይሁዳውያን በሙሉ ቢድኑማ
ኖሮ በረከቱ ምን ያህል ብዙ በሆነ ነበር!

### የአረማውያን ደኅንነት

[13] አሁን እንግዲህ የምናገረው ለእናንተ ለአ
ረማውያን ነው ፤ የአረማውያንም ሐዋርያ እንደ
መሆኔ መጠን በአገልግሎቴ ክብር ይሰማኛል ፤
[14] ይህንንም ማድረጌ ወገኖቼ የሆኑትን አይሁዳ
ውያንን ለማስቀናት ነው ፤ በዚህም ሁኔታ ምና
ልባት ከእነርሱ አንዳንዶቹን አድን ይሆናል ።
[15] እግዚአብሔር እነርሱን በጣላቸው ጊዜ
ሌላው የዓለም ሕዝብ ከእግዚአብሔር ጋር ከታ
ረቀ ፥ እግዚአብሔር እነርሱን በሚቀበላቸው
ጊዜ ምን የሚሆን ይመስላችኋል? ይህማ ከሞት
እንደመነሣት ያህል ነው!
[16] ከአንድ ዐይነት ሊጥ የመጀመሪያው
ክፍል የተቀደሰ ከሆነ ፥ ሊጡ በሙሉ የተቀደሰ
ነው ፤ እንዲሁም አንድ ዛፍ ፥ ሥሩ የተቀደሰ

10፥13 ፦ ኢዩ. 2፥32 ። 10፥15 ፦ ኢሳ. 52፥7 ። 10፥16 ፦ ኢሳ. 53፥1 ። 10፥18 ፦ መዝ. 19፥4 ።
10፥19 ፦ ዘዳ. 32፥21 ። 10፥20 ፦ ኢሳ. 65፥1 ። 10፥21 ፦ ኢሳ. 65፥2 ። 11፥1 ፦ ፊል. 3፥5 ።
11፥3 ፦ 1ነገ. 19፥10 ፤ 14 ። 11፥4 ፦ 1ነገ. 19፥18 ። 11፥8 ፦ ዘዳ. 29፥4 ፤ ኢሳ. 29፥10 ።
11፥9-10 ፦ መዝ. 69፥22-23 ።

ከሆነ ቅርንጫፎቹም የተቀደሱ ናቸው ።
17 እንደ ጓሮ የወይራ ዛፍ ቅርንጫፍ የሆኑ አይ
ሁዳውያን ተቈርጠው ቢወድቁ ፥ እንደ ዱር
የወይራ ዛፍ ቅርንጫፎች የሆናችሁ አረማውያን
በቦታቸው ተተክታችሁ የእነርሱ ሀብትና በረ
ከት ተካፋዮች ሆናችሁ ። 18 ስለዚህ እናንተ
አረማውያን እንደ ቅርንጫፍ ተቈርጠው በወደ
ቁት አይሁዳውያን ላይ አትታበዩ ፤ ምክንያቱም
እናንተ ቅርንጫፎች ብቻ በመሆናችሁ ሥሩ
እናንተን ይሸከማችኋል እንጂ እናንተ ሥሩን
ስለማትሸከሙ መመካት አይገባችሁም ።
19 ነገር ግን “ቅርንጫፎች ተሰብረው የወደ
ቁት እኛ በቦታቸው እንድንተካ ነው” ትሉ
ይሆናል ። 20 አባባላችሁስ ልክ ነው ፤ ነገር ግን
እነርሱ ተቈርጠው የወደቁት በአለማመናቸው
ሲሆን ፥ እናንተ ጸንታችሁ የቆማችሁት በማመ
ናችሁ ነው ፤ ታዲያ እኮ መፍራት እንጂ መታ
በይ አይገባችሁም ። 21 ምክንያቱም እግዚአብ
ሔር በተፈጥሮ ቅርንጫፎች ለሆኑት አይሁዳው
ያን ካልራራላቸው ፥ ለእናንተም እኮ አይራራላ
ችሁም ። 22 እንግዲህ የእግዚአብሔርን ርኅራ
ኄና ጭካኔ ተመልከቱ ፤ ጭካኔውን የሚያሳየው
በወደቁት ላይ ሲሆን ፥ ርኅራኄውን የሚያሳየው
ግን ለእናንተ ነው ፤ ይህንንም የሚያደርገው
እርሱን በማመን ጸንታችሁ ብትኖሩ ነው ፤ ባት
ጸኑ ግን እናንተም ተቈርጣችሁ ትወድቃላ
ችሁ ። 23 አይሁዳውያንም አለማመናቸውን ቢያ
ስወግዱ ወደ ቀድሞው ቦታቸው ይመለሳሉ ፤
ምክንያቱም እግዚአብሔር ወደ ቀድሞው ቦታ
ቸው ሊመልሳቸው ይችላል ። 24 እናንተ አረማ
ውያን በተፈጥሮ የዱር የወይራ ዛፍ ቅርንጫ
ፎች ሆናችሁ ሳለ ያለ ቦታችሁ በጓሮ የወይራ
ዛፍ ላይ መተከል ከቻላችሁ ፥ የጓሮ የወይራ
ዛፍ ቅርንጫፎች የሆኑት አይሁዳውያንማ ወደ
ቀድሞው ቦታቸው ተመልሰው መተከል እን
ዴት አይቻላቸውም !

### የእግዚአብሔር ምሕረት ለሁሉም ነው

25 ወንድሞቼ ሆይ ! “ዐዋቂዎች ነን” ብላ
ችሁ እትመኩ ፤ የምነግራችሁ አንድ ምስጢር
አለ ፤ ይኸውም የእስራኤላውያን እምቢተኛነት
ለዘለቄታው ሳይሆን የተጠሩት አረማውያን ሁሉ
ወደ እግዚአብሔር እስኪመጡ ድረስ መሆኑን
ነው ። 26 እንግዲህ እስራኤላውያን ሁሉ የሚድ
ኑት በዚህ ዐይነት ሁኔታ ነው ። ስለዚህም እን
ዲህ ተብሎ ተጽፎአል ፥
“አዳኝ ከጽዮን ይመጣል ፤
ከያዕቆብም ዘር ሁሉ ኃጢአትን
ያስወግዳል ፤
27 ኃጢአታቸውንም በደመሰስሁላቸው ጊዜ
፥ ከእነርሱ ጋር የምገባው ቃል ኪዳን
ይህ ነው ።”
28 እስራኤላውያን የምሥራቹን ቃል ባለመቀ
በላቸው ስለ እናንተ ስለ አረማውያን ጥቅም የእ
ግዚአብሔር ጠላቶች ሆነዋል ፤ ነገር ግን በም
ርጫ በኩል በነገድ አባቶች ምክንያት የእግዚአ
ብሔር ወዳጆች ናቸው ። 29 ምክንያቱም እግዚ
አብሔር ከመረጠና ጸጋውን ከሰጠ በኋላ ባደረ
ገው ነገር አይጸጸትም ። 30 እናንተ አረማውያን
ቀድሞ ለእግዚአብሔር የማትታዘዙ ነበራችሁ ፤
አሁን ግን አይሁዳውያን ባለመታዘዛቸው ምክን
ያት እናንተ የእግዚአብሔርን ምሕረት አገኛ
ችሁ ። 31 እናንተ ምሕረትን ባገኛችሁበት ዐይ
ነት እነርሱም ምሕረትን እንዲያገኙ እነርሱ
አሁን ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ ሆነዋል ።
32 ምክንያቱም እግዚአብሔር ምሕረቱን ለሰው
ሁሉ ለማሳየት ሲል ሰዎችን ሁሉ የእምቢተኛነ
ታቸው እስረኞች እንዲሆኑ አደረጋቸው ።

### ለእግዚአብሔር የቀረበ ምስጋና

33 የእግዚአብሔር ባለጸግነትና ጥበብ ዕውቀ
ትም እንዴት ጥልቅ ነው ! ፍርዱ የማይመረ
መር ፥ መንገዱም የማይታወቅ ነው ።
34 “የእግዚአብሔርን አሳብ የሚያውቅ
ማንም የለም ፤
የእርሱ አማካሪ የሚሆንም የለም ።
35 ለእግዚአብሔር የሚያበድርና
ያበደረውንም የሚወስድ ማንም
የለም ፤”
36 ምክንያቱም ሁሉም ነገር የተገኘው ከእ
ርሱ ፥ በእርሱና ለእርሱ ነው ፤ ለዘላለም ክብር
ለእርሱ ይሁን ፤ አሜን ።

## ምዕራፍ 12

### እግዚአብሔርን ለማገልገል እንዴት መኖር እንደሚገባ

1 እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ ! ኹለንተናችሁን
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ፥ ሕያውና የተቀ
ደሰ መሥዋዕት አድርጋችሁ እንድታቀርቡ በእ
ግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ ፤ ይህም
ማቅረብ የሚገባችሁ ቅንነት ያለው እውነተኛ
አገልግሎት ነው ። 2 መልካሙንና ደስ የሚያሰ
ኘውን ፍጹም የሆነውንም የእግዚአብሔርን
ፈቃድ ማወቅ እንድትችሉ ፥ አእምሮአችሁ
ታድሶ ሕይወታችሁ ይለወጥ እንጂ የዚህን
ዓለም ሰዎች ክፉ ጠባይ አትከተሉ ።
3 ደግሞም “እያንዳንዳችሁ እግዚአብሔር
በሰጣችሁ እምነት መጠን በትሕትና አስቡ
እንጂ ከሚገባችሁ በላይ ስለ ራሳችሁ በትዕቢት





አታስቡ” ብዬ እግዚአብሔር በሰጠኝ ጸጋ እመ
ክራችኋለሁ ። 4 በአንዱ አካላችን ብዙ ክፍሎች
አሉ ፤ እያንዳንዱም የአካል ክፍል የተለየ ሥራ
አለው ። 5 እንዲሁም እኛ ብዙዎች ሆነን ሳለ
በክርስቶስ አንድ አካል ነን ፤ የአንድ አካል ክፍ
ሎች እንደመሆናችንም መጠን እርስ በርሳችን
ተገጣጥመናል ። 6 ስለዚህ እግዚአብሔር በጸ
ጋው የሰጠንን ልዩ ልዩ ስጦታ በሥራ ላይ እና
ውል ፤ ስጦታችን የእግዚአብሔርን ቃል መና
ገር ከሆነ ፥ በእምነታችን መጠን የእግዚአብሔ
ርን ቃል እንናገር ። 7 ስጦታችን ሌሎችን ማገል
ገል ከሆነ ፥ በትጋት እናገልግል ፤ ስጦታችን
ማስተማር ከሆነ ፥ በሚገባ እናስተምር ፤ 8 ስጦ
ታችን መምከር ከሆነ ፥ እንምከር ፤ ስጦታችን
መለገስ ከሆነ ፥ ከልብ እንለግስ ፤ ስጦታችን ማስ
ተዳደር ከሆነ ፥ በትጋት እናስተዳድር ፤ ስጦታ
ችን ምሕረት ማድረግ ከሆነ ፥ በደስታ ምሕረት
እናድርግ ።
9 ግብዝነት የሌለበት እውነተኛ ፍቅር ይኑራ
ችሁ ፤ ክፉውን ነገር ጥሉ ፤ መልካሙን ነገር
ተከተሉ ። 10 በክርስቶስ ወንድማማቾች እንደመ
ሆናችሁ መጠን እርስ በርሳችሁ ከልብ ተዋ
ደዱ ፤ እርስ በርሳችሁ ለመከባበርም ተሽቀዳ
ደሙ ፤ 11 ስንፍናን አስወግዳችሁ በትጋትና
በሙሉ ልብ ጌታ ኢየሱስን አገልግሉ ። 12 በተ
ስፋ ደስ ይበላችሁ ፤ በመከራ ጊዜ ታገሡ ፤
ሁልጊዜ ጸልዩ ። 13 አማኞች ወንድሞችን በችግ
ራቸው ዕርዱ ፤ በእንግድነት የሚመጡትንም
ተቀበሉ ።
14 የሚያሳድዱአችሁንም መርቁ ፤ መርቁአ
ቸው እንጂ አትርገሙአቸው ። 15 ደስ ከሚላ
ቸው ጋር ደስ ይበላችሁ ፤ ከሚያለቅሱም ጋር
አልቅሱ ። 16 እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ ተስ
ማምታችሁ ኑሩ ፤ ራሳችሁን ከፍ ከማድረግ
ይልቅ ትዕቢትን አስወግዳችሁ ከድኾች ጋር
ተባበሩ ፤* “ያለ እኔ ዐዋቂ የለም” አትበሉ ።
17 በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን ነገር
አድርጉ እንጂ ፤ ሰዎች ክፉ ነገር ሲያደርጉባ
ችሁ እናንተም መልሳችሁ ክፉ ነገር አታድርጉ
ባቸው ። 18 የሚቻላችሁ ቢሆን ፥ ከሰው ሁሉ
ጋር በሰላም ለመኖር በእናንተ በኩል የሚያስፈ
ልገውን ሁሉ አድርጉ ። 19 ወንድሞቼ ሆይ !
ቍጣን ለእግዚአብሔር ተዉ እንጂ ራሳችሁ
አትበቀሉ ፤ ምክንያቱም “የምበቀልና የበቀል
ንም ብድራት የምከፍል እኔ ነኝ ይላል እግዚአ
ብሔር” ተብሎ ተጽፎአል ። 20 ስለዚህ ከመበ
ቀል ይልቅ ጠላትህን ቢርበው አብላው ፤ ቢጠ
ማውም አጠጣው ፤ ይህን ብታደርግ በሐፍረት
እሳት ታቃጥለዋለህ ። 21 ስለዚህ ክፉውን ነገር
በመልካም ነገር አሸንፍ እንጂ በክፉ ነገር አት
ሸነፍ ።

## ምዕራፍ 13

### ለመንግሥት ባለሥልጣኖች መታዘዝ እንደሚገባ

1 ማንኛውም ሥልጣን የሚገኘው በእግዚአ
ብሔር ፈቃድ ስለሆነና አሁን ያሉትም ባለሥል
ጣኖች የተሾሙት በእግዚአብሔር ስለሆነ ፥
ሰው ሁሉ ለመንግሥት ባለሥልጣን መታዘዝ
አለበት ። 2 ስለዚህ ባለሥልጣንን የሚቃወም
ሁሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይቃወማል ፤ የማ
ይታዘዝም ሁሉ በራሱ ላይ የቅጣትን ፍርድ
ያመጣል ። 3 ምክንያቱም ገዥዎች የሚያስፈ
ሩት ክፉ አድራጊዎችን እንጂ መልካም አድራ
ጊዎችን አይደለም ፤ ባለሥልጣንን እንዳትፈራ
ትፈልጋለህን? እንግዲያውስ መልካሙን ነገር
አድርግ ፤ ከእርሱም ምስጋናን ታገኛለህ ። 4 ምክ
ንያቱም ባለሥልጣን ለአንተ መልካም እንዲያደ
ርግ የተሾመ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው ፤
ባለሥልጣን ሰይፍ የታጠቀው በከንቱ ስላልሆነ
ክፉ አድራጊ ከሆንህ ባለሥልጣንን ፍራ ፤ እርሱ
ክፉ አድራጊዎችን በመቅጣትና የእግዚአብሔ
ርን በቀል በማሳየት እግዚአብሔርን ያገለግ
ላል ። 5 ስለዚህ ለመንግሥት ባለሥልጣኖች
መታዘዝ ይገባችኋል ፤ የምትታዘዙትም የእግዚ
አብሔርን ቍጣ ስለመፍራታችሁ ብቻ ሳይ
ሆን ፥ ኅሊናችሁም ስለሚወቅሳችሁ መሆን አለ
በት ።
6 ግብር የምትከፍሉትም ስለዚህ ነው ፤ ምክ
ንያቱም ባለሥልጣኖች በዚህ ሥራ ላይ የተሠማ
ሩት እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው ። 7 እንግ
ዲህ ከመንግሥት ባለሥልጣን በኩል ያለባችሁን
ግዳጅ ፈጽሙ ፤ ግብር ለሚገባው ግብርን ፥
ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን ክፈሉ ፤ መፈራት ለሚ
ገባው መፈራትን ፥ ክብር ለሚገባው ክብርን
ስጡ ።

### እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ

8 የማንም ባለ ዕዳ አትሁኑ ፤ ሊኖርባችሁ
የሚገባ ዕዳ እርስ በርስ መዋደድ ብቻ ይሁን ፤
ምክንያቱም ሰውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞአል ።
9 “አታመንዝር ፤ አትግደል ፤ አትስረቅ ፤ የሌላ
ሰው የሆነውን ማናቸውንም ነገር አትመኝ”
የሚሉት ትእዛዞችና ሌሎችም ትእዛዞች ሁሉ
“ሰውን እንደራስህ አድርገህ ውደድ” በሚለው
በአንዱ ትእዛዝ ተጠቃለው ይገኛሉ ። 10 ሰውን

* 12፥16 ከድኾች ጋር ተባበሩ ፦ ወይም “ዝቅተኛ ሥራ ለመሥራት ፈቃደኞች ሁኑ ።”

የሚወድ ሁሉ ክፉ ነገር አያደርግበትም ፤ ስለ
ዚህ ሰውን የሚወድ ሕግን ሁሉ ፈጽሞአል
ማለት ነው ።
11 እንግዲህ ከእንቅልፍ የምትነቁበት ጊዜ
መድረሱን በማወቅ ይህን ሁሉ አድርጉ ፤ ምክን
ያቱም በፊት ካመንበት ጊዜ ይልቅ አሁን የአዳ
ኛችን መምጫ ቀን ይበልጥ ወደ እኛ ቀርቦ
አል ። 12 ሌሊቱ ሊያልፍ ነው ፤ ቀኑም ቀርቦ
አል ፤ ስለዚህ የጨለማን ሥራ አውልቀን ጥለን
የብርሃንን የጦር መሣሪያ እንልበስ ። 13 በቀን
ብርሃን እንደሚኖሩ ሰዎች በተገቢው አኳኋን
እንመላለስ ፤ ዘፈንንና ስካርን ፤ ዝሙትንና መዳ
ራትን ፤ ጭቅጭቅንና ምቀኝነትን እናስወግድ ።
14 ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት
እንጂ የሥጋችሁን ፍላጎት ለማርካት አታስቡ ።

## ምዕራፍ 14

### በሰው ላይ አለመፍረድ

1 በእናንተ መካከል በእምነቱ ያልጸና ደካማ
ሰው ቢኖር በፍቅር ተቀበሉት እንጂ በአስተሳ
ሰቡ አትፍረዱበት ። 2 ለምሳሌ አንድ ሰው ማን
ኛውንም ነገር ለመብላት የሚያስችል እምነት
ይኖረዋል ፤ በእምነቱ ያልጸና ደካማ ሰው ግን
አትክልት ብቻ ይበላል ፤ 3 ስለዚህ ማንኛውንም
ነገር የሚበላ ሰው የማይበላውን ሰው አይና
ቀው ፤ አትክልት ብቻ የሚበላውም ማንኛው
ንም ነገር በሚበላው ሰው ላይ አይፍረድበት ፤
ምክንያቱም እርሱንም እግዚአብሔር ተቀብሎ
ታል ። 4 ስለዚህ አንተ በሌላው አገልጋይ ላይ
መፍረድ አይገባህም ፤ ምክንያቱም እርሱ
ቢቆም ወይም ቢወድቅ የጌታው ጉዳይ ነው
እንጂ የአንተ ጉዳይ አይደለም ፤ እንዲያውም
ጌታው ሊያቆመው ስለሚችል ጸንቶ ይቆማል ።
5 እንዲሁም "አንዱ ቀን ከሌላው ቀን ይበ
ልጥ ክቡር ነው" ብሎ የሚያስብ ይኖር ይሆ
ናል ፤ ሌላው ደግሞ "ቀኖች ሁሉ እኩል ክብር
አላቸው እንጂ በቀኖች መካከል ልዩነት የለም"
ብሎ ያስባል ። እንግዲህ ይህን በመሳሰለው ነገር
እያንዳንዱ የራሱ አስተሳሰብ ሊኖረው ይች
ላል ። 6 አንዱን ቀን ከሌላው ቀን አስበልጦ የሚ
ያከብር ቢኖር ፤ ይህን ማድረጉ ለጌታ ክብር
ብሎ ነው ፤ ማንኛውንም ምግብ የሚበላ ለጌታ
ክብር ብሎ ይበላል ፤ ስለሚበላውም ምግብ እግ
ዚአብሔርን ያመሰግናል ፤ ማንኛውንም ምግብ
የማይበላ ለእግዚአብሔር ክብር ብሎ አይበ
ላም ፤ ባለመብላቱም እግዚአብሔርን ያመሰግ
ናል ። 7 ከእኛ እያንዳንዱ ሕይወቱም ሆነ ሞቱ
የራሱ አይደለም ። 8 ብንኖር ለጌታ ኢየሱስ እን
ኖራለን ፤ ብንሞትም ለጌታ ኢየሱስ እንሞታ
ለን ፤ ስለዚህ ብንኖርም ፤ ብንሞትም የጌታ ኢየ
ሱስ ነን ። 9 ምክንያቱም ክርስቶስ ሞቶ ከሞት
የተነሣው የሕያዋንና የሙታን ጌታ ለመሆን
ነው ። 10 ታዲያ አንዱ በሌላው ሰው ላይ ለምን
ይፈርዳል? አንዱስ ሌላውን ለምን ይንቃል?
ሁላችንም እኮ በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር
ፊት እንቀርባለን ። 11 ምክንያቱም ፦

"እኔ ሕያው ነኝ ይላል እግዚአብሔር ፤
ሰው ሁሉ በጉልበቱ በእኔ ፊት
ይንበረከካል ፤
በምላሱም እኔ እግዚአብሔር መሆኔን
ይመሰክራል" ተብሎ ተጽፎአል ።

12 ስለዚህ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ሥራ በእግ
ዚአብሔር ፊት ቀርበን መልስ እንሰጣለን ።

### የኃጢአት ምክንያት አትሁን

13 እንግዲህ ከእኛ አንዱ በሌላው ላይ መፍረ
ዱን ይተው ፤ ይልቅስ ሰውን በኃጢአት እሰና
ክሎ የሚጥል ነገርን ላለማድረግ ይወስን ።
14 የጌታ ኢየሱስ ተከታይ እንደ መሆኔ መጠን
ርኩስ የሆነ ምግብ እንደሌለ በእርግጥ ዐውቃ
ለሁ ፤ ነገር ግን አንድ ሰው አንድን ነገር
"ርኩስ ነው" ብሎ የሚያስብ ከሆነ ፤ ያ ነገር
ለእርሱ ርኩስ ነው ። 15 በምግብ ምክንያት
ሰውን የምታስቀይም ከሆንህ በፍቅር የምትኖር
አይደለህም ፤ ስለዚህ ክርስቶስ የሞተለትን ሰው
በምትበላው ምግብ ምክንያት እንዲጠፋ አታድ
ርግ ። 16 እንግዲህ በእናንተ ዘንድ መልካም የሆ
ነውን ነገር ሌሎች እንዲነቅፉት አታድርጉ ።
17 ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት በመ
ንፈስ ቅዱስ የሚገኝ ጽድቅ ፤ ሰላም ፤ ደስታ
ነው እንጂ የመብልና የመጠጥ ጉዳይ አይደ
ለም ። 18 በዚህ ሁኔታ ክርስቶስን የሚያገለግል
ሰው እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል ፤ በሰውም
ዘንድ የተመሰገነ ነው ።
19 ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳ
ችን የምንታነጽበትን ነገር እንከተል ። 20 በምግ
ብም ምክንያት የእግዚአብሔርን ሥራ አናፍ
ርስ ። ምግብ ሁሉ ንጹሕ ነው ፤ ነገር ግን ሌላ
ውን ሰው የሚያሰናክል ምግብ መብላት ስሕ
ተት ነው ። 21 ስለዚህ ሥጋን አለመብላት ፤ የወ
ይን ጠጅን አለመጠጣት ፤ ሌላውን ሰው የሚያ
ሰናክል ማንኛውንም ነገር አለማድረግ መልካም
ነው ። 22 እንግዲህ ይህ የግል እምነትህ በአን
ተና በእግዚአብሔር መካከል ይሁን ፤ ምክንያ
ቱም ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበትን ነገር
ሲያደርግ ኅሊናው የማይወቅሰው ሰው የተመሰ
ገነ ነው ። 23 እየተጠራጠረ የሚበላ ሰው ግን
ድርጊቱ በእምነት ላይ የተመሠረተ ስላልሆነ
ይፈረድበታል ፤ ምክንያቱም በእምነት ያልተደ
ረገ ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው ።

14፡1-6 ፦ ቆላ. 2፡16 ። 14፡10 ፦ 2ቆሮ. 5፡10 ። 14፡11 ፦ ኢሳ. 45፡23 ።



## ምዕራፍ 15

### ሰዎችን ማስደሰት እንደሚገባ

1 እኛ በእምነት ብርቱዎች የሆንን ፤ የደካሞ
ችን ድካም መሸከም ይገባናል እንጂ ራሳችንን
ብቻ የምናስደስት መሆን የለብንም ፤ 2 እያንዳን
ዳችን ፤ ሌላው ሰው በእምነቱ እንዲጠነክር ፤
እርሱን የሚጠቅመውንና የሚያስደስተውን
ነገር እናድርግ ። 3 ምክንያቱም ክርስቶስ ራሱን
ደስ አላሰኘም ፤ ይልቁንም "ተሳዳቢዎች አን
ተን እንደሰደቡ ! እኔንም ሰደቡኝ" ተብሎ እን
ደተጻፈ ሆነበት ። 4 ከቅዱሳት መጻሕፍት በምና
ገኘው ትዕግሥትና መጽናናት ተስፋ እንዲኖረን
አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ትምህርት እንድናገ
ኝበት ተጽፎአል ። 5 እናንተ የኢየሱስ ክርስቶስ
ተከታዮች በመሆናችሁ ፤ የትዕግሥትና የመጽና
ናት አምላክ ፤ የአንድነትን መንፈስ ይስጣ
ችሁ ። 6 እንዲሁም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ
አባት የሆነውን አምላክ[2*] በአንድ ልብና በአ
ንድ ቃል እንድታከብሩ ያድርጋችሁ ።

### የጳውሎስ አገልግሎትና ለአረማውያን የደረሰ የምሥራች ቃል

7 እንግዲህ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያከ
ብሩ ክርስቶስ እናንተን እንደተቀበላችሁ ፤ እና
ንተም እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ ። 8 ይህንንም
ስናገር ፤ እግዚአብሔር ለነገድ አባቶች የሰጠው
ተስፋ እንዲፈጸምና የእግዚአብሔርም ታማኝ
ነት እንዲታወቅ ፤ ክርስቶስ የአይሁዳውያን አገ
ልጋይ ሆነ ማለቴ ነው ። 9 ክርስቶስ የአይሁዳው
ያን አገልጋይ የሆነበትም ሌላው ምክንያት አረ
ማውያን እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ እንዲያ
መሰግኑት ነው ፤

"በአረማውያን መካከል አመሰግንሃለሁ ፤
ለስምህም በዝማሬ ምስጋና
አቀርባለሁ"

ተብሎ እንደ ተጻፈው ነው ። 10 ደግሞም ፤

"እናንተ አረማውያን ፤
እግዚአብሔር ከመረጠው ሕዝብ ጋር
ደስ ይበላችሁ" ተብሎ
ተጽፎአል ።

11 እንደገናም ፤

"አረማውያን ሁሉ እግዚአብሔርን
አመስግኑት ፤
ሕዝቦች ሁሉ አመስግኑት" ተብሎ
ተጽፎአል ።

12 እንዲሁም ኢሳይያስ ፤

"ከእሴይ ዘር የሚወለድ ይመጣል ፤
የአረማውያንም መሪ ለመሆን
ይነሣል ፤
እነርሱም ተስፋቸውን በእርሱ
ያደርጋሉ" ይላል ።

13 ተስፋችሁ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል እያደገ
እንዲሄድ ፤ የተስፋ አምላክ በእርሱ በመታመና
ችሁ ደስታንና ሰላምን በሙላት ይስጣችሁ ።

### ጳውሎስ በድፍረት የጻፈበት ምክንያት

14 ወንድሞቼ ሆይ ! በደግነት የተሞላችሁ ፤
በዕውቀት የበለጸጋችሁና እያንዳንዳችሁም ሌላ
ውን ለመምከር የምትችሉ መሆናችሁን እልጠ
ራጠርም ። 15 አንዳንድ ነገሮችን ላስታውሳችሁ
ፈልጌ ይህን መልእክት በድፍረት ጻፍሁላችሁ ፤
በድፍረት የጻፍሁላችሁም እግዚአብሔር በሰ
ጠኝ ጸጋ መሠረት ነው ። 16 ይህም ጸጋ የተሰ
ጠኝ የእግዚአብሔርን የምሥራች ቃል ለአረማ
ውያን በማብሠር እንደ ካህን ሆኜ ኢየሱስ ክርስ
ቶስን ለማገልገል ነው ፤ ስለዚህ አረማውያን
በመንፈስ ቅዱስ የተቀደሰና እግዚአብሔርንም
ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት ሆነው እንዲቀርቡ
አገለግላለሁ ። 17 በዚህ ምክንያት የኢየሱስ ክር
ስቶስ ሆኜ እግዚአብሔርን ለማገልገል በመቻሌ
እመካለሁ ። 18 የምመካውም ፤ ክርስቶስ በእኔ
ቃልና ሥራ አማካይነት አረማውያን ለእግዚአብ
ሔር እንዲታዘዙ በማድረጉ ነው ፤ 19 እንዲሁም
በታላላቅ ተአምራትና በድንቅ ሥራዎች ፤ በመ
ንፈስ ቅዱስም ኀይል አረማውያን እንዲታዘዙ
በማድረጉ እመካለሁ ። በዚህም ሁኔታ ከኢየሩሳ
ሌም እስከ እልዋሪቆን ድረስ እየዞርሁ የክርስቶ
ስን መልካም ዜና በሙሉ አብሥሬአለሁ ።
20 የዘወትር ምኞቴም ፤ ሌላው ሰው በጣ
ለው መሠረት ላይ መገንባት ሳይሆን ፤ የክርስ
ቶስ ስም ባልተሰማበት ስፍራ ሁሉ መልካሙን
ዜና ማብሠር ነው ። 21 ይህም ፦

"ስለ እርሱ ያልተነገራቸው ያያሉ ፤
ስለ እርሱ ያልሰሙም ያስተውላሉ"

ተብሎ እንደተጻፈው ነው ።

### ጳውሎስ ወደ ሮም ለመሄድ ዐቀደ

22 እስከ አሁን ወደ እናንተ ለመምጣት ያል
ቻልኩት ፤ ቀደም ብዬ በተናገርሁት ምክንያት
ነው ። 23 አሁን ግን በዚህ አካባቢ ባሉት አገ
ሮች የነበረኝን ሥራ ስለ ጨረስሁና ከብዙ ዓመ
ታት ጀምሬም እናንተን ለመጐብኘት ከፍ ያለ
ምኞት ስላለኝ ፤ 24 ወደ እስፔን በምሄድበት
ጊዜ እግረ መንገዴን ልጐበኛችሁ ዐቅጃለሁ ።

[2*] 15፡6 አዲስ ኪዳን መጀመሪያ በተጻፈበት በግሪክኛው ቋንቋ "የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይመስገን" ይላል ።
15፡3 ፦ መዝ. 69፡9 ። 15፡9 ፦ 2ሳሙ. 22፡50 ፤ መዝ. 18፡49 ። 15፡10 ፦ ዘዳ. 32፡43 ። 15፡11 ፦ መዝ. 117፡1 ።
15፡12 ፦ ኢሳ. 11፡10 ። 15፡21 ፦ ኢሳ. 53፡15 ። 15፡22 ፦ ሮም 1፡13 ።

ለጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር ከቆየሁ በኋላ ፥ ጕዞ
ዬን ለመቀጠል የሚያስችለኝን ዕርዳታ እንደም
ታደርጉልኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። [25]አሁን ግን
ለአማኞች የሚሰጥ የገንዘብ ዕርዳታ ይዤ ወደ
ኢየሩሳሌም እሄዳለሁ ። [26]ምክንያቱም የመቄዶ
ንያና የአካይያ አማኞች በኢየሩሳሌም አማኞች
መካከል ላሉት ድኾች የገንዘብ ዕርዳታ ለመላክ
ስለወሰኑ ነው ። [27]ይህንንም ዕርዳታ በፈቃደኝ
ነት የለገሱት ግዴታቸው በመሆኑ ነው ፤ ምክን
ያቱም አረማውያን ከአይሁዳውያን ጋር የመን
ፈስ በረከት ተካፋዮች ከሆኑ ፥ አረማውያንም
በሥጋዊ በረከታቸው አይሁዳውያንን የመርዳት
ግዴታ አለባቸው ። [28]ስለዚህ ይህን የተሰበሰበ
ውን የገንዘብ ዕርዳታ ወደ ኢየሩሳሌም ወስጄ
የማስረከብ ሥራዬን ከፈጸምሁ በኋላ ፥ ወደ
እስፔን እሄዳለሁ ፤ እግረ መንገዴንም እናንተን
እጐበኛችኋለሁ ። [29]ወደ እናንተ በምመጣበት
ጊዜም የክርስቶስን በረከት በሙላት ይዤላችሁ
እንደምመጣ ዐውቃለሁ ።
[30]ወንድሞቼ ሆይ! ስለ እኔ ወደ እግዚአብ
ሔር በመጸለይ በትግሌ እንድትረዱኝ ፥ በጌታ
ችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ፍቅር
እለምናችኋለሁ ። [31]የምትጸልዩልኝም በይሁዳ
ካሉት ከማያምኑ ሰዎች እጅ እንድድንና በኢየ
ሩሳሌም ያለኝ አገልግሎትም በአማኞች ዘንድ
ደስ የሚያሰኝ እንዲሆን ነው ። [32]ይህም ከሆነ
በኋላ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን ወደ እና
ንተ በደስታ መጥቼ ከእናንተ ጋር ማረፍ እወዳ
ለሁ ። [33]ሰላምን የሚሰጥ እግዚአብሔር ከሁላች
ሁም ጋር ይሁን ፤ አሜን ።

## ምዕራፍ 16

### ሰላምታ

[1]ፌቤ በክንክሪያ ከተማ ፥ ቤተ ክርስቲያንን
የምታገለግል ታማኝ እኅታችን መሆንዋን እንድ
ታውቁ እወዳለሁ ። [2]እርስዋ እኔንና ሌሎችንም
ብዙ ሰዎች የረዳች ስለሆነች ፥ የእግዚአብሔር
ሰዎች እንግዶችን መቀበል እንደሚገባቸው ዐይ
ነት በጌታ ስም ተቀብላችሁ በሚያስፈልጋት
ነገር ሁሉ እንድትረዱአት ዐደራ እላችኋለሁ ።
[3]በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ተባባሪዎቼ ለሆ
ኑት ለጵርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ ፤
[4]እነርሱ በእኔ ምትክ ለመሞት እንኳ የተዘጋጁ
ነበሩ ፤ በዚህም ዘወትር አመሰግናቸዋለሁ ፤
እኔም ብቻ ሳልሆን የአረማውያን አብያተ ክርስ
ቲያናት ጭምር ያመሰግኑዋቸዋል ። [5]በእነርሱ
ቤት ለጸሎት ለሚሰበሰቡት ምእመናንም ሰላ
ምታ አቅርቡልኝ ።
በእስያ ክፍለ ሀገር በመጀመሪያ በክርስቶስ
ላመነውና ለምወደው ለኤጶኔቶስ ሰላምታ አቅ
ርቡልኝ ። [6]ለእናንተ ብዙ ለደከመችው ለማር
ያም ሰላምታ አቅርቡልኝ ። [7]ከእኔ ጋር ታስ
ረው ለነበሩና በሐዋርያትም መካከል ታዋቂ
ዎች ለነበሩት አይሁዳውያን ዘመዶቼ ለአንድሮ
ኒቆስና ለዩኒያስ[3*] ሰላምታ አቅርቡልኝ ፤ እነርሱ
በክርስቶስ በማመን እኔን ይቀድሙኛል ።
[8]በጌታ ለምወደው ለአምፕልያቶስ ሰላምታ
አቅርቡልኝ ፤ [9]በክርስቶስ ሥራ ተባባሪያችን
ለሆነው ለዑርባኖስና ለምወደውም ለእስጣኩስ
ሰላምታ አቅርቡልኝ ። [10]በክርስቶስ መሆኑ
ተፈትኖ ለተመሰገነው ለአጵሊስ ሰላምታ አቅር
ቡልኝ ፤ ከአርስጦቡሎስ ቤተ ሰብ ለሆኑትም
ሰላምታ አቅርቡልኝ ፤ [11]ለአይሁዳዊ ዘመዴ
ለሄሮድዮን ሰላምታ አቅርቡልኝ ፤ ከናርሲሶስ
ቤተ ሰዎች በጌታ ላመኑት ሰላምታ አቅርቡ
ልኝ ።
[12]በጌታ አገልግሎት ለሚደክሙት ለትሩፋ
ይናና ለትሩፎሳ ሰላምታ አቅርቡልኝ ። በጌታ
አገልግሎት እጅግ ለደከመችውና በክርስቶስ
ለምወዳት ለፔርሲስ ሰላምታ አቅርቡልኝ ።
[13]ጌታን በማገልገል በጣም ለታወቀው ለሩፎስ
ሰላምታ አቅርቡልኝ ፤ እኔን እንደ ልጅዋ ትወ
ደኝ ለነበረችው ለእናቱም ሰላምታ አቅርቡ
ልኝ ። [14]ለአስንክሪቶስና ለፍሌጎን ፥ ለሄርሜ
ስም ለፓትሮባስም ለሄርማስም ከእነርሱም ጋር
ላሉ አማኞች ወንድሞች ሰላምታ አቅርቡልኝ ።
[15]ለፊሎሎጎስ ፥ ለዩልያ ፥ ለኔርያና ለእኅቱም
ሰላምታ አቅርቡልኝ ፤ እንዲሁም ለኦሉምጳስና
ከእርሱም ጋር ላሉ አማኞች ሁሉ ሰላምታ አቅ
ርቡልኝ ። [16]በወንድማማችነት ስሜት በመሳ
ሳም ሰላምታ ተሰጣጡ ። የክርስቶስ አብያተ
ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል ።

### የመጨረሻ ምክር

[17]ወንድሞቼ ሆይ! በመካከላችሁ መለያየ
ትን ከሚፈጥሩትና በእምነታችሁ እንዳትጠነ
ክሩ ከሚያደርጉት ሰዎች ተጠንቀቁ ፤ የተቀበላ
ችሁትን ትምህርት የሚቃወሙም ስለሆኑ ከእነ
ርሱ ራቁ ። [18]እንደእነዚህ ዐይነት ሰዎች የራሳ
ቸውን ክፉ ምኞት የሚከተሉ ናቸው እንጂ
ጌታችንን ክርስቶስን የሚያገለግሉ አይደሉም ፤
ጥሩ ቃል መስሎ በሚታይና በሚያቈላምጥ ንግ
ግር ተንኰል የሌለባቸውን የዋሆች ያታልላሉ ።
[19]ለምሥራቹ ቃል ታዛዦች መሆናችሁ
በሰው ሁሉ ዘንድ ስለታወቀ ደስ ብሎኛል ፤
ነገር ግን ለመልካም ነገር ጥበበኞች ፥ ለክፉ
ነገር ግን የዋሆች እንድትሆኑ እፈልጋለሁ ።
[20]ይህን ብታደርጉ ሰላምን የሚሰጥ እግዚአብ
ሔር ሰይጣንን በእግራችሁ ሥር ይቀጠቅጥ
ላችኋል ።

[3*] 16፡7 ዩኒያስ ፦ አንዳንድ ቅጂዎች "ዩሊያ" ይላሉ ።

15፡25-26 ፦ 1ቆሮ. 16፡1-4 ። 15፡27 ፦ 1ቆሮ. 9፡11 ። 16፡3 ፦ ሐ.ሥ. 18፡2 ። 16፡13 ፦ ማር. 15፡21 ።



የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ
ጋር ይሁን ።
[21]የሥራ ተባባሪዬ ጢሞቴዎስ ሰላምታ ያቀ
ርብላችኋል ፤ እንዲሁም አይሁዳውያን ዘመዶቻ
ችን የሆኑት ሉቂዮስና ኢያሶን ሶሲጳጥሮስም
ሰላምታ ያቀርቡላችኋል ።
[22]ይህን መልእክት የጻፍሁ እኔም ጠርጥዮስ
በጌታ ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ ።
[23]እኔን አሁን የሚያስተናግደኝና እዚህ
ያሉት ምእመናን በቤቱ ለጸሎት እንዲሰበሰቡ
የሚያደርገው ጋይዮስ ሰላምታ ያቀርብላችኋል ፤
የከተማይቱ በጅሮንድ የሆነው ኤራስጦስ ፥ ወን
ድማችንም ቋርጦስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል ።
[[24]የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ
ጋር ይሁን ፤ አሜን ።]

### የምስጋና ጸሎት

[25]እንግዲህ ለእግዚአብሔር ምስጋና
ይሁን! እኔ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የማበሥረው
የምሥራች ቃልና ለብዙ ዘመናት ተደብቆ
አሁን በተገለጠው እውነት ፥ እግዚአብሔር
በእምነታችሁ ጸንታችሁ እንድትቆሙ ሊያደር
ጋችሁ ይችላል ። [26]ይህም እውነት አሁን በነ
ቢያት መጻሕፍት አማካይነት በግልጥ ታይቶ
አል ፤ ሁሉም አምነው እንዲታዘዙ በሕያው
አምላክ ትእዛዝ ሕዝቦች ሁሉ እንዲያውቁት
ተደርጐአል ።
[27]እርሱ ብቻ ጥበበኛ ለሆነው ለአንድ አም
ላክ ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ምስጋና
ይሁን! አሜን ።

# የመጀመሪያው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት

# ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

## መግቢያ

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈላቸው የመጀመሪያው መልእክት የተጻፈው ጳውሎስ በቆሮን ቶስ ባቋቋመው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክርስትናን ሕይወትና እምነት በሚመለከት ተነሥቶ ስለነበረው ችግር መፍትሔ ለማስገኘት በማሰብ ነው ። በዚያን ጊዜ ቆሮንቶስ ዓለም አቀፋዊ የሆነች የግሪክ ከተማ ከመሆንዋም በላይ አካይያ ለተባለ የሮም ግዛት ዋና ከተማ ነበረች ። ይህች ከተማ ታላቅ በሆነ የንግድ እንቅስቃሴ ፥ በደረጀ ባሕል ፥ እጅግ በመስፋፋት ላይ በነበረ ስድነት ወይም የሞራል ውድቀትና በሃይማኖቶች ብዛት የታወቀች ነበረች ።

ሐዋርያው በተለይ ያተኰረው በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ስለነበረው መከፋፈልና የስድነት ሕይወት ፥ እንዲሁም ስለ ፍትወተ ሥጋና ስለ ጋብቻ ፥ ስለ ኅሊና ጥያቄዎች ፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና ስለ ትንሣኤ ነበር ፤ የምሥራቹ ቃል ስለነዚህ ጥያቄዎች የሚናገረውን በጥንቃቄ ያቀርባል ።

ፍቅር እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከሰጣቸው ስጦታዎች የበለጠ መሆኑን የሚገልጠው ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት ፥ ከዚህ መጽሐፍ እጅግ ታዋቂ የሆነው ክፍል እንደሆነ ይገመታል ።

---

## ምዕራፍ 1

[1]በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ
ሐዋርያ ለመሆን ከተጠራው ከጳውሎስና ከወን
ድማችንም ከሶስቴንስ ፤
[2]ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ባላቸው ኅብረት
የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢ
የሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት
ክርስቲያኖች ጋር ፥ የእግዚአብሔር ቅዱስ
ሕዝብ ለመሆን ለተጠሩት ለቆሮንቶስ ክርስቲያ
ኖች ሁሉ ፦
[3]ከአባታችን ከእግዚአብሔርና ከጌታ ከኢየ
ሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን ።

### ምስጋና ለእግዚአብሔር

[4]በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እግዚአብ
ሔር ጸጋውን ስለ ሰጣችሁ በእናንተ ምክንያት
ሁል ጊዜ አመሰግነዋለሁ ። [5]በሁሉ ነገር በቃ
ልም ሆነ በዕውቀት ፥ በክርስቶስ በልጽ
ጋችኋል ። [6]ስለ ክርስቶስ የነገርናችሁ ምስክር
ነት በእናንተ ዘንድ ጸንቶአል ። [7]ስለዚህ የጌታ
ችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ በመጠባበቅ

16፡21 ፦ ሐ.ሥ. 16፡1 ። 16፡23 ፦ ሐ.ሥ. 19፡29 ፤ 1ቆሮ. 1፡14 ፤ 2ጢሞ. 4፡20 ።
1፡2 ፦ ሐ.ሥ. 18፡1 ።